# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ሰኞ 82ኛ ዓመት ቁጥር 359 ነሐሴ 29 ቀን 2015 ዓ.ም ዋጋ 10.00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!









ፎቶ - አዩብ ተፈሪ

# የዓድዋ ሙዚየም ግንባታ በሦስት ወራት ጊዜ ውስጥ ይጠናቀቃል

- የግንባታው ሂደት 87 በመቶ ደርሷል

**ማርቆስ በላይ**

አዲስ አበባ፡- የዓድዋ ሙዚየም ፕሮጀክት ከሦስት ወራት ባልበለጠ ጊዜ እንደሚጠናቀቅ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሜጋ ፕሮጀክቶች ግንባታ ጽህፈት ቤት አስታወቀ፡፡ የፕሮጀክቱ ግንባታ ሂደት 87 በመቶ መጠናቀቁም ተገልጿል፡፡

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሜጋ ፕሮጀክቶች ግንባታ ጽህፈት ቤት ኮንትራት አስተዳደር ዳይሬክተር አቶ ዳዊት ጥበቡ እንደገለጹት፤ከተማ አስተዳደሩ ከሚያስገነባቸው ዘርፈ ብዙ አገልግሎት ሰጪ ፕሮጀክቶች መካከል አንዱ የሆነው የዓድዋ ዜሮ ኪሎ ሜትር ፕሮጀክት ከሦስት ወራት ባልበለጠ ጊዜ ይጠናቀቃል፡፡

እንደ አቶ ዳዊት ገለጻ፤ ፕሮጀክቱ አራት ነጥብ

የዓድዋ ሙዚየም ... ወደ ገጽ 6 ዞሯል









# በድሬዳዋ አስተዳደር፡-

- በሰንበት ገበያ ከ750 ሚሊዮን ብር በላይ የንግድ ትስስር ተፈጥሯል
- ከ5ሺህ 500 በላይ ሕገወጥ ነጋዴዎች ላይ ርምጃ ተወስዷል

**ዳግማዊት ግርማ**

አዲስ አበባ፡- በድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር በ2015 በጀት ዓመት በሰንበት ገበያ ከ750 ሚሊዮን በላይ የንግድ ትስስር መፈጠሩ ተገለጸ፡፡ የተጋነነ የገበያ ዋጋ ጭማሪ ያደረጉ 5ሺህ 589 ነጋዴዎች ላይ አስተዳደራዊና ሕጋዊ ርምጃዎች ተወስደዋል፡፡

የድሬዳዋ ከተማ የንግድ ፅህፈት ቤት ኃላፊ አቶ አሚኑ ጠሃ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ በበጀት ዓመቱ የኑሮ ውድነትን ለመቀነስና የዋጋ ንረትን ለመከላከል የተከናወኑ ተግባራት ውጤታማ ነበሩ፡፡

በተለይ በሰንበት ገበያ ከ750 ሚሊዮን ብር በላይ የንግድ ትስስር መፈጠሩን የገለጹት ሃላፊው፤ በዚህም ህብረተሰቡ በመደበኛ ገበያ ቢገበያይ ኖሮ ሊያወጣ የነበረውን 450 ሚሊዮን ብር ማዳን ተችሏል ብለዋል፡፡

አቅርቦትንና ፍላጎትን ለማሻሻል በገጠር አራቱም ክላስተሮችና 38 ቀበሌዎች እና በከተማ 22 ቦታዎች በድምሩ 60 ቦታዎች የቅዳሜና እሁድ ገበያዎችን በመክፈት አቅርቦትን በማሻሻል ገበያን ማረጋጋት ተችሏል ሲሉ ተናግረዋል፡፡

በድሬዳዋ አስተዳደር ... ወደ ገጽ 6 ዞሯል








## በዞኑ የተፈጠረውን አንጻራዊ ሰላም ለማጽናት እየተሠራ ነው

ገጽ 6






## በሕገወጥ የወርቅ አምራቾችና ነጋዴዎች ላይ ርምጃ ተወሰደ

ገጽ 6



አቶ ገብረማርያም ሰጠኝ



ወይዘሮ መጅዲያ ሐቢብ፤

# በአነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዝ ከ122 ሺ በላይ የሥራ እድል ተፈጥሯል

**ራስወርቅ መሉጌታ**

አዲስ አበባ፡- በአነስተኛና መካከለኛ አምራች ኢንተርፕራይዞች እንደ ሀገር ከ122 ሺ በላይ ለሚሆኑ ዜጎች የሥራ እድል መፍጠር መቻሉን የኢትዮጵያ ኢንተርፕራይዝ ልማት አስታወቀ።

በኢንተርፕራይዙ የስትራቴጂክ ጉዳዮች ሥራ አስፈጻሚ ወይዘሮ መጅዲያ ሐቢብ በተለይ ለአዲስ ዘመን ጋዜጣ እንደተናገሩት በተጠናቀቀው በጀት ዓመት አዲስ አምራች ኢንተርፕራይዞችን በማቋቋምና ነባሮችን በማጠናከር ከ122 ሺ 300 በላይ ለሚሆኑ ዜጎች ሥራ መፍጠር ተችሏል። በዚሁ ጊዜ ውስጥ 5 ሺ 47 አዳዲስ አምራች ኢንተርፕራይዞች የተቋቋሙ ሲሆን 16 ሺ 362 የሚሆኑት ላይ የማጠናከር ሥራ ተሰርቷል። ለሥራ ማስኬጃ ሁለት ነጥብ አራት ቢሊዮን ብር እንዲሁም ለካፒታል እቃዎች ፋይናንስ ከሶስት ቢሊዮን ብር ባላይ ወጪ መደረጉን አስረድተዋል።

በበጀት አመቱ ከወጪ ንግድ ከ33 ነጥብ ሶስት ሚሊዮን ዶላር በላይ ማግኘት የተቻለ ሲሆን ተኪ ምርት በማምረትም ይወጣ የነበረውን ከ428 ሺ 700 ሚሊዮን ዶላር በላይ ማስቀረት ተችሏል። ለቀጣይ ዓመትም ወደ ውጭ ከሚላኩ ምርቶች 37 ሺ 400 ሚሊዮን ዶላር በላይ ለማግኘትና ተኪ ምርት በማምረትም ከ311 ሚሊዮን በላይ ዶላር ወጪ ለመታደግ እንደሚሠራ አስረድተዋል።

በበጀት ዓመቱ 503 ከአነስተኛ ወደ መካከለኛ እንዲሁም 56 ከመካከለኛ ወደ ከፍተኛ ማሸጋገር መቻሉን በማስታወስ ይህንን ውጤታማ አፈጻጸም በማስቀጠል በ2016 ዓ.ም የበጀት ዓመት 559 ኢንተርፕራይዞችን በየደረጃው በማብቃት ለማሸጋጋር እንደሚሠራ ገልጸዋል።

የተቋሙ ዓላማ ኢንተርፕራይዞች እንዲስፋፉና እንዲጠናከሩ በማድረግ ፍትሃዊ የሀብት ክፍፍልን ለማረጋገጥ የሚደረገውን ጥረት መደገፍ፤ ለከፍተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት መሠረት መጣል፤ እንዲሁም አምራች ኢንተርፕራይዞችን ለማስፋፋትና ለማጠናከር አስፈላጊ መሠረተ ልማቶችን በማልማትና በማስተዳደር ዘርፉን ተወዳዳሪና ውጤታማ እንዲሆን ማስቻል ነው ያሉት ሥራ አስፈጻሚዋ፤ በዘርፉ እንደ ሀገር ከፍተኛ ውጤት የሚጠበቅ መሆኑን ተናግረዋል፡፡

በቀጣይ አመት አዳዲስ ኢንተርፕራይዞችን በማቋቋምና ነባሮችን በማጠናከር ከ181 ሺ 500 በላይ ለሚሆኑ ዜጎች የሥራ እድል ለመፍጠር ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በቅንጅት እንደሚሰራ በመግለጽም ለዚህ ሥራ ማስኬጃና ለካፒታል እቃ አቅርቦት ስድስት ቢሊዮን ብር የሚጠጋ ወጪ መመደቡን ጠቁመዋል።

# በክልሉ ሁለት ነጥብ አራት ሚሊዮን ተማሪዎች በትምህርት ገበታቸው ላይ ይገኛሉ

## - 110 ትምህርት ቤቶች ለተፈናቃዮች መጠለያነት እያገለገሉ ነው

**ቃልኪዳን አሳዬ**

አዲስ አበባ፡- በ2016 ዓ.ም የትምህርት ዘመን ሁለት ነጥብ አራት ሚሊዮን ተማሪዎች በትምህርት ገበታቸው ላይ ይገኛሉ ተብሎ እንደሚጠበቅ የትግራይ ክልል ትምህርት ቢሮ አስታወቀ፡፡ በክልሉ የሚገኙ 110 ትምህርት ቤቶች ለተፈናቃዮች መጠለያነት እያገለገሉ መሆኑ ተገልጿል፡፡

የክልሉ ትምህርት ቢሮ ኮሙኒኬሽን ዳይሬክተር ተወካይ አቶ ሰለሞን ገብረታትዮስ ለኢፕድ እንደገለጹት፤ በክልሉ ከነበረው ግጭት ጋር ተያይዞ የተዛባውን የትምህርት ሥርዓት በማስተካከልና ጉዳት የደረሰባቸውን ትምህርት ቤቶች አገልግሎት ለማስጀመር የተለያዩ እንቅስቃሴዎች በመደረግ ላይ ይገኛሉ፡፡

በ2016 ዓ.ም የትምህርት ዘመን ሁለት ነጥብ አራት ሚሊዮን ተማሪዎች በትምህርት ገበታቸው ይገኛሉ ተብሎ ይጠበቃል ያሉት አቶ ሰለሞን፤ ከነሐሴ 25 እስከ መስከረም 12 የተማሪዎች የምዝገባ ጊዜ እየተከናወነ ይገኛል ብለዋል።

አቶ ሰለሞን እንዳስታወቁት፤ አሁን ላይ በግጭት ወቅት የባከነውን የትምህርት ጊዜ ለማካካስ የሚያስችል ትምህርት እየተሰጠ ነው። መስከረም 16 ቀን 2016 ዓ.ም መደበኛው የመማር ማስተማር ሂደት ይጀመራል።

በክልሉ ሁለት ሺህ 494 ትምህርት ቤቶች ይገኛሉ፤ ከዚህ ውስጥ አንድ ሺህ 666ቱን ጊዜያዊ አስተዳደሩ ይቆጣጠራቸዋል ብለዋል።

ዓመታትን በፈጀው ግጭት ሁሉም በሚባል መልኩ ግብዓቶቻቸው ጉዳት እንደረሰባቸው ጠቁመው፤ የጥቁር ሰሌዳ፣ የተማሪዎች መቀመጫ፣ የመጽሀፍትና የተለያዩ ግብዓቶች እጥረት እንዳለባቸው ተናግረዋል፡፡



አቶ ሰለሞን ገብረታትዮስ

ጉዳት የደረሰባቸው ትምህርት ቤቶች በመጠገን ወደሥራ ለማስገባት እንቅስቃሴዎች እየተደረጉ ነው ያሉት አቶ ሰለሞን፤ በነበረው ግጭት የአካል ጉዳት የደረሰባቸው በርካታ መምህራንና ተማሪዎች በመኖራቸው ከችግሮቻቸው ማገገም እንዲችሉ የተለያዩ ድጋፎች እንደሚደረግላቸው አስረድተዋል።

ከተለያዩ ግብረ ሰናይ ድርጅቶች፣ ከአካባቢው ማህበረሰብና በተለያዩ ሀገራት የሚገኙ የትግራይ ተወላጆች ጋር በጋራ በመሥራት የትምህርት ቁሳቁሶችን የማሟላት ሥራ እየተከናወነ መሆኑን ገልጸዋል።

በቀጣይም የተለያዩ የገቢ ማስገኛ ቴሌቶኖችን ለማዘጋጀት መታቀዱን አስታውቀው፤ ዘርፉን ለማጠናከር የሚደረገው ጥረት ተጠናክሮ እንደሚቀጥል አመላክተዋል።

2015 ዓ.ም 844 ሺህ የሚጠጉ ተማሪዎች በትምህርት ገበታቸው ተገኝተዋል፤ በርካታ ትምህርት ቤቶች ለተፈናቃዮች መጠለያነት እያገለገሉ ይገኛል ብለዋል።

አቶ ሰለሞን እንዳስታወቁት፤ በትግራይ ክልል 110 ትምህርት ቤቶች የተፈናቃይ መጠለያ ሆነው በማገልገል ላይ ናቸው። ተፈናቃዮችን ወደቄያቸው መመለስ ካልተቻለ በአካባቢዎቹ የሚገኙ ተማሪዎችን ወደመማር ማስተማር ሂደቱ ለመመለስ አዳጋች ይሆናል፡፡

በተጨማሪ በግጭቱ ምክንያት የመማሪያ መጻሕፍት በመውደማቸውና ለአዲስ የትምህርት ሥርዓት የሚሆኑ መጻሕፍትን ማዘጋጀት አዳጋች ነው ያሉት አቶ ሰለሞን፤ የትምህርት ሥርዓቱን በቴክኖሎጂ በመደገፍ በዲጂታል ቤተ-መጻሕፍት እንዲሁም የቴሌቪዥንና በሬዲዮ ትምህርት በማቅረብ ያለውን ክፍተት ለመሙላት እንቅስቃሴዎች በመደረግ ላይ ናቸው ብለዋል።

አቶ ሰለሞን እንዳመለከቱት፤ እስከ 2018 ዓ.ም ድረስ ከአንደኛ እስከ ስምንተኛ ክፍል ለሚገኙ ተማሪዎች በቀድሞው ሥርዓተ ትምህርት ካሪኩለም አማካኝነት ትምህርት እንዲያገኙ ይደረጋል።

አስፈላጊ የመማሪያ መጻሕፍትን በወቅቱ ማሟላት ከተቻለ በ2016 ዓ.ም አዲሱን ሥርዓተ ትምህርት በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ላይ ተግባራዊ ለማድረግ መታቀዱን አስታውቀዋል።

በክልሉ ያለውን የትምህርት ግብዓትና የቁሳቁስ እጥረት በመገንዘብ ሁሉም የህብረተሰብ ክፍልና የተለያዩ ተቋማት ድጋፍ እንዲያደርጉም ጥሪ አቅርበዋል፡፡

# ‹‹የየእምነቱ መምህራን ተከታዮቻቸው ፈጣሪን የመፍራት መንፈስ እንዲላበሱ ሊያስተምሩ ይገባል››

## - ሼክ ዛኪር ኢብራሂም
## በኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክርቤት የሰላም ዘርፍ ሥራ አስፈጻሚ

**ዘሳለም ግዛው**

አዲስ አበባ፡- የየእምነቱ አስተማሪዎች የሰላምን አስተምህሮ በማጠናከር ተከታዮቻቸው በሥነምግባር እንዲታነጹ፣ ፈጣሪን የመፍራት መንፈስ እንዲላበሱ ሃላፊነታቸውን መወጣት እንደሚገባቸው በኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤት የሰላም ጉዳይ ሥራ አስፈጻሚ ሼክ ዛኪር ኢብራሂም ገለጹ።

ሼክ ዛኪር ኢብራሂም ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የመማር፣ የማምለክ፣ ወጥቶ የመግባት ትርጉሙ የሚለካው በሰላም አውድ ውስጥ ነው። የሰላም መስፈን ለእምነት ተቋማት፣ ለቤተሰብ፣ ለሀገር ግንባታም ያስፈልጋል።

የአስተምህሮት ጉድለት ባይኖር በየትኛውም እምነት ውስጥ አንድ አማኝ ፈጣሪን የማያስደስት ድርጊት አይፈጽምም ነበር፣ በመሆኑም የአስተምህሮት ጉድለትን ማስተካከል ይገባል ብለዋል።

አሁን አሁን ከዚህ በፊት ያልነበሩ ችግሮች እና ጭካኔዎች እየተከሰቱ ይገኛሉ ያሉት ሼክ ዛኪር፤ እምነት እየተስፋፋ ባለበት ወቅት አጋጣሚ ጥፋቶች መበራከታቸው ምክንያቱን መመርመር ያስፈልጋል ብለዋል።

የየእምነቱ አስተማሪዎች የእምነት ተከታዮችን በማስተማር ፈጣሪን በመፍራትና በመልካም ሥነ ምግባር በማነጽ ሃላፊነታቸውን ሊወጡ እንደሚገባም አሳስበዋል።

አብዛኛው ኢትዮጵያዊ አማኝ ቢሆንም ዘረፋ እና ግድያ ዛሬም ይስተዋላል፤ የዚህ ምክንያቱ ደግሞ የአስተምህሮት ጉድለትና ለእምነታችን ጽኑ አለመሆን በመሆኑ መታረም ይኖርበታል ነው ያሉት።

እንደርሳቸው ማብራሪያ፤ ሰላም ካልሰፈነ ቤተሰብ አይገነባም፣ ትዳር መስርቶ ወልዶ ማሳደግ፣ ለወግ ለማዕረግ ማብቃት ያዳግታል። ኢትዮጵያውያን የምንታወቅበትን ፈጣሪን የመፍራትና የመከባበር እሴትን መመለስ ይጠበቅብናል።

ሰላም ከሌለን ተስፋ እናጣለን፣ ሞራል አይኖረንም፣ የልጆቻችን አስተዳደግ ይበላሻል፣ ለንብረቶቻችን ዋስትና እናጣለን። ንጹሃን ምንም በማያውቁት ጉዳይ በከንቱ ይሞታሉ፣ አካል ጉዳት ይደርሳል፣ በርካታ ንብረቶች ይወድማሉ። የኑሮ ውድነት ፣ የቤት እጦት ችግሮች ይባባሳሉ። በመሆኑም ሁሉም ሰው የሰላምን ዋጋ ተገንዝቦ ዋጋ መክፈል አለበት።

አላህ ሰላም ያመጣል ብለን እናስባለን። ከአላህ ቀጥሎ መንግሥት በእምነቶች መካከል፣ በብሄረሰብ መካከል፣ ከመንግሥት በተቃራኒ ከተሰለፉ ድርጅቶች ጋር በመወያየት ለሰላም መስፈን ሃላፊነቱን መወጣት ይጠበቅበታል ብለዋል።

ሁሉም እምነቶችም ስለሰላም ይሰብካሉ፣ ይናገራሉ፣ ያስተምራሉ። መንግሥትም ሰላም ሚኒስቴርን አቋቁሞ፣ መዋቅር ዘርግቶ ይሰራል። ሆኖም ከንግግር አልፎ ወደ ተግባር አልተቀየረም። የሰላም ችግር ሲፈጠር ለማርገብ ከመሯሯጥ ይልቅ ሁል ጊዜ ትኩረት መስጠት እንደሚያስፈልግም ሼክ ዛኪር ጠቁመዋል።

ሰላም ለመሆን ፈልጎ የሌላውን ሰላም መንሳት ትክክል አይሆንም። ሁሉም አማኝ ስለሰላም መኖር ይገባዋል። ችግር ሲፈጠር በውይይትና በመነጋገር መፍታትን መልመድ ይገባል።

ሰላም ለዓለም ያስፈልጋል፤ በተለይም መኖሪያ ቤታችን ለሆነችው ኢትዮጵያ ሰላም መስፈን አለበት። ችግሮችን ለመፍታት ውይይትንና ንግግርን ባህል ማድረግ፣ የችግሮችን መንስኤዎች መለየትና በቅደም ተከተል ለመፍታት ጥረት ማድረግ ይገባል። በመንግሥት የሚፈታውም በጊዜ መፈታት ይኖርበታል።

ጥያቄ ያላቸው አካላትም በሕጋዊና በሰላማዊ መንገድ መብታቸውን መጠየቅ አለባቸው። ነገር ግን በየአካባቢው ሁከትና ችግር መፍጠር ኪሳራው ለሁሉም ነው። ሰላም ሲጠፋ የመንግሥት ሠራተኛው፣ መንግሥት፣ ነጋዴውና ቤተሰብም ይቸገራል።



ሰላም ካልሰፈነ ንግድ አይካሄድም፣ ትምህርት ይዘጋል፣ መሠረተ ልማት ይወድማሉ፣ ኢኮኖሚ ይቀዛቀዛል፣ ስጋት ይሆናል፣ ጭንቀት ይተርፈናል፣ ማዕድ በጋራ ለመቁረስ ይቸግረናል ድምር ውጤቱም ለሁሉም ይተርፋል። የሰላም ዋጋው ለሆነ ህብረተሰብ፣ ቤተሰብ፣ አካባቢ ብቻ አይደለም፤ ለሁሉም በጣም አስፈላጊ ነው።

ሰላም በሌለበት ሁኔታ አማኝ እምነቱን የሚጠብቅበትን ሥርዓት ማከበር አይችልም። ንብረት ማፍራት፣ ቤተሰብ መመስረትም አይታሰብም። ስደተኛ ይበዛል። ከሶሪያ የታዘብነው ንብረት ጥሎ፣ ቤተሰብ በትኖ ሀገር ጥሎ መሰደድን ነው።

ንብረት ከጠፋ፣ ከወደመና ሀገር ከፈረሰ በኋላ የመንግሥት ህልውና መቀጠል አይችልም። ንብረት ከመውደሙ፣ የሰው ሕይወት ከመጥፋቱ፣ አካል ጉዳት ከመድረሱ አስቀድሞ እንዳይከሰት መቆጣጠር አለበት። የሃይማኖቶች ዋናው አስተምሮ ሰላም በመሆኑ የየእምነቱ አስተማሪዎች በየተቋሞቻቸው ስለ ሰላም ማስተማር እንደሚጠበቅባቸውም አመልክተዋል።



አቶ ኤፍሬም ተሰማ

# በኦሮሚያ ክልል 11 ሚሊዮን የሚጠጋ የመጻሕፍት ህትመት ተጠናቋል

## - ከስምንት ነጥብ ሶስት ሚሊዮን በላይ መጻሕፍት ተሰራጭቷል

**ሄለን ወንድምነው**

አዲስ አበባ፡- በኦሮሚያ ክልል የአዲሱን ሥርዓተ ትምህርት መሠረት ያደረገ 11 ሚሊዮን የሚጠጋ የመጻሕፍት ህትመት መጠናቀቁን የክልሉ ትምህርት ቢሮ አስታወቀ። ስምንት ሚሊዮን 379 ሺህ 452 መጻሕፍት ለተማሪዎች መሰራጨታቸው ተጠቁሟል።

ክልሉ በ2016 የትምህርት ዘመን ከ11 ነጥብ አራት ሚሊዮን በላይ ተማሪዎችን ተቀብሎ ለማስተማር አቅዷል።

በኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ በምክትል ቢሮ ኃላፊ ደረጃ የኦሮሚያ ትምህርት አማካሪ አቶ ኤፍሬም ተሰማ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት የመማሪያ መጻሕፍትን ለሁሉም ተማሪዎች ተደራሽ ለማድረግ 74 ሚሊዮን መጻሕፍት ያስፈልጋሉ።

እንደ አቶ ኤፍሬም ገለጻ፣ በ2015 የትምህርት ዘመን 27 ሚሊዮን 152 ሺህ 46 መጻሕፍትን አሳትሞ ለማሰራጨት ዕቅድ ይዞ ሲሰራ የቆየ ቢሆንም፤ ህትመታቸው የተጠናቀቀው 10 ሚሊዮን 879 ሺህ 452 የመማሪያ መጻሕፍት መሆናቸውን አስታውቀዋል።

የህትመት ሂደታቸው ከተጠናቀቁት ውስጥ ስምንት ሚሊዮን 379 ሺህ 452 መጻሕፍት ለተማሪዎች መሰራጨታቸውን ጠቁመው፤ ሁለት ነጥብ አምስት ሚሊዮን መጻሕፍትን የማጓጓዝ ሥራ እየተከናወነ ሲሆን፤ እስከ መስከረም ወር ድረስ በትምህርት ቤቶች እንደሚደርስ አስገንዝበዋል።

የቀሪ መጻሕፍቶች ህትመት እንዲጠናቀቅ በማድረግ ከስር ከስር ለተማሪዎች ተደራሽ የማድረግ ሥራ በትኩረት እንደሚሰራ ገልጸዋል።

ለመማሪያ መጻሕፍት ሕትመት ሥራ የሚያገለግሉ ግብዓት ከውጭ ሀገራት የሚገቡ መሆናቸውንና የበጀት እጥረትን እንደ ችግር ያነሱት አቶ ኤፍሬም፤ በሀገሪቱ ያሉት የማተሚያ ድርጅቶች የተማሪዎቹ ብዛት የሚጠይቀውን ያህል መጻሕፍት በሚፈለገው ጊዜ ለማሳተም አቅማቸው ውሱን ነው ብለዋል።

በተማሪዎች ቁጥር ልክ የሚያስፈልገውን መጻሕፍት አሳትሞ ማሰራጨት ጊዜ የሚወስድ በመሆኑ ተማሪዎችና መምህራን አማራጭ እንዲያገኙ ለማስቻል መጻሕፍት በሶፍት ኮፒ ተዘጋጅተው ተደራሽ መደረጋቸውን አብራርተዋል።

ክልሉ በ2016 የትምህርት ዘመን ከ11 ነጥብ አራት ሚሊዮን በላይ ተማሪዎችን ተቀብሎ ለማስተማር ማቀዱን ያስታወቁት አቶ ኤፍሬም፤ 10 ነጥብ ስድስት የሚሆኑት ነባር ተማሪዎች ሲሆኑ፤ ቀሪዎቹ በዘንድሮው ዓመት አዲስ ገቢ ተማሪዎች ናቸው ብለዋል።

የምዝገባ መርሐግብሩ ከነሀሴ 25 /2015 ዓ.ም እስከ ጷጉሜን አምስት ድረስ የሚከናወን ሲሆን፤ መደበኛው የመማር ማስተማር ሂደት በቆላማ አካባቢዎች መስከረም 7 ቀን 2016 ዓ.ም ይጀምራሉ። በሌሎች አካባቢዎች የሚገኙ ተማሪዎች ደግሞ መስከረም 14 እንደሚጀምሩ አስታውቀዋል።

የ2016 የትምህርት ዘመን የትምህርት ጥራት የሚረጋገጥበትና የላቀ ውጤት የሚመዘገብበት እንዲሆን ለማድረግ ተማሪዎች ጊዜያቸውን በአግባቡ መጠቀም፣ መምህራንና ወላጆች ተገቢውን ክትትል ማድረግ እንደሚገባቸውም አሳስበዋል።

# በሕገወጥ የመድኃኒትና የምግብ

## ምርቶች ላይ የሚደረገው ቁጥጥር ተጠናክሮ ቀጥሏል

**ቃልኪዳን አሳዬ**

አዲስ አበባ፡- በሕገወጥ የመድኃኒትና የምግብ ምርቶች ላይ የሚደረገው ቁጥጥር ተጠናክሮ መቀጠሉን የአፋር ክልልና የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር ጤና ቢሮዎች ገለጹ፡፡

የአፋር ክልል ጤና ቢሮ የሬጉላቶሪ ዳይሬክተር ወይዘሮ ሃስያ ኑር ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በ2015 በጀት ዓመት በተለያዩ የሸቀጣሸቀጥ ሱቆች ላይ ጠንካራ ፍተሻዎችን በማድረግ የአገልግሎት ጊዜያቸው ያለፈባቸው ምግቦች፣ የለስላሳ መጠጦችና ብስኩቶች እንዲወገዱ ተደርጓል።

በተለይ በሰመራ፣ በሎጊያና በሌሎች የክልሉ ከተሞች ሕገወጥ የመድኃኒትና የምግብ ቁጥጥር በማከናወን ከ400 ሺህ ብር በላይ የሚያወጡ የተለያዩ ሕገወጥ የለስላሳ መጠጦችና የታሸጉ ምግቦች እንዲወገዱ መደረጉን አስታውቀዋል።

ክልሉ ድንበር አካባቢ የሚገኝ እንደመሆኑ ሕገወጥ መድኃኒትና ምግቦች ላይ ብዙ ከፌዴራል መንግሥት ጋር በመሆን አስፈላጊው የቁጥጥር ሥራ እየተከናወነ ይገኛል ያሉት ወይዘሮ ሃስያ፤ ድንገተኛ ፍተሻዎችን በማድረግ ህብረተሰቡን ከአደጋ ለመጠበቅ ጥረት እየተደረገ መሆኑን ጠቁመዋል።

በሕገወጥ ተግባራት ላይ በተሳተፉ የንግድ ተቋማት ላይ ማስጠንቀቂያ ከመስጠት ጀምሮ እስከ እገዳ የሚደርሱ ርምጃዎች እየተወሰዱ መሆኑን ያነሱት ዳይሬክተሯ፤ የቁጥጥር ሥራውን አጠናክሮ ማስቀጠል እንደሚገባ ተናግረዋል፡፡

ክልሉ ለቁጥጥር ሥራው ከዚህ ቀደም የፌዴራል ደንብ እንደሚጠቀም ያስታወሱት ዳይሬክተሯ አሁን፤ የራሱን ደንብ አጽድቆ ሥራውን በተሻለ ሁኔታ እያከናወነ እንደሚገኝ አብራርተዋል፡፡

በድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር ጤና ቢሮ የጤናና የጤና ነክ አገልግሎት ግብዓት ዳይሬክተር አቶ



ወይዘሮ ሃስያ ኑር



አቶ ወንድሙ ተስፋዬ

ወንድሙ ተስፋዬ በበኩላቸው፤ ከተማ አስተዳደሩ በመድኃኒትና በምግብ ቁጥጥር ዘርፍ የሚያከናውነውን ተግባር በተጠናከረ መልኩ እያከናወነ መሆኑን ገልጸዋል።

በተጠናቀቀው በጀት ዓመት የምግብና መድኃኒት ቁጥጥር ደንብ ቁጥር 30/2015 በማጽደቅ በኮንትሮባንድ የሚገቡትን እንዲሁም በንግድ ሱቆች ውስጥ በሚገኙ ሕገወጥ ምርቶ ላይ ፍተሻ እየተደረገ መሆኑን አንስተዋል፡፡

በችርቻሮ መደብሮች ላይ በተደረገ ድንገተኛ ፍተሻ ሕገወጥ ምርቶችን ሲሸጡ የተገኙ አምስት የመድኃኒት መደብሮችን በማሸግ ምርቶቻቸውን መወረሱን አስታውቀዋል።

የአገልግሎት ጊዜያቸው ያለፈባቸውና በህብረተሰቡ ላይ ጉዳት የሚያደርሱ ከ410 ሺህ ብር በላይ የሚያወጡ የተለያዩ የምግብና የመጠጥ ምርቶችን በመሰብሰብ እንዲወገድ መደረጉን አመላክተዋል።

እንደ አቶ ወንድሙ ገለጻ፤ ድሬዳዋ ከተማ በአብዛኛው የወደብ ዕቃ የሚራገፍበት አካባቢ በመሆኑ፤ ይህንን ታሳቢ ያደረገ አዲስ የሕግ ማዕቀፍ በማዘጋጀት ወደተግባር ለመግባት ዝግጅት እየተደረገ ይገኛል።

አሁን ላይ ባለው አደረጃጀት ከፍትህና ከጸጥታ አካላት፣ ከገቢዎች ቢሮ እንዲሁም ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን የተለያዩ የቁጥጥር ሥራዎች እየተከናወኑ ይገኛል ብለዋል።

ከጸጥታ አካላት በሚደርስ መረጃ መሠረት በአብዛኛው ምሽት ላይ ሕገወጥ ምርቶች ይሰራጫሉ ያሉት አቶ ወንድሙ፤ ችግሩን ለመቅረፍ በማታ የሚደረጉ ድንገተኛ ፍተሻዎች ተጠናክረው ይቀጥላሉ ብለዋል፡፡

በአንጻሩ ሕግና ደንብን ተከትለው እየሰሩ ለሚገኙ ሶስት የመድሃኒት መደብሮች ዕውቅና መስጠቱን ገልጸው፤ በስራቸው ሞዴል የሆኑ ተቋማትን በመለየት በዓመት ሁለት ጊዜ የልምድ ልውውጥ እየተደረገ መሆኑን አስታውቀዋል።

# በኢትዮጵያ የወጪ ንግዱን በተሻለ መንገድ ለመምራት የሚረዳ ስትራቴጂ ያስፈልጋል

**ልጅዓለም ፍቅሬ**

አዲስ አበባ፡- በኢትዮጵያ የወጪ ንግዱን በተሻለ መንገድ ለመምራት የሚረዳ ስትራቴጂ እንደሚያስፈልግ የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር ገለጸ።

የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር አመራርና ሠራተኞች የወጪ ንግድ ልማት ስትራቴጂን አስመልክቶ ትናንት ከላኪዎች ጋር ውይይት አካሂደዋል።

በዕለቱ ንግግር ያደረጉት በንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስትር ዴኤታ አቶ ካሳሁን ጎፌ እንዳስታወቁት፤ የሀገሪቷን የወጪ ንግድ ለማሳደግ በዘርፉ ያሉ ወስንነቶችን በሳይንሳዊ መንገድ ለይቶ በመፍታት የመፍትሄ አቅጣጫዎችን ማመላከት ይገባል፡፡ የሀገሪቱ ኢኮኖሚ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ ቢመጣም የወጪ ንግዱ ደረጃ በደረጃ አለማደጉ ትክክለኛ ስትራቴጂ አለመኖሩን ያሳያል ብለዋል፡፡

ከዚህ በፊት በሀገር አቀፍ ደረጃ ግልጽ የሆነ ስትራቴጂ አለመኖሩ የወጪ ንግዱ እንዳያድግ እንቅፋት ሆኗል ያሉት ሚኒስትር ዴኤታው፤ ዘመኑን የዋጀ የኢትዮጵያ ብሔራዊ የወጪ ንግድ ልማትና ፕሮሞሽን ስትራቴጂ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱን አስረድተዋል።

ስትራቴጂው ሙሉ እንዲሆን የሚያስፈልጉ ግብዓቶች ለመጨመርና ለማስተካከል የሚረዳ መድረክ ከምርት ላኪዎች ጋር መሰናዳቱ ጠቀሜታው የጎላ ነው ሲሉ ተናግረዋል።

እንደ ሚኒስትር ዴኤታው ገለጻ፣ ሀገሪቱ ብሪክስን መቀላቀሏ የገበያ መዳረሻዎች ለማስፋት



አቶ ካሳሁን ጎፌ

ብሎም የወጪ ንግድ ለማሳደግ ከፍተኛ ሚና አለው፡፡

የወጪ ንግዱ ዘርፍ ለአጠቃላይ ሀገራዊ ምርት ዕድገት ( ጂዲፒ) ትልቅ ድርሻ ያለው ቢሆንም እያስገኘው ያለው ገቢ አነስተኛ መሆኑን የገለጹት ሚኒስትር ዴኤታው፤ ዘርፉ እንዳያድግ ማነቆ የሆኑበትን ችግሮች በጥናትና ምርምር በመለየት ከላኪዎች ጋር በጋራ እንደሚሠራ ጠቁመዋል፡፡

እንደ አቶ ካሳሁን ከሆነ፤ ሌሎች ሀገራት የወጪ ንግዳቸውን በስትራቴጂ በመደገፍ ልማታቸውን ከገበያው ጋር አቆራኝተዋል። ስትራቴጂያቸውን አዘጋጅተው ሁሉም አካል አውቀውት እንዲተገብሩ ያደረጉ ሀገራት አጠቃላይ ሀገራዊ የምርት ዕድገታቸው (የጂዲፒያቸው) 170 በመቶ በወጪ ንግድ ገቢ ያገኛሉ፡፡

ኢትዮጵያም የወጪ ንግድ ገቢዋን ለማሳደግ አቅጣጫዎችን በግልጽ የሚያመላክት የዘርፉ ስትራቴጂ ያስፈልጋታል ብለዋል። የአፍሪካ የንግድ ቀጣና በቅርቡ የሚጀመር በመሆኑ የብሔራዊ የወጪ ንግድ ልማትና ፕሮሞሽን ስትራቴጂ መተግበር አስፈላጊ ነው ሲሉ አቶ ካሳሁን ተናግረዋል።

የተዘጋጀውን ረቂቅ ስትራቴጂ ሰነድ ያቀረቡት ሔኖክ ስዩም(ዶክተር) በበኩላቸው ፤ የሀገሪቷ የወጪ ንግድ ገቢ በጅምር ላይ እንደሆነና ከፍተኛ ውስንነት ያሉበት በመሆኑ የስትራቴጂውን ሰነድ ማዘጋጀት አስፈላጊ እንዳደረገው አስረድተዋል፡፡

እንደ ዶክተር ሄኖክ ገለጻ፤ ረቂቅ ስትራቴጂው ምርትና አገልግሎቶችን ለማብዛት፣ ጥራትን ለማሳደግ፣ መዳረሻዎች ለማስፋት፣ በቂ የሰው ኃይል ለማፍራት፣ ለኢትዮጵያ ምርት ያለው አመለካከት ጥሩ እንዲሆን የማስተዋወቅና ለተሻለ ለውጥ ተቋማትን ለማቀናጀት የሚረዳ ነው ብለዋል።

ዶክተር ሄኖክ አክለውም፤ ስትራቴጂው የወጪ ንግድን ለማሳደግ በሚደረጉ ክንውኖች ላይ የንግድ የፖሊሲ ለማዘጋጀትና የወደፊት አቅጣጫ ለማስቀመጥ መሠረት የሚጥል ነው።

እያንዳንዱ ምርት ላይ ያለው የገበያ ፍላጎትና አቅርቦት ተመሳሳይ ባለመሆኑ እንዳንዱ ምርት መሠረት ያደረገ የንግድ ፍኖተ ካርታ ያስፈልጋል ያሉት ዶክተር ሄኖክ፤ በዚህ ረገድ ስትራቴጂው ውጤታማ ሥራ ለማከናወን ጠቀሜታው የጎላ መሆኑን አመላክተዋል።

ስትራቴጂው በቀጣይ ግብዓቶች ታክለውበት ለማጸደቅ ጥረት እንሚደረግ ተገልጿል።

GET AS

GET AS INTERNATIONAL PLC
ጌት አስ ኢንተርናሽናል ሐላፊነቱ የተ/የግ/ማ

SUZUKI

# በኢትዮጵያ የተፈቀደለት የሱዙኪ ወኪል አከፋፋይ



## የማሳያ ቦታዎቻችን

- ፍል ውሃ አሮጌው ቄራ
- ቦሌ ራማዳ ሆቴል
- ገርጂ አንበሳ ጋራዥ ወደ ዩኒቲ ዩኒቨርሲቲ በሚወስደው መንገድ
- አዳማ ራስ ሆቴል ግቢ ውስጥ

0930 09 85 60

## የባንክ ብድር
እናመቻቻለን

100,000 ኪ.ሜ
ወይም
3 ዓመት ዋስትና

## የጥገና ማዕከላችን

- ገርጂ አንበሳ ጋራዥ ወደ ዩኒቲ በሚወስደው መንገድ

0964 96 28 48








0930 09 85 60 - የማሳያ ቦታዎቻችን | 0964 96 28 48 - የጥገና ማዕከላችን

# ርዕሰ አንቀፅ

## የኢንዱስትሪው ልማት ቀጣይነት ማሳያ!

ኢትዮጵያ ምጣኔ ሀብቷን ከግብርና ወደ ኢንዱስትሪ ለማሸጋገር ራዕይ ሰንቃ መስራት ከጀመረች ዓመታት ተቆጥረዋል፤ ለእዚህም ለኢንዱስትሪው ዘርፍ የሚያስፈልጉ መደላድሎችን በማዘጋጀት እየሰራች ትገኛለች። በኢንዱስትሪው ዘርፍ የተያዘውን ራእይ ለማሳካት ደንቃራ ሆኖ የቆየውን የመሬት፣ የመሰረተ ልማትና የመሳሰሉት ችግሮች ለመፍታት የሚያስችል ተግባር ሲከናወን ቆይቷል።

በእዚህም የውጭም ሆኑ የሀገር ውስጥ ባለሀብቶች በአምራች ኢንዱስትሪው ዘርፍ መሰማራት ሲፈልጉ ማሽነሪዎቻቸውን ብቻ አምጥተውና ገጣጥመው፣ ሰራተኞችን አሰልጥነው በማሰማራት ወደ ስራ መግባት የሚያስችሏቸው 13 የኢንዱስትሪ ፓርኮች ተገንብተዋል። ፓርኮቹ የመንገድ፣ የኤሌክትሪክ፣ የውሃ፣ የቴሌኮምና የመሳሰሉት መሰረተ ልማቶች የተሟሉላቸው ግዙፍ ሼዶችን ያካተቱ በመሆናቸውም በእርግጥም የባለሀብቶችን የዘመናት ጥያቄ የሚመልሱ፣ የሀገሪቱንም የኢንዱስትሪ ልማት ጉዞ የሚያሳልጡ ናቸው። እንደ ሀዋሳ ኢንዱስትሪ ፓርክ ባሉት ፓርኮች እየታየ ያለውም ይሄው ነው።

መንግስት የኢንዱስትሪ ፓርኮችን ብቻውን መገንባት እንደሌለበትም ያምናል፤ የግሉ ዘርፍም የኢንዱስትሪ ፓርኮችን ገንብቶ ለባለሀብቶች ምቹ ሁኔታዎችን እንዲፈጥር ሠርቷል፤ በዱከም ተገንብቶ በርካታ አምራቾችን እያገለገለ የሚገኘው የቻይናው ኢስተርን ኢንዱስትሪ ፓርክም ከዚህ አኳያ የሚጠቀስ ነው።

የኢንዱስትሪ ፓርኮች የውጭ ምንዛሬ ለማስገኘት ታልመው የተገነቡ እንደመሆናቸው ምርቶቻቸው ለውጭ ገበያ እየቀረበ ይገኛል። በርካታ ዓለም-አቀፍ ብራንድ ያላቸው ኩባንያዎች በእነዚህ ፓርኮች ገብተው እየሰሩ ምርቶቻቸውን ለውጭ ገበያ እያቀረቡ ይገኛሉ። ፓርኮቹ ለብዙ ሺህ ኢትዮጵያውያንም የሥራ ዕድል መፍጠር ችለዋል።

የቴክኖሎጂ እና የእውቀት ማሸጋገሪያ ድልድይ በመሆን እያገለገሉም ናቸው። የነገ የተዘጋጁ አልባሳት አምራቾች በፓርኮቹ እየተፈጠሩ ናቸው። ሀገሪቱ በውጭ ምንዛሬ ግኝት፣ በሼዶች ኪራይና በሚሰጡ የተለያዩ አገልግሎቶች ተጠቃሚ እየሆነችም ትገኛለች። በቴክኖሎጂና የዕውቀት ሽግግር፣ በግብአት አቅርቦት ትስስር፣ የገቢ ምርቶችን በመተካት በኩልም ተጠቃሚ እየሆነች ትገኛለች።

የሀገሪቱ የኢንዱስትሪ ራዕይ በ13 የኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት በሚከናወን እንዲሁም እስከ አሁን ባለው የግሉ ዘርፍ ጥረት ብቻ ከግቡ የሚደርስ አይደለም። እነዚህ ፓርኮች በቀጣይ ሀገሪቱ ለሚያስፈልጓት አያሌ የኢንዱስትሪ ፓርኮች ማሳያዎችና እርሾዎች ናቸው። ሌሎች በርካታ የኢንዱስትሪ ፓርኮች ያስፈልጋሉ።

ከግብርና ወደ ኢንዱስትሪ የሚደረግ ጉዞ በየጊዜው የኢንዱስትሪ መሰረተ ልማቶችን መገንባትን ይጠይቃል። የኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን በመጪዎቹ ዓመታት ከ100 በላይ የኢንዱስትሪ ፓርኮችን ለመገንባት ማቀዱ ከዚህ አኳያ ሲታይ የኢንዱስትሪ ፓርክ የማልማቱ ስራ ተጠናክሮ መቀጠሉን ያመለክታል።

ሀገሪቱ ሥራ ላይ ባሉት ፓርኮች ብዙ ተሞክሮ የቀሰመች እንደመሆኑ እነዚህን ፓርኮች የመገንባቱ ስራ እንደ ውጭ ምንዛሬ እጥረት ያሉ ፈተናዎች ካልገጠሙ በስተቀር ብዙም ፈታኝ ይሆናል ተብሎ አይታሰብም። ዋናው ነገር ቀጣዩን የኢንዱስትሪ ዘመን ታሳቢ በማድረግ ለኢንዱስትሪ ፓርኮች ግንባታ ትኩረት መስጠቱ ነው።

ሀገሪቱ በሰሜን ኢትዮጵያ ከገጠማት ጦርነት፣ ከኮቪድ ወረርሽኝ፣ ከዓለም አቀፍ ጫና ጋር በተያያዘ ስራ ላይ ያሉት የኢንዱስትሪ ፓርኮች ፈተና እንደገጠማቸው ይታወቃል። ይህ ፈተና ግን የኢንዱስትሪ ልማቱን አንገጫግጮታል እንጂ፣ ቀጣይነቱን አላቆመውም። መንግስትና ባለሀብቶች እያደረጉ ያሉትን ጥረት ተከትሎ ከዚህ ፈተና እየተወጣ ነው፤ የሰሜን ኢትዮጵያው ጦርነት በስምምነት መቋጨቱ፣ በኢትዮጵያ ታምርት ንቅናቄና በመሳሰሉት የኢንዱስትሪው ዘርፍ እንዲነቃቃ እየተደረገ ያለው ርብርብና እየታየ ያለው ለውጥ የኢንዱስትሪው ዘርፍ በጥሩ መሰረት ላይ መቆሙን ያመለክታል። በፈተና ውስጥ በዘርፉ እየታየ ያለው ለውጥ ዘርፉ በቀጣይም ተጠናክሮ እንደሚቀጥል ያስገነዝባል።

ለኢንዱስትሪው በተጣለው መሰረት ላይ የሚደረገው የኢንዱስትሪ መሰረተ ልማት ግንባታ መጠናከር ይኖርበታል። ይህ እንዲሆን የሚያስገድዱ ሁኔታዎች በርካታ ናቸው።

በሀገሪቱ ባለሀብቶች ትኩረት ሳይሰጠው የቆየው የአምራች ኢንዱስትሪው ዘርፍ አሁን ትኩረት እያገኘ ነው፤ አንዱ አንዱን እያየ ወደ ዘርፉ እየተሳበ ይገኛል። አዳዲስ በአምራች ኢንዱስትሪው ዘርፍ ሊሰማሩ የሚችሉ ባለሀብቶች እየተፈጠሩ ናቸው። በቀጣይም ይሄ በሰፊው ይፈጸማል።

ኢትዮጵያ በዓለም አቀፍ ደረጃ ያላት ስፍራ እየጨመረ መምጣት፣ በተለይ ሰሞኑን በብሪክስ የተሰጣት ትልቅ ስፍራ የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት ፍሰቱ እንዲጨምር ሊያደርግ እንደሚችል ከወዲሁ እየተተነበየ ነው። ይህ ሁሉ በኢንዱስትሪ መሰረተ ልማት ግንባታ ላይ ከወዲሁ ዝግጅት ማድረግና መሥራትን ይጠይቃል።

ሀገሪቱ ምጣኔ ሀብቷን ከግብርና ወደ ኢንዱስትሪ ለማሸጋገር የምትሰራ እንደመሆኗ አቅም ካልፈተነ በቀር ሁሉም መሰረተ ልማት የተሟላላቸው፣ ባለሀብቶች ማሽነሪዎቻቸውን አስመጥተው በመገጣጠም ሰራተኞችን አሰልጥነው በማሰማራት በቀጥታ ወደ ማምረት የሚገቡበትን ሁኔታ አሟልተው የያዙ የኢንዱስትሪ ፓርኮችን ገንብቶ መጠበቅ ያስፈልጋል። የኮርፖሬሽኑ ዕቅድ ከዚህ አኳያ ሲታይ ተገቢና አስቀድሞ የታየ ሊባል የሚችል የኢንዱስትሪው ልማት ቀጣይነት ማሳያ ነው!


## አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፡- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## እንዴት ነጻ እንውጣ?

**ምሕረት ሞገስ**

ልማድ ተንቆ ሊተው የሚችል ተራ ጉዳይ አይደለም። ክፉም ሆነ ደግ ልማድ የሚቆሙት በብዙ ድካም ነው። ምክንያቱም ልማዶች ሱሰኛ የመሆን ውጤትን ያስከትላሉ። አልኮል የመጠጣት ልማድ፣ ጫት የመቃም ልማድ ወይም ሲጋራ የማጨስ ልማድ ሕክምና ተወስዶ በብዙ ድካም መወገድ የሚችሉ ናቸው። ክፉ ልማዶችን በተለይም ብዙዎችን ሊጎዱ የሚችሉ ልማዶችን በጊዜ ማቆም ያስፈልጋል።

ልክ እንደክፉ ሁሉ በተቃራኒው በበጎ ሊገለፁ የሚችሉ ሰው የማክበር፣ የማንበብ፣ ወደ ማምለኪያ ስፍራ ወይም ወደ ገበያ የመሔድ፣ የታመመ እና የታሠረ ሰውን የመጠየቅ ልማዶችም አሉ። እነዚህ ልማዶች መጥፎ ናቸው ማለት ባይቻልም፤ እንዲቆሙ ከተፈለገ እነኚዎቹም በቀላሉ የሚቆሙ አይደሉም። ምክንያቱም ልማዶች ሁሉ በውል ሳይታወቁ በፍጥነት ወደ ሱስነት ያመራሉ።

በሌላ በኩል በግለሰብ ደረጃ ብቻ ሳይሆን በቡድን ወይም በማህበረሰብ ደረጃ የሚፀናወቱ ልማዶች አሉ። ለምሳሌ የሰዎች ሞትን ያለመቀበል ልማድ፣ ሃዘንን የማብዛት ልማድ፣ የጦርነት ልማድ፣ ጊዜን የማባከን ልማድ፣ ሰዎች ያለማዳመጥ ልማድ፣ የስግብግብነት ልማድ ... ወዘተ እያልን ብዙ ልማዶችን መግለፅ እንችላለን።

በእርግጥ የማህበረሰብም ሆኑ የግለሰብ ልማዶች ጠቃሚ ከሆኑ ቢቀጥሉ እና ቢያብቡ መልካም ነው። በተቃራኒው ግን የግለሰብ ብቻ ሳይሆን የማህበረሰብ ልማድ መስለው የሚታዩ ብዙዎችን በመጉዳት ላይ ያሉ ልማዶች ደግሞ በጊዜ መክሰም አለባቸው። ለምሳሌ ሙት አንጋሽ እና ሙት ወቃሽ የመሆን ልማድ በፍጥነት መቆም ያለባቸው ልማዶቻችን ናቸው።

ከተራ የግለሰብ ሞት የቀብር ሥነሥርዓት ላይ ከሚነበብ የሕይወት ታሪክ ጀምሮ የሞተን ማወደስ የተለመደ ነው። የሞተ ተወደሰ አልተወደሰ ምን ልዩነት አለው? ቢያንስ ሲኖር የተወቀሰ ሲሞት ይወደስ ሊባል ይችላል። ነገር ግን ይህ ልማድ በሕይወት እያለ ሰዎችን ሲያሰቃይ እና ሲገድል የነበረ ሰው ታዝኖለት ብቻ ሳይሆን ልማድ ሆኖ ውዳሴ መፃፉ ፍፁም ተገቢነት የጎደለው ነው። ይህ እየዳበረ ሲቀጥል፤ ውሸትን መፃፍ እንደትክክለኛ ተግባር ይወሰዳል። አሁንም ይህንኑ እየታዘብን ነው።

በተቃራኒው በጎ ነገር ሲሰራ የነበረ ሰው ወይም መጥፎ ነገር ሲሰራ የነበረ ሰው ይሞታል። ‹‹የሞተ አንበሳ ሣር ይበቅልበታል›› እንደሚባለው አንዳንድ ግለሰቦች ልማድ ሆኖባቸው ዘላለማቸውን፤ ገንዘባቸውን ጊዜያቸውን ሙሉ ሕይወታቸውን የሚሳልፉት የሞተውን ሰው በመውቀስ እና የአሁኑ ሕይወታቸው በዛ ሰው ምክንያት የተበላሸ መሆኑን በመግለፅ ነው። ዛሬ ላይ ቆመው ዛሬን እና ነገን የተሻለ የሚያደርጉ ሃሳቦችን ከማመንጨት እና ያንንም ከማስተላለፍ ይልቅ ጥላቻን በመዝራት ጊዜያቸውን ያባክናሉ።

አንዳንዶች ደግሞ በሁሉም ነገር ላይ እነርሱ ብቻ አዋቂ እንደሆኑ የሚያስቡ ነገር ግን አላዋቂነት የፀናባቸው ሰዎች አሉ። በሁሉም ነገር ላይ እኔ አዋቂ ነኝ ብለው ይከራከራሉ። ለዚህ ሁለት በግንባታ ሥራ ላይ ተሠማርተው ሥራቸውን ሲያከናውኑ የነበሩ ሰዎች ጥሩ ማሳያ ይሆናሉ። ሰዎቹ ሥራቸውን ሲሰሩ በአብዛኛው መከራከር ልማዳቸው ነው። ክርክራቸው ከስራቸው ያለፈ ሊሆን ይችላል። የዕለቱ ክርክራቸው ለገሃር የሚባለው ሰፈር አሰያየም ላይ ያተኮረ ነበር። በጣም የሚያስገርመው ጉዳዩ ለጭቅጭቅ የሚያደርሳቸው መሆን ባይኖርበትም መጨቃጨቅ ላይ ደረሱ።

አንደኛው የመከራከር ልማድ ተጠቂ፤ አንዱን የኢትዮጵያ ብሔር ቋንቋ ጠቅሶ ለገሃር የሚለው ቃል የመጣው ከዚህ ነው አለ። ሌላኛው ተከራካሪ ለገሃር አካባቢ ተወልዶ ያደገ ሲሆን፤ ቃሉ መነሻው ፈረንሳይኛ መሆኑን አስታውሶ ከነትርጉሙ አስረዳ። ነገር ግን ተከራካሪው ለማዳመጥ ዝግጁ አልነበረም። ቢያንስ ተደማምጠው መረዳዳት ባይችሉ እንኳን፤ የአካባቢውን ስያሜ አመጣጥ ለታሪክ ትተው በዕለቱ ሥራቸው ላይ ሃሳብ ከመለዋወጥ ይልቅ በማያዋጣ እና ጥቅም በሌለው ጉዳይ ላይ ሲጨቃጨቁ፤ ቀናቸውን ብቻ ሳይሆን ግንኙነታቸው ላይ ጠባሳ የሚጥል ተግባር ፈፀሙ። ዱላ እስከመማዘዝ ደርሰው ለገላጋይ አስቸገሩ።

ከላይ የተጠቀሱ ሁሉን እናውቃለን ባይ ተከራካሪዎች በልማዳቸው ምክንያት ለዱላ ሲጋበዙ፤ እርስ በእርስ ቢጎዳዱም ጉዳታቸው ጎልቶ ሌሎች ላይ አልታየም። ነገር ግን የአንዳንዶች ልማድ ግን ጉዳቱ ከአንድ ግለሰብ አልፎ ብዙዎች ላይ ያርፋል። ጎሳን፣ ሃይማኖትን፣ ፆታን ወይም አንድ ቡድንን (መደብን) መነሻ በማድረግ መሳብ እና የመሳሳብ ልማድ ከሆነ አደገኛ ነው። እንደዚህ ዓይነት አደገኛ አዝማሚያዎች ደግሞ በጊዜ ካልቆሙ መጨረሻ ላይ የሚያስከትሉት ጉዳት ከባድ እና ብዙ ዋጋ የሚያስከፍሉ ይሆናሉ። ጉዳታቸውም ከአንድ ግለሰብ አልፈው ብዙዎች ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ያሳድራሉ።

በዚህ ጊዜ ዓለም አቀፍ ዕውነታን ካለመ ለማመድ የተነሳ ዓለም እንዲህ ወደ አንድ መንደርነት እየተቀየረችበት ባለ ዘመን በተራ አንድ ቡድን ውስጥ ታጥሮ መባከን ክፉ ልምድ ነው። አሁን አሁን ደግሞ ይህ ክፉ ልማድ እንደ ዕውቀት እየተወሰደ መጓተቱ፤ የኋልዮሽ ለመሳሳብ መሞከሩ ያሳፍራል። በእርግጥ መስራት መልካም ነው። መማርም በጎ ነው። መስራት እና መማር ተዳምሮ ሥልጣን ሲያዝ አስተማማኝ እኩልነት እንዲሰፍን ማድረግ ሲገባ፤ በተቃራኒው ወደ ኋላ መመለስ ጊዜ ሲያልፍ ትውልድን ብዙ ዋጋ ያስከፍላል።

በእርግጥ ማንም ሊክደው በማይችል መልኩ በዓለም ላይ ሙሉ ለሙሉ እኩልነት ሰፍኗል ማለት አይቻልም። እያንዳንዱ አገር፣ እያንዳንዱ ከተማ፣ እያንዳንዱ ወረዳ፣ እያንዳንዱ ሆስፒታል፣ እያንዳንዱ ዩኒቨርሲቲ፣ እያንዳንዱ ተቋም በዓለም ላይ ከመምራት ጋር የተያያዙ ቦታዎች በሙሉ በጣት ከሚቆጠሩ ሴቶች በስተቀር ከ99 በመቶ በላይ የሚመሩት በወንዶች ነው። ምክንያቱም ተወደደም ተጠላ፤ በግልፅም ሆነ በስውር ዓለም ላይ ትልቅ ክፉ ልማድ አለ። ይኸውም መምራት የሚችለው እና መምራት ያለበት ወንድ ብቻ ነው የሚል ልማድ አለ። ይህንን ተከትሎ ከሴቶች ይልቅ ብዙ ገንዘብ፣ ብዙ የዓለም ሃብት በወንዶች እጅ ነው።

በሌላ በኩል ዓለምን መምራት ያለባት አሜሪካን ብቻ እንደሆነች የማሰብ ብቻ ሳይሆን የማመን ዝንባሌዎች አሉ። ቻይናም ሆነች ሩሲያ ወይም የትኛውም አገር በቴክኖሎጂም ሆነ በተለየ የሃብት መጠን በፍፁም ዓለምን መቆጣጠር አይችልም የሚል ልማድ ይስተዋላል። ይህ ብቻ አይደለም በሃይማኖት በኩልም በተመሳሳይ መልኩ የማይገቡ ልማዶች አሉ።

በዓለም ላይ ያሉ ልማዶች ተለይተው ሲስተዋሉ ፆታ፣ ሃይማኖት ወይም የቆዳ ቀለም ላይ የተመረኮዙትን እንደመነሻ ስንጠቅስ፤ ጉዳታቸው ከፍተኛ በመሆኑ መወገድ አለባቸው።

በዚህ ላይ ዓለምን ከእነዚህ ልማዶች ለማላቀቅ ቢከብድም፤ ቢያንስ ከራስ ቤተሰብ፣ ከራስ ተቋም፣ ከራስ አገር በመጀመር ክፉ ልማዶችን ለማስቆም የሚጠበቅብንን ሚና በመጫወት እራሳችንን ነጻ እናውጣ። ሰላም!

ዜና

# በሕገወጥ የወርቅ አምራቾችና ነጋዴዎች ላይ ርምጃ ተወሰደ

**ጽጌረዳ ጫንያለው**

አዲስ አበባ፡- በሕገወጥ ወርቅ ፍለጋና የግብይት ሥራ ላይ በተሰማሩ ከ18 በላይ ማህበራት ላይ እና በ37 አዟሪዎች ላይ የተለያዩ ርምጃዎችን መውሰዱን የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል አስታወቀ፡፡

የክልሉ ማዕድንና ኢነርጂ ልማት ኤጀንሲ ዋና ዳይሬክተር አቶ ገብረማርያም ሰጠኝ ከኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ጋር በነበራቸው ቆይታ እንደተናገሩት፤ በክልሉ ለብሔራዊ ባንክ የሚያቀርበው የወርቅ ምርት ከእስከዛሬው አንጻር አፈጻጸሙ ዝቅተኛ ነው፡፡ ስለዚህም ክልሉ ቀጣዩም ጊዜ በዚህ አይነት ሁኔታ እንዳይጓዝ ለማድረግ የተለያዩ ርምጃዎችን ወስዷል፡፡

በክልሉ ርዕሰ መስተዳድር የሚመራ ግብረኃይል ተቋቁሞ በሕገወጦች ላይ የተለያዩ ርምጃዎች እየተወሰዱ ነው ያሉት አቶ ገብረማርያም፤ ይህም ካለፈው መጋቢት ወር ጀምሮ ወደ ሥራ የተገባበት ነው ብለዋል፡፡

«በግብረ ኃይሉ ውሳኔ መሠረት በወርቅ ማዕድን ፍለጋና ልማት የተሰማሩ ማኅበራት ለብሔራዊ ባንክ ከአንድ ኪሎ ግራም በታች ወርቅ ማቅረብ አይችሉም» የሚል መመሪያ እንደተሰጠ የጠቆሙት ዳሬክተሩ፤ ይህንን ማሟላት ባልቻሉና የቁፋሮ ቦታ ተሰጥቷቸው ወደ ልማት ያልገቡ እንዲሁም የማይሆን ቦታ ተሰጥቷቸው ቅያሬ ወስደው ሥራ ባልጀመሩ ከ20 በላይ ከሆኑ ማህበራት መካከል ከ18 በላይ የሆኑት እንዳይሰሩ እገዳ ተጥሎባቸዋል፡፡ ይህም ፈቃድ አግኝተው አሁን ላይ የሚሰሩት ሁለቱ ብቻ መሆናቸውን ተናግረዋል፡፡

በማህበራቱ ላይ የተወሰደው ውሳኔ ቅሬታ እየቀረበበት ቢሆንም ግብረኃይሉ መርምሮ ውሳኔ የሚያስተላልፍ እንደሚሆን የሚያነሱት ዋና ዳይሬክተሩ፤ ርምጃው በማህበራቱ ብቻ የተወሰነ አይደለም ብለዋል፡፡

በፌዴራል ደረጃ «ፒኤል ሲ» ተብለው ፈቃድ ከተሰጣቸው ከ44 አዟሪዎች መካከልም 21 የሚሆኑት የንግድ ፈቃዳቸው መወሰዱንና በ16ቱ ላይ ደግሞ የማስጠንቀቂያ ርምጃ መወሰዱን ጠቅሰዋል፡፡

ችግሩን ከመሠረቱ ለመፍታትም በዘርፉ የተሰማሩትን አካላት የማብቃትና ግንዛቤ የማስጨበጥ ተግባር እየተከናወነ እንደሆነ የገለጹት አቶ ገብረማርያም፤ ሕገ ወጥነትን በመከላከል ዙሪያ በተሠራው ተግባር ለውጦች መታየታቸውን ጠቅሰው፤ ሥራው ከመሰራቱ በፊት ማለትም ከጥር እስከ መጋቢት ባሉት ሦስት ወራት ወደ ብሔራዊ ባንክ የገባው የወርቅ መጠን ሦስት ኪሎ ግራም ብቻ እንደነበር አስታውሰዋል፡፡

ግብረ ኃይል ተቋቁሞ ወደ ሥራ ከተገባ በኋላ ነገሮች ተቀይረው በጥቂት የወርቅ አቅራቢዎች ከሚያዝያ እስከ ሰኔ መጨረሻ ድረስ 21 ኪሎ ግራም ወርቅ ወደ ብሔራዊ ባንክ ማስገባት ተችሏል ብለዋል፡፡

ቀደም ባሉት ጊዜያት ከአካባቢው የሚገኘው የወርቅ መጠን እስከ 800 ኪሎ ግራም የሚደርስ ሲሆን፤ የዘንድሮው አፈጻጸም ግን በተለያዩ ምክንያቶች በጣም ዝቅ ማለቱንም ጠቁመዋል፡፡

የክልሉ እቅድ በ2015 በጀት ዓመት ለብሔራዊ ባንክ 450 ኪሎ ግራም ወርቅ ማቅረብ ሲሆን፤ ማቅረብ ግን የቻለው 67 ኪሎ ግራም ብቻ ነው፡፡ ይህም በመቶኛ ሲሰላ 14 ነጥብ 8 በመቶ ነው፡፡

በመሆኑም ክልሉ ችግሮች ናቸው ብሎ የለያቸውን የጸጥታ፤ የሕገወጥነት መስፋፋትና የመሠረተ ልማት ችግሮች ላይ ከፌዴራል መንግሥት ጋር በመነጋገር መፍትሄ ለመስጠት ቁርጠኛ መሆኑን አቶ ገብረማርያም አስረድተዋል፡፡



# በዞኑ የተፈጠረውን አንጻራዊ ሰላም ለማጽናት እየተሠራ ነው

**ማህሌት ብዙነህ**

አዲስ አበባ፡- በአማራ ክልል ደቡብ ወሎ ዞን ከነበረው የጸጥታ መደፍረስ በኋላ የተፈጠረውን አንጻራዊ ሰላም ለማጽናት እየተሠራ መሆኑን የዞኑ አስተዳደር አስታወቀ።

የደቡብ ወሎ ዞን ዋና አስተዳዳሪ አቶ አሊ መኮንን ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በክልሉ ከተከሰተው የጸጥታ ችግር አኳያ በዞኑም የተወሰኑ ወረዳዎች ከፊል ችግሮች የነበሩ ቢሆንም አሁን ላይ አንጻራዊ ሰላም ተፈጥሯል።

በተለይም በዞኑ ወግዲ ወረዳ መካነሰላም ቦረና ፣አማራ ሳይንት እና መሀል ሳይንት ፣ጃማ ደጎሎ፣ለጋምቦ አቀስታ የሚባሉት አካባቢዎች ውስጥ በከፊል የጸጥታ መደፍረስ እንደነበር ጠቁመው፤ የሀገር መከላከያ ሠራዊት በአካባቢው በመግባት አሁን ላይ ምንም አይነት የጸጥታ ችግር የሌለበት ሰላማዊ ሁኔታ ላይ መሆኑን አብራርተዋል።

የተለያዩ የመንግሥት መዋቅሮች ከአካባቢው የጸጥታ መዋቅር ጋር በጋራ ወደ ሥራ ገብቶ እየተሰራ መሆኑንም ተናግረዋል።

ይሁን እንጂ አሁንም በደላንታ ወገልጤና ወረዳ መጠነኛ ችግር ያለበት አካባቢ ሲሆን በዚህ ወረዳም ሰላማዊ እንቅስቃሴን ለመፍጠር የክልሉ እና የአካባቢው የጸጥታ መዋቅር እንዲሁም መከላከያ ሠራዊት በጋራ እየተሠራ እንደሚገኝም አስተዳደሩ አስታውቀዋል።

ሰላም የሚረጋገጠው በወታደራዊ ኃይል ብቻ ሳይሆን ህብረተሰቡ ለሰላም በሚሰጠው ከፍተኛ ዋጋ ነው ያሉት አስተዳደሩ፤ ይህንን ለማሳካትና የበለጠ ሰላምን ለማጽናት በየደረጃው ካለው መዋቅር ብሎም ከህዝቡ ጋር ውይይት እየተደረገ ነው ብለዋል።

እንዲሁም ታጥቆ እየተንቀሳቀሰ እና ሰላም እያደፈሰረ ያለውን ኃልም በየአካባቢው የሀገር ሽማግሌዎችና የኃይማኖት አባቶች እየተወያዩ ችግሩን በሰላማዊ መንገድ ለመፍታት ጥረት እየተደረገ ነው ብለዋል።

አቶ አሊ እንደገለጹት፤ በአካባቢው መለስተኛ ችግሮች ሲያጋጥሙ ሊከላከል የሚችል አቅም ያለው የአካባቢው የጸጥታ መዋቅርን በመፍጠር ውይይቶች፣ ግምገማዎችና የማጥራት ሥራዎች እየተሰሩ ነው። ይህ ተደምሮ የአካባቢዎች ሰላም ዘላቂነት እንዲኖረውና ህዝቡ እና የአካባቢው የጸጥታ መዋቅር በጋራ ሰላምን ለማዝለቅ የሚገባውን ሚና ለመጫወት እየተሰራ ነው።

በዚህም ሙሉ በሙሉ በራስ አቅም በአካባቢ አመራር እና የጸጥታ ሃይል እንዲሁም ህዝቡን ባሳተፈ መንገድ የበለጠ ሰላምን ለማረጋገጥ አመራር ተመድቦ ከመከላከያ ሠራዊት ጋርም የውይይት መድረኮች እየተካሄደ ዘላቂነቱን ለማጋገጥ እየተሠራ ነው ብለዋል።

የነበረው የጸጥታ መደፍረስ አርሶ አደሩን የማዳበሪያ አቅርቦት እንዳይደርስና የዝናብ ወቅትን ያስተጓጎለ፣ የንግድ እንቅስቃሴን ያስተጓጎለ ፣ኑሮ ውድነቱ እንዲባባስ እንዲሁም የምርት እንቅስቃሴ እንዳይኖር ያደረገ ቢሆንም በሰው ላይ ምንም አይነት ጉዳት እንዳልደረሰ አስታውቀዋል።

በንብረት ላይ የተወሰነ ደረጃ በመካነሰላም አካባቢ የማረሚያ ቤት ንብረትና እስረኛ እንዲለቀቅ ተደርጓል። እንዲሁም በአቀስታ ወረዳ የመንግሥት ተቋማን ለመዝረፍ ሙከራ ተደርጓል። ከዚያ ውጭ የአካባቢው ማህበረሰብ ባደረገው ጥረትና ጥንቃቄ ምንም አይነት የንብረት ጉዳት አልደረሰም ሲሉ አስታውቀዋል።

በተጨማሪም ከተቋቋመው ምስራቅ አማራ ክልል ኮማንድ ፖስት በተጨማሪም ንዑስ ኮማድ ፖስት የተዋቀረ ሲሆን ይህም የአካባቢው ሰላም እንዲረጋገጥ በማድረግ ትልቅ ፈይዳ አለው ብለዋል።

ለዚህም በዞኑ በሚገኙ ሁሉም ወረዳዎች የኮማንድ ፖስት በማዋቀር ክልከላና የሰአት እላፊ እንዲኖር ከማድረግ ባለፈ የእርምት ርምጃ እና ማህበረሰቡ ስለአማራ ክልል አሁናዊ ሁኔታ የተሻለ ግንዛቤ እንዲኖረው የውይይት መድረክና የተሀድሶ ማእከላትን በማዘጋጀት እየተሠራ ነው ሲሉም ገልጸዋል።

በቀጣይ በክልሉ ብሎም በዞኑ ሰላማዊ ሁኔታዎችን ለመፍጠር ሁሉም ማህበረሰብ የራሱን ድርሻ ማበርከት አለበት ብለዋል።

# የዓድዋ ሙዚየም...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

ስድስት ቢሊዮን ብር ወጪ የተደረገበት ሲሆን የግንባታው ሂደት 87 በመቶ ተጠናቋል፡፡ ፕሮጀክቱን በታሰበለት ጊዜ ሙሉ ለሙሉ ለማጠናቀቅ አስፈላጊው ግብዓት ቀርቦ በመሰራት ላይ ነው ብለዋል፡፡

ሙዚየሙ በውስጡ በርካታ ክፍሎች ያሉት መሆኑን የጠቀሱት አቶ ዳዊት፤ ከነዚህ መካከል በዓድዋ ጦርነት የተሰዉ ጀግኖችን የሚዘክር ሙዚየም፣ የመዝናኛ ሥራዎች፣ ካፍቴሪያዎች፣ ሲኒማ ቤቶችና ሁለገብ አዳራሾች እንደሚገኙበት ጠቅሰዋል፡፡ ታሪክ ቀጣይነት እንዲኖረው ከማድረግ በኩል ያለው ፋይዳ የጎላ መሆኑንም ዳይሬክተሩ ተናግረዋል፡፡

ፕሮጀክቱ ከከተት አዋጁ እስከ ዓድዋ ድል ያለውን ሁነት ማሳየት በሚያስችል መልኩ መሠራቱን በመጥቀስ ከተለያዩ የሀገሪቱ ክፍል ተነስተው በጦርነቱ የተሳተፉ ጀግኖች መታሰቢያ በሮች እንዳሉትም ገልጸዋል፡፡

በሙዚየሙ ቀደም ሲል የነበሩ ኢትዮጵያውያን ጀግንነት የሚንጸባረቅበት መሆኑን የገለጹት አቶ ዳዊት የአሁኑ ትውልድ ለልማት ያለውን ጀግንነት ለማሳየት የሚያስችልም ነው ብለዋል፡፡

ከመነሻው እስከ ድሉ ቦታ ያለውን አድካሚ ጉዞ ለማሳየት የሚያስችሉ ደረጃዎች በሙዚየሙ መካተታቸውን ጠቅሰው በተለይም ሙዚየሙ የዓድዋን አካባቢ እንዲመስል የዓድዋ ተራሮች በግድግዳ ላይ መሳላቸውን አስረድተዋል፡፡

ሙዚየሙ በጦርነቱ የነበረው የሴቶች ተሳትፎ ይበልጥ ጎልቶ እንዲወጣ በሚያስችል መልኩ መሠራታቸውን ጠቅሰው የከተማ አስተዳደሩ ምክር ቤት ቢሮና የስብሰባ አዳራሽን ጨምሮ የተለያዩ የምርምር መሥሪያ ቦታዎችና ላይብረሪዎች ተሰርተዋል ብለዋል፡፡

ሙዚየሙ የአውቶቡስ ተርሚናል ጭምር ያለው መሆኑን የጠቀሱት አቶ ዳዊት፤ ይህም በፒያሳ የሚታየውን የታክሲና አውቶብስ መጨናነቅ ማስቀረት የሚያስችል እንደሆነ አብራርተዋል፡፡

ፕሮጀክቱ የትራፊክ መጨናነቅን በመቀነስ ዜጎች ታክሲን በተርሚናሉ አማካኝነት እንዲጠቀሙ የሚያስችል መሆኑንም አቶ ዳዊት ተናግረዋል፡፡

# በድሬዳዋ አስተዳደር ...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

የድኅማ ፍጆታ ዕቃዎች ስኳርና የምግብ ፓልም ዘይት በተጨማሪ ከ59 ዓይነቶች የግብርና እና የኢንዱስትሪ ምርቶች በድሬ ሁለ-ገብ የገበሬዎችና የከተማ ዩንየኖች በሸማቾች ህብረት ሥራ ማህበራቶች እና በአስተዳደሩ አስመጪዎች አማካኝነት ለህብረተሰቡ ቀርቧል ሲሉም አስረድተዋል።

አቶ አሚኑ እንደገለጹት፤ የሌማት ትሩፋትን እንደምቹ አጋጣሚ በመጠቀም የከተማ ግብርና ላይ የተሰማሩ ኢንተርፕራይዞች የዶሮና የእንቁላል ምርቶችን በቅዳሜና እሁድ ገበያ ላይ እንዲያቀርቡ እየተደረገ ይገኛል።

አነስተኛ ገቢ ላይ የሚገኙ 9ሺህ 500 የመንግሥት ሠራተኞች በመሠረታዊ የፍጆታ ምርቶች ተደራሽ ለማድረግ፤ ለያንዳንዳቸው በየወሩ አስቤዛ በተመጣጣኝ ዋጋ እንዲያገኙ እየተደረገ ይገኛል ብለዋል።

ከዚህም ባሻገር በበጀት ዓመቱ የወጪ ምርቶችን መዳረሻ በማስፋትና የቀጣናዊ ትስስርን በማጠናከር ላይ ሥራዎች መሠራታቸውን ጠቁመው፤ በዚህም በከተማ አስተዳደሩ ከወጪ ንግድ 165 ነጥብ 5 ሚሊዮን ዶላር ገቢ ማግኘት ተችሏል ብለዋል።

እንደ ኃላፊው ንግግር ገለጻ፤ በበጀት ዓመቱ ትስስሩን ለማጎልበት ወደ ጎረቤት ሀገራት ጅቡቲና ሶማሊያ የሚላኩ ምርቶችን በመጠንና በጥራት እንዲጨምር ከአቅራቢዎችና ላኪዎች ጋር መወያየት ተችሏል። ከሶማሊላንድ የመጡ የንግድና ኢንቨስትመንት ሚኒስትር ጋር ወይይት ተደርጓል።

በአስተዳደሩ የሚገኘው ኢንዱስትሪ ፓርክ እንዲሁም እየተገነቡ ያሉትንና እያመረቱ የሚገኙ ኢንዱስትሪዎችን በማስጎብኘት በቀጣይ ምርቶች መዳረሻ እንዲሰፉና ትስስሩ እንዲጎለብት እየተሠራ ይገኛል ሲሉ ኃላፊው ገልጸዋል።

የሕገ-ወጥና የኮንትሮባንድ ንግድን ለመከላከልም በበጀት ዓመቱ ሥራዎች መሠራታቸውን ኃላፊው አንስተዋል፤ የጸረ-የሕገ-ወጥ ንግድና የፀረ-የኮንትሮባንድ ንግድ ዐቢይ ግብረ-ኃይልና በየቀበሌው በቋቋሙ ንዑሳን ግብረ- ኃይል አማካኝነት የተጋነነ የገበያ ዋጋ ጭማሪ ያደረጉ 5ሺህ 589 ነጋዴዎች ላይ አስተዳደራዊና ሕጋዊ ርምጃዎች ተወስደዋል ብለዋል።

በዚህም በህገ-ወጥ መንገድ ሲዘዋወር የነበረ ከ41 ሺህ ሊትር በላይ ነዳጅ በመውረስ ከአንድ ሚሊዮን 100 ሺህ ብር በላይ ለመንግሥት ገቢ ተደርጓል። ኢ መደበኛ ነጋዴዎችን ወደ መደበኛ ለመመለስ በተደረገው ጥረትም 5ሺህ 892 ወደ መደበኛ ንግድ ገብተዋል ብሏል።

# ነፃ ሃሳብ

# ብሪክስ አቃፊ ለሆነ የመልማት መርህ

**በትረ ሙሴ (መልከ ኢትዮጵ)**

ከሰሞኑ በደበብ አፍሪካ በተካሄደው 15ኛ የብሪክስ አባል ሀገራት ስብሰባ ላይ ሀገራችን ለአባልነት ያቀረበችው ጥያቄ ተቀባይነት እንዳገኘ መገለጹ ይታወሳል። በዚህም ጉባኤ ላይ ሀገራችንን ጨምሮ አርጀንቲና፣ ግብጽ፣ ኢራን፣ ሳውዲ አረቢያ እና የተባበሩት ዓረብ ኢሚሬቶችን በአዲስ አባልነት ተመዝግበዋል።

በጉባኤው ላይ የተሳተፉት ጠቅላይ ሚኒስቴር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ‹ይህ ለሀገራችን ታሪካዊ ሁነት ነው። ኢትዮጵያ ሁሉንም አካታች ለሚሆን የበለጸገ የዓለም ስርዐት መስፈን ከሁሉም ጋር ለመስራት ዝግጁ ናት› ሲሉ መልዕክት አስተላልፈዋል። በዚህ ጉባኤ ላይ ጥያቄአቸው ተቀባይነትን ያገኘ አዲስ አባላት ከፊታችን ባለው የፈረንጆቹ አዲስ ዓመት ቡድኑን በይፋ እንደሚቀላቀሉ በደቡብ አፍሪካው ፕሬዚዳንት በሲሪል ራማፎዛ በኩል ተገጿል።

አምስት ሀገራት ማለትም ብራዚል፣ ሩሲያ፣ ህንድ፣ ቻይናና ደቡብ አፍሪካ የተጣመሩበት ብሪክስ የተመሰረተው እንደፈረንጆቹ የዘመን ስሌት ከአስራ ሁለት ዓመት በፊት በ2009 ነው። መሰረቱን ሲያቆም ደቡብ አፍሪካ ባልተካተተችበት የአራት ሀገራት ምክር ሲሆን የኋላ ኋላ ከአንድ ዓመት ዝግመት በኋላ ማለትም በ2010 ደቡብ አፍሪካን አካቶ የቡድኑን ቁጥር አምስት አድርሷል።

ከጋርዮሽ የኢኮኖሚ ጥምረት ጎን ለጎን የጥቂት ሀገራትን የበላይነት ለመገዳደር አስቦና ተልሞ የተመሰረተው የአምስቱ ሀገራት ጥምረት የወደፊቷን ዓለም ገጽታ በበጎ ይቀይራሉ ተብለው ተስፋ ከተጣለባቸው ጥምረቶች አንዱ ነው። ባነገበው ዓላማና በሚከተለው ሁለንተናዊ መርህ በእስካሁኑ ጉዞው ከ40 የሚልቁ ሀገራት የአባልነት ጥያቄ አቅርበውበታል።

በራስ ወዳድነትና ሚዛናዊነትን በሳተ እሳቤ የሚንቀሳቀሰውን የዓለም ስርዐት ከማስተካከል አኳያ ትልቅ ድርሻ ያለው ብሪክስ እንደ አይ ኤም ኤፍ፣ የዓለም ባንክን እና ሌሎች የፋይንንስ ተቋማት አሰራራቸውን እንዲያሻሽሉ ጫና ከማድረግ ባለፈ፤ ለታዳጊ ሀገራት ምጣኔ ሀብት ድምጽና ውክልና ተቆርቋሪነትንም ለመፍጠር ያስችላል ተብሎ ይታመናል።

ከምንም በላይ ስርዐት አልበኝነት ለሚታይባት ምድርና የሰው ልጅ ፍትህንና እኩልነትን ማምጣት፣ በፖለቲካ ጣልቃ ገብነት የሚስተዋሉ ክፍተቶችን በማረቅ ለፍትህ ተሚጋች ከመሆን አንስቶ እስከ አቅም ግንባታ የሚዘልቅ አቅም መፍጠር የቡድኑ ተቀዳሚ ዓላማ ሆኖ ከፊት ተቀምጧል። ዓለም ያለፈችባቸውን ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ስርዐቶች በማጤንና በመገምገም ሁሉን ያማከለ ሁነኛ ምላሽ መስጠት የተቋቋመበት አንዱ ዓላማ ሆኖ እናገኘዋለን።

ከዶላር ውጪ ሌሎች ዓለም አቀፍ መገበያያዎች እንዲኖሩ፣ የዓለም ምጣኔ ሀብት እድገት ፍትሀዊ እንዲሆን እንደሚሰራ የሚጠበቅው ሕብረቱ፤ የተለያዩ ባህሎችን፣ አተያይና አረዳድ ታሪክ ያላቸውን ህዝቦች መያዙ እንደ አንድ ትልቅ አማራጭ ተደርጎ እንዲወሰድ ያደርገዋል። ጥምረቱ በሁሉም ረገድ የዓለምን ነባር ብልሹ አሰራር የሚሞግት፣ የሚያርቅና የሚያቀና አዲስና ዘመኑን የዋጀ አስተሳሰብ መሆኑን መነሻውን በማየት መረዳት ይቻላል።

ብሪክስ እንዳነሳሱ መድረሻውም የዛን ያክል ተስፋ ሰጪ ነው። በአሁኑ ሰዓት በምዕራባውያን ልብ ውስጥ ብርቱ ስጋትን በመፍጠር ላይ የሚገኝ የብዙሀን ነጸብራቅ ነው። ስጋቱን ከፍ ያደረገው ደግሞ በኃይል የበላይነት ወደአንድ ጎን ያጋደለውን ኢኮኖሚ ሚዛን በማስተካከል ፍትህ ላጡ ሀገራትና ህዝቦች የሚሞግት መሆኑ ነው።

በእንዲህ አይነቱ የጋራ ድምጽን ባነገበ መንገድ ካልሆነ በስተቀር በራስወዳድነት የተሞላውን አሁናዊ ዓለም አቀፍ ስርዓት መቋቋም አይቻልም። ህብረቱ አዳዲስ አባሎችን እየጨመረ በሀሳብና በተግባር፣ በአቅምና በገንዘብ እየጎለበተ በሄደ ቁጥር በዓለም አቀፍ ደረጃ ተጨባጭ የፍትህ ለውጥ እንደሚያመጣ በብዙዎቹ ታምኖበታል።

ደቡብ አፍሪካ ላይ በተዘጋጀው ጉባኤ ላይ አዲሶቹን አባላት እንኳን ደስ አላችሁ ከማለት ጀምሮ ልዩ አቀባበልን በማድረግ ‹ኑ አብረን እንስራ፣ የሚለው የህብረቱ ድምጽም የዚሁ እውነታ አንዱ መገለጫ ነው።

አምስቱ የብሪክስ አባላት የህዝብ ቁጥር እንደዋነኛ የኢኮኖሚ መገንቢያ አቅም ተደርጎ በሚወሰድበት በዚህ ዘመን በህዝብ ቁጥራቸው ግንባር ቀደምት ናቸው፤ ቻይናና ህንድ በህዝብ ቁጥራቸው ከቀዳሚዎቹ ተርታ የሚሰለፉ ናቸው። ብራዚልን ብንወስድ በአራተኛ ደረጃ ላይ የምናገኛት ሀገር ናት።

በኢኮኖሚ ደረጃም እጅግ የበረታ አቅም ያላቸው፣ መጪውን የዓለም ፖለቲካና ኢኮኖሚ ይቆጣጠራሉ ተብለው ከተተነበየላቸው ውስጥ የተቀመጡ ናቸው። ከጠቅላላው የዓለም ህዝብ 3.24 ቢሊዮን የህዝብ ቁጥር ይዘዋል። በጋራ 26 ትሪሊዮን ዶላር ታቅፈዋል። ይሄ አሀዝ የዓለምን 26 ከመቶ ምጣኔ ሀብት የሚይዝ ነው።

ብሪክስ መነሻውን ያደረገው በሶስት አበይት ዓላማዎች ነው። የመጀመሪያው የኢኮኖሚ ትብብርን በመፍጠር የንግድ ልውውጡን በማስፋት በኢኮኖሚው ዘርፍ የማይበገር ሚና መጫወት ነው። ሁለተኛው በሁሉም ዘርፍ ቀጣይነት ያለውን እድገት ማበረታታት ሲሆን በሶስተኛነት የምናገኘው ፖለቲካዊ አንድምታ የሚለውን ነው። እኒህን ሶስት ተቀዳሚ ዓላማዎች ወደ አንድ ስንጨምቃቸው ፍትህና እኩልነት የሚል የጋራ መጠሪያ ይሰጡናል።

ብሪክስ መነሻው ፍትሀአዊ ዓለም አቀፍ ስርአት መፍጠር ነው። ወደ አንድ በኩል ያዘነበለ የዓለምን ሽፋፋ አቋም ማስተካከል ነው። ያለፍትህ የተያዙ የኢኮኖሚና የፖለቲካ የበላይነትን ማዳከምና ሀገራት ነጻ የሆነ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ እንቅስቃሴአቸውን ያለማንም ጣልቃ ገብነት እንዲከውኑ ማስቻል ነው። የጋራ እሴት፣ የጋራ የኢኮኖሚ ጥምረት በመመስረት የእርስ በርስ መደጋገፍን ማሳደግ ነው።

በአሁኑ ሰዓት ዓለም በሁለት ጎራ እየተከፈለች ያለች ይመስላል። የመጀመሪያው አሜሪካ እና ምዕራባውያን ወዳጆቿን ያቀፈው ቡድን ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ብሪክስ ቻይና፣ ሩሲያን ፣ ህንድ ፣ ብራዚል እና ደቡብ አፍሪካን የያዘው /ብሩሪክስ / ነው ።

አሜሪካ በምትመራው አሁነኛ የዓለም ስርዓት ብዙ የዓለም ሀገራት ተጽዕኖ ውስጥ ወድቀዋል። ይሄን ተጽእኖ ለመፋቅ እንደብሪክስ ያሉ በጋራ ሀሳብ የጋራ ህልም ያለሙ ሀገራት ወዳጅነትን ፈጥረው በኢኮኖሚና በፖለቲካው ዘርፍ ልዩነትን ለመፍጠር መነሳታቸው የሚበረታታ ነው። አማራጭ የዓለም ስርዓት ለመፍጠርም የተሻለ እድል ይፈጥራል።

ብሪክስ የብዙ አስተሳሰቦች፣ የብዙ ፍላጎቶች፣ ለፍትህ የቆሙ የብዙ መሻቶች ጥርቅም ከመሆኑ አንጻር፣ ይሄ አስተሳሰብ እንደ አፍሪካ ላሉ በድህነትና በኋላ ቀርነት ከፍ ሲልም በጦርነትና ባለመረጋጋት በሚታመሱ ሀገራት ላይ የራሱ የሆነ በጎ ውጤት ይዞ እንደሚመጣ ይታመናል። ከኢኮኖሚና ከፖለቲካ መረጋጋት እኩል በሰላምና በሌሎች ማህበራ እሴት ግንባታዎች ላይ የራሱ አስተዋጽኦ ያለው ስብስብ ነው።

ማንም ገብቶ በሚወጣበት፣ ማንም የፈለገውን አድርጎ እንዲህ አድርግ እንዲያ አድርግ በሚልበት የአፍሪካ አህጉር ውስጥ ጣልቃ ገብነትን ከመከላከል እና የራስን እድል በራስ ከመወሰን አንጻር ድርሻው የላቀ ነው። በሀገራችን አሁናዊ ሁኔታ ውስጥም ከሰላም ፈጣሪነት እና ከኢኮኖሚ መነቃቃት ጋር አስተሳስረን ልናይም የሚገባ ክስተት ነው።

ጥምረቱ መነሻው ሀሳብ ነው። በአንድነት ለአንድነት አይነት መልዕክት ያለው ሁሉን አቃፊ የአዲስ ስርዓት ጅማሬ ነው። የፍትህና የአብሮ መልማት እሳቤ ጎልቶ የሚደመጥበት ነው። ይህ እሳቤ አማራጭ አጥቶ ለከረመው ለአፍሪካ ሀጉር ሁለንተናዊ ተሀድሶን የሚያመጣ የንቃት፣ የብርታት ድምጽ ነው።

በአፍሪካውያን ልብና መንፈስ አእምሮ ውስጥ ከፍ ያለ መነቃቃት መፍጠር የሚችል ነው። ይህ በሁሉም ረገድ ድጋፍና ትብብር ያልተለየው ተያይዘን ዓለምን እናያያዝ አይነት መነሻ ያለው የብሪክስ የአስተሳሰብ መሰረት ሀገራችንን በብዙመልኩ እንደሚጠቅማት ለመገመት የሚከብድ አይደለም።

ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ መረጋጋትን ለመፍጠር ትልቅ አቅም መፍጠር የሚያስችል ነው። እንደ አንድ አባል ሀገር ለሰላምና ለጀመርናቸው የለውጥ እንቅስቃሴዎች የሀሳብ እና የንቃት አውድ ሆነው ሊያገለግሉን ይችላሉ።

ብሪክስ ባጠቃላይ ለአፍሪካና ለመላው ዓለም ‹የአዲስ ስርዓት ውልደት ነው ብሎ ለመቀበል ጊዜ ቢጠይቅም፤ ከተነሳበት የአስተሳሰብ መርህ አንጻር በስብስቡ ተስፋ ማድረግ ግን ብዙም እንደአላዋቂነት የሚያስቆጥር አይሆንም። በጥምር ጉባኤው በኩል የሚስተዋሉ የለውጥ ቁርኝቶች መጪውን ጊዜ ተስፋ እንድንጥልበት እድል የሚሰጡን ናቸው።

ከግለኝነትና ከአንባገነንነት በጸዳ መንገድ የዓለምን ችግር በዓለም አቀፍ ሀሳብና መፍትሄ ለመፍታት ዓለም አቀፉን ማህበረሰብ የመረጠ ስብስብ ነው። ሀገራችንም ከዚህ ጥምረት የራሷን አስተዋጽኦ በማድረግ ከራሷ አልፋ ሌሎችን እንደምትጠቅም በብዙዎች ዘንድ ተስፋ ሰንቋል።

እንደ ሀገር ሀገራችን ኢትዮጵያ ከናይጄሪያ ቀጥሎ በህዝብ ብዛት ከአፍሪካ ቀዳሚ ሀገር ነች። በአፍሪካ እና በምስራቅ አፍሪካ በተለይም ከሰሀራ በታች ካሉ ሀገራት በኢኮኖሚ ግስጋሴዋ ቀዳሚ ሆና ትጠቀሳለች። በታሪክ፣ በባህል፣ ለሰላም ባላት ጽኑ መሻትና ዓለም አቀፉን የቅኝ ወራሪ ስርዓት ታግላ በመጣል ለአፍሪካና ለመላው ጥቁር ህዝብ የንቃት እና የነጻነት ፋና ወጊ ነች፣ በቆዳ ስፋት፣ በተፈጥሮ ሀብቶቿ በሌሎችም በርካታ ጸጋዎቿ የአባልነቷ ጥያቄ ተቀባይነትን አግኝቷል።

ከምንም በላይ የብሪክስ አባል መሆኗ ትልቅ ዲፕሎማሲያዊ ድል ነው። በዲፕሎማሲው ዘርፍ ያሳየችው ተጨባጭ ስራ ለእንዲህ አይነቱ መልካም አባልነት አሳጭቷታል። ከዚህ አይነቱ እድልና ድልን ከያዘው መልካም አጋጣሚ በመማር ቀጣይም በዲፕሎማሲው ዘርፍ የተሻለ ስራ በመስራት ሌሎች እድሎችንም መፍጠር እንደሚቻል ጥቁምታ የሰጠ ነው።

በሰላምና በተረጋጋ ማህበራዊ ንቃት ሀገሪቱ ውስጥ ተጨባጭ ዘላቂ ሰላም ከመጣ ከየትኛውም ሀገር በላይ ለእንዲህ አይነቱ ዓለም አቀፍ አባልነት ተመራጭ እንደሚያደርጋት ለጥያቄ የሚቀርብ አይሆንም። የድሌም ተጠቃሚ በመሆን ለውጥ ለማምጣት የሚከብደን አይሆንም።

ሀገራችን የብሪክስ ጥምረት ውስጥ የራሷን ሀሳብ፣ የራሷን አቋም፣ የራሷን እውነት ይዛ ለዓለም ፍትህ ዘብ የምትቆምበት ጊዜ ላይ ነች። እድልና አጋጣሚዎችን ካገኘን ብዙ ስራዎችን ለዓለም እንደምናበረክት ያለፉ ታሪኮቻችንን ማየቱ በቂ ነው። በጀመርነው መንገድ ቀጥለን በኢኮኖሚውና በፖለቲካው አሁን ያለውን የህዝብ ጥያቄ በመመለስ የተሻለች ሀገር መፍጠር እንችላለን።

ለዓለም ሰላም፣ ለዓለም እኩልነት ከነጻነት ናፋቂዎች ጋር መሰለፋችን ታሪክ ትላንትናን ሲበረብር የሚያገኘው ዘመን ተሻጋሪ ድላችን ነው። ድል የሚጣፍጠው ከውጤት ጋር በመሆኑ እድሉን ወደ ፍሬ ለመለወጥ አሁን ላይ ሀገራዊ ፈተና የሆነብንን የሰላም እጦት በሰላም ለመፍታት ሁላችን ዘብ ልንቆም ይገባል።

> **አሜሪካ በምትመራው አሁነኛ የዓለም ስርዓት ብዙ የዓለም ሀገራት ተጽዕኖ ውስጥ ወድቀዋል። ይሄን ተጽእኖ ለመፋቅ እንደብሪክስ ያሉ በጋራ ሀሳብ የጋራ ህልም ያለሙ ሀገራት ወዳጅነትን ፈጥረው በኢኮኖሚና በፖለቲካው ዘርፍ ልዩነትን ለመፍጠር መነሳታቸው የሚበረታታ ነው**

ኢኮኖሚ

# ግብርና

# የሜትሮሎጂ ትንበያውን ለግብርናው ውጤታማነት

**ጽጌረዳ ጫንያለው**

በኢትዮጵያ የግብርናው ሥራ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ በሁለት ዋና ዋና ወቅቶች ተከፋፍሎ ነው በስፋት ሲከናወን የኖረው፤ በበልግና በመኸር። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ የበጋ ወቅት የመስኖ ስራ ሌላው ሰፊው የግብርና ስራ ሆኖ መጥቷል።

ሀገሪቱ አሁን በመኸር ወቅት የግብርና ስራ ላይ ትገኛለች። ክረምት ወይም የመኸር ወቅት የግብርናው ስራ በስፋት የሚከናወንበት እንደመሆኑ ይህ ወቅት አርሶ አደሩ ዝናብ፣ ብርድ፣ ጭቃ ሳይል ቀን ከሌት የሚተጋበትና ነገን ተስፋ አርጎ የሚሰራበት ነው። በሰኔና ሐምሌ የበረታ ገበሬ የዕለት ጉርሱን የዓመት ልብሱን ያገኛል። ለዚህም ነው አርሶ አደሩ በዚህ ወቅት በሕይወቱ ትርጉም ያለው ሥራ የሚሰራው፤ ለከተሜውም በአጠቃላይም ለሀገር የሚተርፍ ተግባር የሚያከናውነው።

የግብርና ስራ የሀገርና ህዝቧ ዋልታና ማገር መሆኑን የተገነዘበው መንግስትም ከአርሶ አደሩ ባልተናነሰ ለእዚህ ወቅት የግብርና ስራ ተግቶ ይሰራል። የግብርናው ዘርፍ ተዋንያንም በዚህ ወቅት ላይ ለአርሶ አደሩ መረጃ በማድረስ፣ ቴክኖሎጂ በማቅረብ፣ ምክር በመስጠት፣ ሌሎች የተለያዩ ድጋፎችን በማቅረብ በትኩረት ይሰራሉ። የኢትዮጵያ ብሔራዊ ሚትሮሎጂ ኢንስቲትዩትና የግብርና ሚኒስቴር የስራ ኃላፊዎች ሰሞኑን ከሰጡት መግለጫ መረዳት የሚቻለውም ይህንኑ ነው።

የኢትዮጵያ ሚትሮሎጂ ኢንስቲትዩት በመግለጫው መነሻውን ያደረገውም ያለፈውን ዓመት የክረምት ወቅት ትንበያ ነው። እስከ ቀጣዩ በጋ ድረስ የዘለቀ ትንበያም ተሰጥቷል። እስከ 2016 ዓ.ም ያለው የበጋ ወቅት ጭምር ምን ያህል መጠን ያለው ዝናብ በየትኛው አካባቢ ይኖራል በሚለው ላይ ሰፊ ትንታኔ ሰጥቶበታል።

በተመሳሳይ የትንበያው ቀጣይነትም በመድረኩ ላይ በምን መልኩ እንደሚከናወን የተነሳ ሲሆን፤ ግብርና ሚኒስቴርም ከወጡት ትንበያዎች ጋር በተያያዘ የግብርና ሥራውን በምን መልኩ እያስኬደ እንደሆነ፤ ቀጣይ የሚሰሩ ሥራዎችና ተያያዥ ጉዳዮችን የተመለከቱ መረጃዎችን በሚኒስቴሩ በሚኒስትር ዴኤታው በኩል አመልክቷል።

የኢትዮጵያ ሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተር አቶ ፈጠነ ተሾመ በመድረኩ ላይ እንደተናገሩት፤ ኢንስቲትዩቱ ለተለያዩ መንግስታዊና መንግስታዊ ላልሆኑ ተቋማት የሚሰጠውን ወቅታዊ የአየር ጠባይ ትንበያ አገልግሎትን ይበልጥ ለማጠናከር በተለይም ለአየር ሁኔታና ጠባይ ተጋላጭ የሆኑ ተቋማትን ከየተቋማቸው አኳያ በተሰጠው ትንበያ መሰረት ሥራቸውን እንዲያከናውኑ ለማስቻል በየወቅቱ የአየር ጠባይ ግምገማ ያደርጋል፤ ምክረ ሀሳብም ይሰጣል። ከዚህ አኳያም ብዙ ሥራዎች ውጤታማ ሆነው ታይተዋል። በተለይም ከግብርናው ጋር በተያያዘ ብዙ የመፍትሄ አቅጣጫዎችን ማሳየት ተችሏል።

የባለፈው ክረምት 2014/15 ዓ.ም ወቅትን ብቻ ብንመለከት በተሰጠው ትንቢያ መሠረት ዝናቡ እንደተጠበቀው በደቡብ ምዕራብ አካባቢዎች ላይ ቀድሞ መጀመሩን አስታውሰው፣ የዝናቡ መጠንና ስርጭትም በአብዛኛው የሀገሪቱ የወቅቱ ዝናብ ተጠቃሚ አካባቢዎች ላይ የተስፋፋና የተጠናከረ እንደነበር ጠቅሰዋል። ከሰኔ እስከ ነሐሴ የነበረው ዝናብም ለክረምት ዝናብ ተጠቃሚ አካባቢዎች ከፍተኛ ጠቀሜታ መስጠቱን ገልጸው፣ በዚህም አርሶ አደሩ በተገቢው መጠን እንዲጠቀምበት ማስቻሉን አብራርተዋል።

እሳቸው እንዳሉት፤ የክረምቱ ወቅት መደበኛ ዝናብ ብቻ ሳይሆን ከባድ መጠን ያለው ዝናብም አስተናግዷል። ስለዚህም የተሰጠው ትንበያ ይህ ባጋጠማቸው መካከለኛው፤ ሰሜን ምስራቅ እና ደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ አንዳንድ ቦታዎች ላይ የጎርፍ ክስተት ስለነበረ ቅድመ ማስጠንቀቂያው ደርሷቸው ከአደጋ ድነዋል። ትንበያው እለታዊ ተጽእኖውን መቋቋም እንዲቻልም አድርጓል ይላሉ። በተጨማሪም ያለውን አወንታዊ ነገር ያሳየ በመሆኑ ማለትም ቀጣዩ ወቅት እርጥበትን የያዘ እንደሚሆን በመንገሩ አርሶአደሩ ያንን እድል እንዲጠቀምበትም ማስቻሉን ነው ዋና ዳይሬክተሩ ያመለከቱት።



በመድረኩ ላይ የተለያዩ ተቋማት የሥራ ኃላፊዎች ተገኝተዋል

አቶ ፈጠነ የዘንድሮ የክረምት ዝናብም እንዲሁ ያለውን ትንበያ መሰረት ያደረገ መሆኑን አንስተዋል። እርሳቸው እንዳሉትም፤ ይህ ወቅት በምዕራብ አጋማሽ የሀገሪቱ አካባቢዎች መደበኛ እና ከመደበኛ በላይ እንዲሁም በሰሜን ምስራቅና የምስራቅ መደበኛና ከመደበኛ በታች ዝናብ ይስተናገድበታል። በአንዳንድ አካባቢዎች ይኸው የመኸር ወቅት ዝናብ በከፍተኛ ሁኔታ ተለዋዋጭነት የሚያሳይበት ሁኔታም ይኖራል። ይህም ሁኔታ እንዲፈጠር የሚያደርገው የትሮፒካል ፓስፊክ ውቅያኖስ የባህር ወለል ሙቀት ከመደበኛው በላይ መሆኑ ነው። ስለዚህም ኢሊኖ የመሆን አጋጣሚን ይፈጥራል። ይህ ደግሞ ለአርሶ አደሩ የግብርና ሥራ እንቅስቃሴ እንዲሁም ለተፋሰሶች የውሃ አቅርቦት በማሻሻል ረገድ አዎንታዊ ተፅዕኖ ይኖረዋል።

አቶ ፈጠነ የመጪውን የበጋ ማለትም የ2016 ዓ.ም የአየር ጠባይ ትንበያን በተመለከተም ማብራሪያ ሰጥተዋል፤ በዚህ ትንበያ መሠረትም « መጪው በጋ የትሮፒካል ፓስፊክ ውቅያኖስ ከመደበኛ በላይ የባህር ወለል መሞቅ ስለሚያመጣ ኢሊኖ ይፈጠራል። ይህ ደግሞ የሰሜናዊ ህንድ ውቅያኖስ ከመደበኛ በላይ የባህር ወለል የሙቀት መጠን አወንታዊ ሚና እንደሚኖረው የትንበያ መረጃዎች ያመላክታሉ። ስለዚህም አርሶአደሩና በዚያ አካባቢ የሚኖሩ ማንኛቸውም ሰራተኞች የወቅቱ ዝናብ አጀማመር በአብዛኛው የበጋ ዝናብ ተጠቃሚ አካባቢዎች ቀድሞ እንደሚጀምር አውቀው ልዩ ዝግጅት ማድረግ ይኖርባቸዋል» በማለት አስረድተዋል።

ዝናቡ በአወጣጥ ደረጃም ይዘገያል ያሉት አቶ ፈጠነ፤ በዚሁ መሰረት የዘንድሮ የበጋ ወቅት ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት የደቡብና ደቡብ ምስራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ከመደበኛ በላይ ዝናብ ይኖራል ሲሉ ጠቁመው፣ ይህንን አጋጣሚ መጠቀም እንደሚያስፈልግ ያስረዳሉ። በተመሳሳይ የምዕራብ አጋማሽ የሀገሪቱ አካባቢዎች ደግሞ መደበኛና ከመደበኛ በላይ ዝናብ እንደሚኖርባቸው ተናግረው፣ ከዚህ አኳያም ሁኔታውን አውቆ መስራት እንደሚያስፈልግ ያሳስባሉ።

በአሁኑ ወቅት እየተስተዋሉ ከሚገኙት የአየር ሁኔታ ክስተቶች በመነሳት በሰሜን፤ በመካከለኛው፥ በምስራቅና በሰሜን ምዕራብ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ወቅቱን ያልጠበቀ ዝናብ ሊፈጠር እንደሚችልም ዋና ዳይሬክተሩ ይጠቁማሉ። በሌላ በኩል ደግሞ የቀኑ ዝቅተኛ የሙቀት መጠን በሰሜን ምስራቅ፤ መካከለኛውና በምስራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ አልፎ አልፎ ከአምስት ዲግሪ ሴልሽየስ በታች ሊሆን እንደሚችል ያመላክታሉ። ከዚሁ ጋር አያይዘው ህብረተሰቡ በሚቀጥለው የበጋ ወቅት የሚጠበቀውን የአየር ጠባይ ትንበያን ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት እና የሚገኘውን የዝናብ መጠንና ሰርጭት በአግባቡ በመጠቀም በዚህ ወቅት የሚካሄደውን የግብርና እንቅስቃሴ እና ሌሎች ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሥራዎችን ከባለሙያዎች ጋር በመመካከር መከወን እንዳለበት አስገንዝበዋል።

በመድረኩ ላይ የተገኙት የግብርና ሚኒስቴር ሚኒስትር ዴኤታ ዶክተር መለስ መኮንን ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፡ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ሜትሮዎሎጂ ኢንስቲትዩት በየጊዜው የሚያወጣቸው መረጃዎች ለግብርና ሥራው እጅግ ወሳኝ ናቸው። በመሆኑም መረጃዎቹን መሰረት በማድረግ እንደ ግብርና ሚኒስቴር በርካታ ተግባራት ተከናውነዋል። አንዱ ደግሞ በዚህ በመኸር ወቅት የተከናወነው ተግባር ነው።

ትንበያው በሰጠው መረጃ መሰረት ከተከናወኑ ሥራዎች መካከል አንዱ ከዝናብ ጋር ተያይዞ የተሰራው ሥራ ሲሆን፤ ያጋጠሙ ችግሮችን በተለያየ መልኩ ለመፍታት ተሞክሯል። የዝናብ እጥረት ሲያጋጥም እጥረቱ ያጋጥማቸዋል በተባሉ አካባቢዎች ላይ ሌሎች የውሃ አማራጮችን መጠቀም የሚያስችሉ ሥራዎችን ማከናወን ተችሏል። በተመሳሳይ ከአየር ንብረቱ ጋር የሚስማሙ ሰብሎች እንዲዘሩ የማድረግ ሥራም ተከናውኗል። ይህ ደግሞ አርሶ አደሩ ችግሩን በመፍትሄ እንዲያቀለው አድርጎታል ይላሉ።

ዶክተር መለሰ አክለውም፤ ትንበያው በሰጠው መረጃ መሰረት መሥራት የተባይ ክስተት ከመከላከል አኳያም ትልቅ አስተዋጽኦ ማበርከቱን አስታውቀዋል። ለአብነት በአንዳንድ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ በነበረ የዝናብ ወጣ ገባነት ምክንያት ተምች ተፈጥሮ እንደነበር አስታውሰው፣ ቀድሞ መረጃው ስለነበርና መሬቱ እርጥበት የያዘበት ሁኔታ በመፈጠሩ ክስተቱ ቢፈጠርም ምንም አይነት ጉዳት ሳያስከትል መከላከል ተችሏል ብለዋል። በሌላ በኩል የበረሃ አንበጣ ክስተትም የተፈጠረ ቢሆንም ይህንንም ክስተት እንዲሁ ጉዳት እንዳያደርስ ተደርጎ መመከት ተችሏል ብለዋል።

እሳቸው እንዳሉት፤ የበረሃ አንበጣው የተፈጠረበት ምክንያት ደረቃማ ሁኔታዎች በመኖራቸው የተነሳ ነው። በተለይ በሀገሪቱ ሰሜናዊው ክፍል ችግሩ በስፋት ታይቷል፤ ከጅምሩ ለማጥፋት ትንበያው ምቹ ሁኔታዎችን ፈጥሯል። የአየር ጸባይ ትንበያው መረጃ በመኖሩ ምክንያት እየተከታተሉ መከላከል ላይ የመስራት ተግባር ተከናውኗል። በዚህ ደግሞ አሁን ላይ መጀመሪያ የተከሰተበትን ትግራይን ጨምሮ አፋርና አማራ ክልልን ከአንበጣ ነጻ ማድረግ ተችሏል።

ይህ የበረሃ አንበጣ በሌሎች አካባቢዎች ላይ እየታየ መሆኑን የጠቀሱት ሚኒስትር ዴኤታው፤ ቀደም ብሎ በተከሰተባቸው አካባቢዎች ላይ የለም ይባል እንጂ ዳግመኛ አይከሰትም ተብሎ መወሰድ እንደሌለበት ተናግረዋል፤ በቀጣይም እነዚህ አካባቢዎች ላይ ዝናብ ወጣ ገባ ሊሆን እንደሚችል የአየር ትንበያው እንደሚያሳይ ጠቅሰው፣ በዚህም ላይ ቀደም ብሎ እንደተሰራበትና ጉዳት ሳያደርስ ችግሩን መመከት እንደተቻለ ሁሉ አሁንም ለሚከሰቱ ችግሮች በተጠንቀቅ ሆኖ መፍትሄ መስጠት ያስፈልጋል ብለዋል።

እንደ ግብርና ሚኒስቴር እነዚህንና መሰል ችግሮችን ለመፍታት ትንበያዎች በሚያመላክቱት መልኩ የሚሰራ ይሆናል። በሰው ኃይል፣ በአውሮፕላን እንዲሁም በኬሚካል የመከላከል ሥራውም ተጠናክሮ ይቀጥላል ያሉት ሚኒስትር ዴኤታው፣ የዝናብ ሁኔታው ትንበያ እየታየ ክትትልና ቁጥጥርም የሚደረግ ይሆናል ብለዋል። በተለይም የአንበጣ መንጋው ከዚህ በፊት ያደረሰው ጫና ስለሚታወቅ እጭ ጥሎ እንዳያድግ ከማድረግ አኳያ ግብርና ሚኒስቴር በሁሉም ሁኔታ ራሱን አዘጋጅቶ አሰሳ እያደረገ መሆኑንም አስታውቀዋል።

የሜቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት በየጊዜው የሚሰጠው ትንበያ በተለይም ለግብርናው ሥራ ወሳኝ መሆኑን የሚናገሩት ሚኒስቴር ዴኤታው፤ በሚሰጠው ትንበያ መሠረት ቅድመ ዝግጅት ሁሌም እንደሚደረግና ሚኒስቴሩ እየተጠቀሙበትም እንደሆነም ያስረዳሉ። ለዚህም አብነት የሚያደርጉት ደግሞ በክረምት ወቅት በተሰጠው ትንበያ መሠረት ለግብርናው እንቅስቃሴ አስፈላጊውን ዝግጀት በማድረግ ውጤት መመዝገቡን ነው።

15 ነጥብ ስምንት ሚሊዮን ሄክታር መሬት በዘር መሸፈን ለተቻለበት ሁኔታ ትንበያው አስተዋጽኦ ማድረጉን ጠቅሰው፤ አሁንም ዘር በሚከናወንባቸው አካባቢዎች ላይ ትንበያውን መሰረት በማድረግ እየተሰራ መሆኑ ጠቁመዋል።

በመርሃግብሩ ላይ በአየር ንብረት ለውጥ ሳቢያ ሊከሰቱ የሚችሉ የአደጋ ስጋቶችን ቀድሞ መከላከል ላይ ያተኮረ “ቅድመ ማስጠንቀቂያ ለሁሉም” የተሰኘ ዓለም አቀፍ ፕሮጀክት ተግባራዊ እንደሚደረግም ተጠቁሟል።

የውሃና ኢነርጂ ሚኒስትር ዴኤታ ዶክተር አብርሃም አዱኛ ጉዳዩን አስመልክቶ በሰጡት ማብራሪያ እንዳሉት፤ “ቅድመ ማስጠንቀቂያ ለሁሉም” የሚለው ፕሮጀክት በተባበሩት መንግስታት ድርጅት ዋና ፀሐፊ አንቶኒዮ ጉተሬዝ ሀሳብ አመንጭነት የተጀመረ ነው። የሰው ልጅ ከአስጊ የአየር ሁኔታ፣ ከአየር ንብረት ክስተቶችና ከውሃ ዑደት ለውጥ ጋር በተገናኘ ከሚከሰቱ ችግሮች እንዲጠበቅ የሚያደርግ ፕሮጀክት ነው። ፕሮጀክቱ ከውሃና አየር ንብረት ለውጥ ክስተቶች ጋር የተያያዙ ችግሮችን ለመቀነስና የተጎጂውን ማህበረሰብ የአየር ንብረት ለውጥ ተፅዕኖን የመቋቋም አቅምን ለማሳደግ ያግዛል።

ፕሮጀክቱ በዓለም የሜቲዎሮሎጂ ድርጅት ዋና አስተባባሪነት የሚተገበር ሲሆን፤ ለፕሮጀክቱ 30 ሀገራት ተመርጠዋል። ከእነዚህ መካከልም በአፍሪካ ደረጃ ምርጫው ውስጥ የገቡት ኢትዮጵያ፣ ሱዳን፣ ደቡብ ሱዳንና ዩጋንዳ ናቸው። ኢትዮጵያ በዚህ ፕሮጀክት ተመራጭ እንድትሆን ያደረጋት ደግሞ አረንጓዴ አሻራን ጨምሮ የአየር ንብረት ለውጥን ለመከላከል እያደረገች ያለችው አስተዋጽኦ እና የቅድመ ማስጠንቀቂያ ሥራ እንደሆነ ዶክተር አብረሃም ጠቅሰው፣ ፕሮጀክቱ እ.ኤ.አ ከ2023 እስከ 2028 ለአምስት ዓመታት እንደሚቆይም አስረድተዋል።

ማህበራዊ

# አስኳላ

# አዲሱ የትምህርት ዘመንና የትምህርት ቤቶች ዝግጅት

ግርማ መንግሥቴ

ተማሪዎች ለሁለት ወራት ያህል እረፍት ላይ ነበሩ። እረፍት ላይ ይሁኑ እንጂ እረፍታቸውን ያሳለፉበት መንገድ ግን ከተማሪ ተማሪ ይለያያል። የገጠር ተማሪ ከከተሜው፤ ከተሜ እራሱ ከመሀል ከተሜው እንደሚለያይ ሁሉ፤ የግል ምርጫ ጉዳይ ሲኖር ደግሞ በአንድ ቤት ውስጥ ያሉ ሁለት ወንድማማቾች በፍላጎት እንኳን እንደሚለያይ ግልፅ ነው። በአብዛኛው ግን ተማሪዎች በአካባቢያቸው በሚገኙ ቤተ መፃህፍት ውስጥ የእረፍት ጊዜያቸውን እንዳሳለፉ ይገመታል።

ተማሪ ላምሮት ኪዳነማሪያም አብዛኛውን የእረፍት ግዜዋን ያሳለፈችው መሀል አራት ኪሎ በሚገኘው አብርሆት ቤተመጻሕፍት ውስጥ ያሉና ለእርሷ የሚስማሙ መፅሃፍትን በማንበብ ነው። ካነበበቻቸው መፅሃፍትም በርካታ ቁምነገሮችን፣ እውቀቶችንና መረጃዎችን አግኝታለች። ላምሮት የክረምቱን ወቅት መፅሃፍቶችን በማንበብ ብታሳልፍም ታዲያ አዲስ ዓመት በመቃረቡና የትምህርት ግዜም ሊጀመር በመሆኑ ቀጣዩ ትኩረቷ ትምህርቷን በትጋት መከታተል ነው። ለዚህም በእረፍት ግዜዋ በሚገባ ራሷን አዘጋጅታለች።

አዎ! መስከረም ለሁሉም ሰው አንድ ሆኖ ለመምህራንና ተማሪዎች ግን ይለያል። የልዩነቱ መሰረት ደግሞ ሌላ ሳይሆን ትምህርት ነው። የትምህርት ተቋማት ለሁለት ወራት ተዘግተው ዳግም የሚከፈቱት በአዲሱ ዓመት በወርሃ መስከረም ነው። ተማሪዎችም ወደ ትምህርት ገበታቸው የሚመለሱት አዲስ ዓመት ሲገባ ነው። የዘንድሮው የትምህርት ዘመን መስከረም 3 ቀን 2016 ዓ.ም እንደሚጀመርም በትምህርት ሚኒስቴር በኩል ተገልጿል። ትምህርት ቤቶችም ዝግጅታቸውን እያጧጧፉ ይገኛሉ።

በመስከረም ወር ወደ ትምህርት ገበታቸውና አዲስ ወደ ተዛወሩበት የክፍል ደረጃ እንደሚገቡ ያወቁ ተማሪዎች ትምህርት ቤት ተከፍቶ ከጓደኞቻቸው ጋር ለመገናኘት ናፍቀዋል። የአዲሱ ክፍል ትምህርታቸው ምን እንደሚመስል ለማወቅ ልባቸው ተሰቅሏል። ምን አይነት መምህር ለምን አይነቱ ትምህርት እንደሚመደብላቸው ለማየት ጉጉታቸው ከጣራ በላይ ሆኗል። ትምህርት ቤት ነገ ቢከፈት ደስታቸው ነውና ለእነርሱ መስከረም 3 ሩቅ ነው።

ይህ እንዳለ ሆኖ ታዲያ አዲሱ ዓመት መጥቶ፣ በመማር-ማስተማር ሂደት እንቅስቃሴ ውስጥ ወሳኙን ሚና የሚጫወቱት፣ ትልቁንም ድርሻ የሚይዙት ትምህርት ቤቶች መሆናቸው ግልፅ ነው። “የትምህርት ገበታ” የሚለውም የሚያመለክተው ይህንኑ መሰረታዊ ጉዳይ ነው። የዛሬው ጽሑፍም የበለጠ በትምህርት ቤቶች ላይ ያተኩራል።

የትምህርት ቤቶች መከፈቻ ይፋ የተደረገበት ቀን አገር አቀፋዊ ይዘት ያለው ቢሆንም በጊዜና ስፍራ ውስንነት ምክንያት አዲስ አበባ ያሉ የተወሰኑ ትምህርት ቤቶችን ዝግጅት ብቻ ወስዶ መመልከቱ በቂ ነው። ይህም የተደረገው በአጠቃላይ ትምህርት ቤቶች ገፅታቸውም ሆነ እንቅስቃሴና ተግባራቸው በአብዛኛው ተመሳሳይ እንደ መሆኑ ጥቂቶቹ አብዛኛዎቹን ትምህርት ቤቶች ይወክላሉ በሚል መነሻ ነው።

በአዲስ አበባ ከተማ የሚገኙ ትምህርት ቤቶች በተያዘላቸው ቀነ ቀጠሮ መሰረት ተከፍተው፤ ተማሪዎች ወደየ ትምህርት ቤታቸው መጥተውና አስፈላጊው አቀባበል ተደርጎላቸው የመማር ማስተማሩን ተግባር ለመጀመር ተፍ ተፍ እያሉ ነው። ከነዚህ ውስጥ አንዱ ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል የመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤት እና አፀደ ህፃናት ነው።

የትምህርት ቤቱ መምህርና የመምህራን ልማት ምክትል ርእሰ መምህር አቶ መስፍን ገብረእግዚአብሄሔር እንደሚሉት፣ ተማሪዎችን በጥሩ ሁኔታ ለመቀበል የሚያስችሉ ስራዎች እየተሰሩ ይገኛሉ። በተለይም የትምህርት ቤቱን አጠቃላይ ሁኔታ መቀየርን በተመለከተ እየተሰሩ ያሉ በርካታ ስራዎች አሉ። ከነዚህ ውስጥም የመማሪያ ክፍሎችን ከማስዋብና ምቹ ማድረግ አንዱ ነው። ሁሉ ነገር አልቆ የመማሪያ ክፍሎች ለእድሳት ዝግጁ ተደርገዋል። ጨረታውን ያሸነፈው አዳሽ ድርጅትም ዝግጅቱን አጠናቅቆ ወደ ስራ



ትምህርት ቤቶች፣ መምህራንና ተማሪዎች የእረፍት ጊዜያቸውን አገባደው ወደ ትምህርት ቤት ስመመለስ በዝግጅት ላይ ናቸው፣

የሚያስገባው በር ላይ ቆሟል።

ከአምናው የትምህርት ቤት ዝግጅት የዘንድሮው የሚለየውም ይሄው የመማሪያ-ማስተማሪያን ስፍራን ምቹና ማራኪ ለማድረግ እየተሰራ ያለው ስራ ነው። ይህ ደግሞ ተማሪዎች ወደትምህርት ቤት ሲመጡ ልዩ ስሜት እንዲፈጥርባቸውና ከአምናው የበለጠ ዘንድሮ በትምህርትቸው ውጤታማ እንዲሆኑ ያስችላቸዋል ተብሎ ይጠበቃል።

እንደ ምክትል ርእሰ መምህሩ ገለፃ ትምህርት ቤቱ ተመራጭ እንደመሆኑ መጠን ዘንድሮ በርካታ አዳዲስ የአፀደ ህፃናት ተማሪዎች ለምዝገባ መጥተው ባሉት ጥቂት ክፍት ቦታዎች እንዲመዘገቡ ተደርጓል። ከነበሩት የቢሮና የማስተማሪያ ክፍሎች በማሸጋሸግና ማቻቻል አንድ ራሱን የቻለና ስልሳ ተማሪዎችን የሚያስተናግድ ክፍል ተዘጋጅቷል። የቦታ ችግር በቀጣይ የሚቀረፍ ከሆነ ደግሞ የትምህርት ቤቱ ተማሪዎችን የመቀበል አቅም ከፍ ይላል። ዘንድሮም የትምህርት ቤቱ ተማሪዎችን የመቀበል አቅም ወደ 991 ከፍ ብሏል። የትምህርት ጥራትን በማሻሻልና ተማሪዎችን በማብቃት ላይ ጠንከር ያለ ስራ በመስራት የከፍተኛ ውጤት ባለቤት ለመሆንም ርብርብ ይደረጋል። ከትምህርት አይነቶችና ይዘቶች አኳያም ዘንድሮ በተወሰኑ የትምህርት አይነቶች ላይ ማሻሻያ ተደርጓል። ለዚህም የአፋን ኦሮሞ ትምህርት አሰጣጥና የሚሰጥባቸው ክፍሎች ተለይተዋል።

ቀደም ባሉት ዓመታት አፋን ኦሮሞ ከ1ኛ እስከ 3ኛ ክፍል ደረጃ ነበር የሚሰጠው። በመጪው አዲስ ዓመት ግን ከ3ኛ እስከ 8ኛ ክፍሎች ድረስ ይሰጣል። ከ3ኛ እስከ 6ኛ ክፍል ደረጃ በሳምንት 3 ክፍለ ጊዜ፣ ለ7ኛ እና 8ኛ ክፍል ደግሞ በሳምንት 2 ክፍለ ጊዜ እንዲሰጥ ከትምህርት ቢሮ በተላለፈ ደብዳቤ ተገልጿል። በዚሁ መሰረትም ትምህርቱ የሚሰጥ ይሆናል። የአፋን ኦሮሞ ትምህርት እንደ አንድ የትምህርት አይነት የሚሰጥ እንደመሆኑ መምህራን ስለሚያስፈልጉ ትምህርት ቤቱ የቅጥር ማስታወቂያ አውጥቶ የአፋን ኦሮሞ መምህራንን በመቅጠር ሂደት ላይ ይገኛል።

ዘንድሮ በትምህርት ቤቱ ውስጥ ሌላም ተጨማሪ ለየት ያለ ነገር ለመስራት የታቀደ ሲሆን ይኸውም ለመምህራን ከፍተኛ የደሞዝ ማሻሻያ ማድረግ ነው። ለመምህራን ከፍተኛ የደሞዝ ጭማሪ ለማድረግ የታሰበውም ዘንድሮ ወላጆች 60 ከመቶ የተማሪ ክፍያ በመጨመራቸው ነው። ጭማሪውም ለውስጥ ስራ፣ ለመምህራንና ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች ደሞዝ ይውላል። ይህም መምህራንና ሰራተኞች በተነቃቃ ስሜት ስራቸውን እንዲሰሩ ያደርጋል። በተማሪዎች በኩልም ከፍተኛ ውጤት እንዲመዘገብ አይነተኛ ሚና ይኖረዋል።

የዳግማዊ ምኒልክ ከፍተኛ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ርእሰ መምህር አቶ ኤፍሬም አይተንፍሱ በበኩላቸው እንደሚናገሩት አንጋፋው የዳግማዊ ምኒልክ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ከፍተኛ ልምድና አቅም ያለው ነው። በትምህርት ቤቱ የመምህራን ቁጥርም ሆነ የትምህርት ጥራት ጥሩ ደረጃ ላይ ይገኛል። ከ80 በመቶ በላይ መምህራን የሁለተኛ ዲግሪ /ኤ ም ኤ/ ባለቤቶች ናቸው። ከዚህ አንፃር የዘንድሮውን የትምህርት ዘመን ለመጀመር ዝግጅቱ ጥሩ ነው።

አጠቃላይ የዘንድሮውን ዓመት የትምህርት ዝግጅት ለመጀመር መርሀ ግብር ወጥቶ እየተሰራ ነው። ከነሀሴ 23 እስከ ጷጉሜ 3 ቀን 2015 ዓ.ም ምዝገባ መካሄድ አለበት በተባለው የግዜ ሰሌዳ መሰረት እየተካሄደ ይገኛል። የዘንድሮውን የምዝገባ ፕሮግራም ከዚህ ቀደም ከነበሩት ለየት የሚያደርገውም ፕሮግራሙ ከተማ አቀፍ በመሆኑ ነው። ዳግማዊ ሚኒልክን ጨምሮ በከተማ አስተዳደሩ ስር ያሉ ትምህርት ቤቶች በሙሉ ምዝገባቸውን የሚያካሂዱት በእነዚህ ቀናት ነው። በዚህ ዓመት የሚካሄደው ምዝገባም በሶፍትዌር የተደገፈ የዳታ ምዝገባ ስርዓትን የተከተለ ነው።

ከዚህ አንፃር የዘንድሮው ምዝገባ እንደ ቀድሞው ጊዜ የተማሪው መማር ላይ ብቻ ያተኮረ አይደለም። ምዝገባው የተማሪውን አጠቃላይ ፕሮፋይል ያካትታል። የቤተሰቡንና የራሱን ሁኔታ፣ ወደ ትምህርት ቤት ሲመጣ ስንት ኪሎ ሜትር እንደሚጓዝ፣ አካላዊ ጤንነቱንና የመሳሰሉትን ጉዳዮችን ሁሉ አካቶ ይይዛል። ሌሎች ተማሪውን የሚመለከቱ መረጃዎችም ይመዘገባሉ። ይኸው የምዝገባ ስርዓት ገና ዘንድሮ ወደ ስራ የገባ ነው።

ርእሰ መምህሩ እንደሚያብራሩት ትምህርት ቤቱ ዘንድሮ ባጠቃላይ 2 ሺህ 200 ተማሪዎች ይኖሩታል። ይህም ከዚህ በፊት ከነበረው በቁጥር ከፍ ያለ ነው። የተማሪ/መምህር ጥምርታ አንድ ለአርባ (1 መምህር ለ40 ተማሪዎች) መሆን እንዳለበት ከግንዛቤ ውስጥ ገብቶ ስራ እየተሰራ ነው። ነገር ግን 2 ሺህ 200 ተማሪ ጥምረቱን ትንሽ ከፍ ስለሚያደርገው እዚህ ላይ ትንሽ መስራት ያስፈልጋል። የመምህራንን ቁጥርም መጨመር ይገባል። እንዲያም ሆኖ ግን ዘንድሮ ያን ያህል የጎላ ችግር አይኖርም። 2 ሺህ 200 ተማሪዎችን በአግባቡ ተቀብሎ ማስተናገድ የሚቻልበት እድል አለ።

ባለፈው ዓመት 561 ተማሪዎች የከፍተኛ ትምህርት ተቋም መግቢያ ፈተና ወስደው 79ኙ ብቻ ዩኒቨርሲቲ ገብተዋል። ይህ እንደ አገር፣ ማለትም ከሌሎች ት/ቤቶች ጋር በንፅፅር ሲታይ፣ ጥሩ ውጤት የሚባል ነው። እንደ ትምህርት ቤት ከታየ ግን ብዙ መስራት ይቀራል። በመሆኑም፣ በዚህ ዓመት ይህንን ቁጥር በመቀየር ከፍ ያለ ውጤት ለማምጣት ስራ እየተሰራ ነው። ከመምህሩ ጀምሮ፣ የትምህርት ክፍሎችና በየደረጃው ያሉት ሁሉ መግባባት ላይ ደርሰው ለ2016 ዓ.ም የትምህርት ዘመን ዝግጅታቸውን አጠናቀዋል።

በቀጣዩ አዲሱ የትምህርት ዘመን አማርኛን በአፍ መፍቻነት የሚማሩ ተማሪዎች አፋን ኦሮሞን በሁለተኛ ቋንቋነት ይማራሉ። አፋን ኦሮሞን በአፍ መፍቻ ቋንቋነት የሚማሩ ተማሪዎች ደግሞ አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት እንዲማሩ ይደረጋል። ይሁንና የትምህርት ቤቱ ዋነኛ ስጋት ምናልባት የአፋን ኦሮሞ ተማሪዎች ቁጥር የሚፈለገውን ያህል ካልሆነ ነው።

በሌላ በኩል ደግሞ ትምህርት ቤቱ እንደተጨማሪ ችግር የሚያየው የመማሪያ-ማስተማሪያ መጻሕፍት እጥረት ወይም አለመኖር ነው። በአሁኑ ግዜም ከፍተኛ የመማሪያ-ማስተማሪያ መፃህፍት እጥረት ይታያል። የህትመት ችግር አለ በሚል መፅሃፎች በፒ ዲ ኤ ፍ የተሰራጩ ነው። ይህም ቢሆን የተሟላ አይደለም። አንዳንዱም ከመሃል ምእራፍ ይጎለዋል። በዚህ መልኩ መፅሃፍቶቹን ለተማሪው ለማድረስም ከፍተኛ ወጪ ይጠይቃል።

ለመጻህፍቱ እጥረት የሚነገረው ወይም የሚሰጠው መልስ ውስብስብና በአብዛኛው ከህትመት ጋር መጨመር ጋር የተያያዘ ነው። ከዚህ ጋር የተያያዙ ችግሮች እንዲፈቱና የመፃህፍት እጥረቱ እንዲቃለል ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ንግግሮች እየተካሄዱ ነው።

እንደ ርእሰ መምህሩ ገለፃ ይህንን ትምህርት ቤቱን ለማሻሻል በርካታ የህብረተሰብ ክፍሎች ይሳተፋሉ። ትምህርት ቤቱን ለማሻሻል የቀድሞ የትምህርት ቤቱ ተማሪዎች፤ ማህበረሰቡ፣ የተማሪ ወላጆች፣ እራሳቸው ተማሪዎችና አስተማሪዎች ሲሳተፉ ቆይተዋል። ተሳትፏቸው አሁንም ቀጥሏል። የተማሪ ወላጆችም የልማት ክፍያ በመፈፀም ለትምህርት ቤቱ ያላቸውን አጋርነት እያሳዩ ይገኛሉ። ይህም የሚሆነው መንግስት ሁሉንም ነገር ለብቻው ማሟላት ስለማይችል ነው። ለዚህም ነው ህብረተሰቡ በዚህ ተግባር አምኖ ገንዘብ እያዋጣ ያለው። የተሻለ ተቋም ለመጪው ትውልድ ማስተላለፍ የሚገባ መሆኑን ስለተገነዘበ ነው በትምህርት ቤት ልማት የሚሳተፈው።

የክረምቱ ወቅት አልፎ ወደ በጋው እየመጣ ነው። ተማሪውም የእረፍት ጊዜውን አገባዶ ወደ ትምህርት ቤት ለመግባት በዝግጅት ላይ ነው። በተመሳሳይ ትምህርት ቤቶችም ዝግጅታቸውን እያጠናቀቁና ተማሪዎቻቸውን ከደጅ ለመቀበል አቆብቁበው እየተጠባበቁ ይገኛሉ። መስከረም ሁሉንም በሠላም ያጨባብጣቸው ዘንድ ደግሞ የሁሉም ሰው ምኞች ነው። መልካም አዲስ ዓመት!!

# ‹‹አሁን የተከሰተው የአንበጣ መንጋ የዛሬ ሶስት ዓመት ከተከሰተው ጋር የሚነጻጸር አይደለም ››



*-አቶ ፈለገ ኤሊያስ -*

*የምስራቅ አፍሪካ የበርሃ አንበጣ መከላከያ ድርጅት ከፍተኛ ባለሙያ*

<u>እፀገነት አክሊሉ</u>

**አንድ ጎልማሳ የበርሃ አንበጣ በየቀኑ የራሱን ክብደት ያህል ማለትም ሁለት ግራም ምግብ የሚበላ ሲሆን፣ አማካይ ብዛት ያለው የበርሃ አንበጣ መንጋ ደግሞ የ10 ዝሆኖች ወይም የ25 ግመሎች ወይም 25 ሺህ ሰዎች በቀን ውስጥ የሚመገቡትን ምግብ ይጨርሳል። በወረርሽኝ ወቅት የበርሃ አንበጣ መንጋ እስከ 29 ሚሊየን ካሬ ኪሎ ሜትር የሚሸፍን ሰፊ መሬት በመያዝ ወደ 60 ሀገራት ውስጥ የመሰራጨት አቅም አለው እንዳለው የዓለም ምግብ እና እርሻ ድርጅት መረጃ ያመላክታል ። ይህም የዓለማችን 20 በመቶ መሬት ማለት ሲሆን፣ የዓለማችንን 10 በመቶ ሕዝብ ኑሮ ያስተጓጉላሉ እንደማለትም ነው።**

**ሴት የበርሃ አንበጣ ከ95 እስከ 158 እንቅሏል የምትጥል ሲሆን የበርሃ አንበጣ መንጋ በነፋስ እየታገዘ በሰዓት ከ16 እስከ 19 ኪሎ ሜትር ሲጓዝ የሚችል ነው፣ በአንድ ቀን ውስጥ ብቻ ከ5 እስከ 130 ኪሎ ሜትር መጓዝ ይችላል።**

**በአንድ ካሬ ኪሎ ሜትር ስፋት ባለው መሬት ላይ የበርሃ አንበጣ መንጋ ውስጥ ከ40እስከ 80 ሚሊዮን የሚገመቱ አንበጣዎች ይገኛሉ። የበርሃ አንበጣ መንጋ በአየር ሁኔታ እና ሥነ ምኅዳር ላይ መሠረት በማድረግ ከሦስት እስከ አምስት ወራት በሕይወት መቆየት ይችላል።**

**እ.ኤ.አ እስከ 1921 ድረስ ሁለት ዓይነት የበርሃ አንበጣ መንጋ ዝርያዎች ብቻ የነበሩ ቢሆንም አሁን ላይ የአፍሪካ፣ የሩቅ ምሥራቅ፣ ቀይ የምሥራቅ አፍሪካ፣ ቡናማ የደቡብ አፍሪካ፣ የሞሮኮ፣ የቦምቤይ፣ የአውስትራሊያ እና የዛፍ የሚባሉ ክፍፍሎች አሳቸው።**

**የበርሃ አንበጣ መንጋ አጭር ቀንድ መሰል ነገር የያዙ በደርዘኖች የሚቆጠሩ ዝርያዎች አሉት። የበረኃ አንበጦች በዓመት ከ200 ሚሊ ሜትር በታች ዝናብ በሚያገኙ ከፊል ደረቅ እና ደረቃማ የአፍሪካ ክፍሎች፣ መካከለኛው ምሥራቅ እና ደቡብ ምዕራብ እስያ ውስጥ የሚገኙ ሲሆን፣ ይህም አካባቢ በድምሩ 16 ሚሊዮን ካሬ ኪሎ ሜትር ስፋት ያለው መሬት እና 30 አገራት የሚያካትት ነው።**

**የአንበጣ መንጋን ለመበተን ከሚያስችሉ ዘዴዎች መካከል በጎን በኩል ሆኖ ማባረር፣ የአንበጣ መንጋ አንድን አካባቢ ሲለቅ የሚችለው የመንጋውን ሥርዓት እንዲዘበራረቅ በማድረግ ነው። የአንበጣ መንጋን ከኋላ ሆኖ ማባረር እንደማይጠቅም ጥናቶች አረጋግጠዋል። በመሆኑም ከጎን በኩል በመግባት የመንጋውን ሥርዓት ማዛባትና ክፍፍል መፍጠር መንጋው በቀላሉ አንድን አካባቢ እንዲለቅ ለማድረግ ያግዛል። ከጀርባ ለማባረር መሞከር እንደ መንዳት ይቆጠራል ጠቀሜታው ዝቅተኛ ነው።**

**ሌላው ከፍተኛ ድምፅ ማሰማት ሲሆን የአንበጣን መንጋ ከፍተኛ ድምፅ ያስበረግገዋል። በመሆኑም የጥይት ድምፅ፣ ጥሩንባ እና ጩኸት ማሰማት ጠቃሚ ናቸው። ጎማ ማቃጠል ምንም እንኳን ከአካባቢ ብክለት አንፃር የሚመከር ባይሆንም ጎማ ማቃጠል ግን የአንበጣን መንጋ እንደሚያስበረግግ ጥናቶች ያሳያሉ።**

**ሌላው ፀረ-ተባይ መድሃኒቶችን መጠቀም ነው፤ ከላይ ከተጠቀሱት ባህላዊ የመከላከያ እርምጃዎች በተጨማሪ በሰው አቅም፣ በመኪና እና በአውሮፕላን የሚረጩ ፀረ-ተባይ ኬሚካሎችን መጠቀም ሳይንሳዊ አማራጭ ነው::**

**እኛም ካለፉት ሶስት ዓመት ወዲህ ሀገራችን ላይ መለስ ቀለስ የሚለው የበርሃ አንበጣ መንጋ በሰብል ላይ ከፍ ያለ ጉዳትን እያስከተለ መሆኑን በመገንዘብ ጉዳዩ በቀጥታ የሚመለከተው የምስራቅ አፍሪካ የበርሃ አንበጣ መከላከያ ደርጅት ምን እየሰራ ነው? ስንል በድርጅቱ የመረጃና ትንበያ ከፍተኛ ባለሙያ ከሆኑት አቶ ፈለገ ኤልያስ ጋር ቆይታን አድርገናል።**

**አዲስ ዘመን፡- የምስራቅ አፍሪካ የበርሃ አንበጣ መከላከያ ድርጅት ዋና የስራ ኃላፊነቱ ምንድን ነው? ከሚለው እንነሳ፤**

**አቶ ኤልያስ፡-** የምስራቅ አፍሪካ የበርሃ አንበጣ መከላከያ ድርጅት እኤአ በ1962 በዘጠኝ አባል አገራት የተመሰረተ ድርጅት ነው። እነዚህ አባል አገራትም ኤርትራ፤ ጅቡቲ፤ ኢትዮጵያ፤ ኬንያ፤ ደቡብ ሱዳን፤ ሱዳን፤ ሶማሊያ፤ ታንዛኒያና ኡጋንዳ ናቸው።

ድርጅቱ ለመቋቋሙም ዋናው ምክንያት የበርሃ አንበጣ በአንድ ቦታ ተወስኖ የማይቆም፤ ከሀገር ሀገር የሚዞር ድንበር የማያግደው በመሆኑና ይህንን ለመቋቋም የተመሰረተ ድርጅት ነው። ድርጅቱ የሚሰራቸው ስራዎችም በዋናነት የበርሃ አንበጣን መከላከል ቢሆንም አንበጣ የሚከሰተው ግን ሁለት አልያም ሶስት ዓመታትን እየቆየ በመሆኑ በተጓዳኝ ለምን ሌሎች ጸረ ሰብል የሆኑ ተባዮችን አካቶ አይሰራም በሚል የግሪሳ ወፍን፣ ተምችን እንዲሁም ጳጳፍላይን በመሳሰሉት ተውሳኮች ላይ እንዲሰራ ኃላፊነት ተሰጥቶታል።

ዋናው ስራውን እነዚህ ፀረ ሰብል የሆኑ አካላትን በአየር ላይ የማሰስና የመከላከል ስራ ሲሆን ይህንን ተግባር የሚያከናውንባቸው አውሮፕላኖች አሉት፤ ምንም እንኳን እነዚህ አውሮፕላኖች አሮጌ ቢሆኑም በዘንድሮ ዓመት ግን አንድ አዲስ አውሮፕላን ለማግኘት ተሞክሯል።

ሌላው ድርጅቱ የምርምር ስራን ይሰራል፤ ይህ ማለትም እነዚህ ጸረ ተባዮች አካባቢ ላይም ጉዳት ስለሚያደርሱ አማራጭ የሚሆኑ ጸረ ተባዮችን መፈለግ ነው። በዚህም ስነ ህይወታዊ የመከላከል ዘዴ በሚባለው ምርምር ተሰርቶ ብዙ ውጤት ተገኝቶበት ጥቅም ላይ ውሏል።

መረጃን የመሰብሰብ፤ ከዛም የመተንተንና ትንበያን የመስጠት ስራ አባል ሀገራት ላይ ያሉ ተዛማጅ ተባዮችን ያሉበትን ደረጃ የሚገልጽ ሪፖርት በየጊዜው ይሰበሰባል የተሰበሰቡት መረጃዎች ይታያሉ፤ ወደፊት ምን ሊሆን እንደሚችል የመተንበይና ቅድመ ማስጠንቀቂያ የሚያስፈልግበት ቦታ ላይ ማስጠንቀቂያ እንሰጣለን።

ሌላው የድርጅቱ ስራ የሰው ኃይልን የማብቃት ስራ ሲሆን በዚህም ለባለሙያዎች ስልጠናዎችን መስጠት ነው። በአባል አገራት ላይ ያሉ የእጽዋት ጥበቃ ባለሙያዎች የተዛማጅ ተባዮችን እንዴት መከታተልና መቆጣጠር ይቻላል በሚለው ላይ የንድፈ ሃሳብና የተግባር ስልጠናውን በመስጠት የአባል ሀገራት አቅም እንዲጠናከር ይሰራል።

**አዲስ ዘመን፡- በአባል ሀገራት መካከል ያለው ግንኙነትና የመረጃ ልውውጥ እንዴት ይገለጻል?**

**አቶ ኤልያስ፡-** እነዚህ አባል ሀገራት ችግሩን በጋራ እንከላከል ለዚህ ደግሞ አንድ ድርጅት እናቋቁም ብለው ወደውና ፈቅደው ያቋቋሙት ነው። ድርጅቱም በዩናይትድ ኔሽን የተመዘገበ ነው፤ አባላቱም በየዓመቱ ስብሰባ ያደርጋሉ፡፡ በተለይም የእጽዋት ጥበቃ ዳይሬክተሮች ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ የሆኑበት እንዲሁም ሚኒስትሮቹ በሚኒስትር ካውንስል ደረጃ የሚሰበሰቡበት፤ በዚህም ስራዎች የሚገመገሙበት እቅድ የሚጸድቅበት አንዳንድ ትልልቅ ውሳኔዎችም የሚሰወኑበት ነው።

ከዓመት ወዲህ ደግሞ በየጊዜው እነዚህ አገራት ከመረጃ መስጠትና መቀበል እንዲሁም ድርጅቱ ስራውን እንዲቀጥል መዋጮቻቸውን ከመክፈል አንጻር ተሳታፊ ናቸው። በመሆኑም አባል አገራት ድርጅቱ በሁለት እግሩ ቆሞ እስከ አሁን ድረስ እንዲቀጥል ትልቅ ሚና ተጫውተዋል ማለት ይቻላል። ነገር ግን እነዚህ አባል ሀገራት ዓመታዊ መዋጮን ማጓተት አንዳንድ ጊዜም አለመክፈል የሚታይባቸው መሆኑ ደግሞ ተቋሙ ከዚህ በላይ እንዳያድግና የተጣለበትን ኃላፊነት በሚገባ እንዳይወጣ ተግዳሮት ይሆናል።

ተዛማጅ ተባዮች ድንበር ዘለል ከመሆናቸው አንጻር አንድ ሀገር ብቻዬን እቆጣጠረዋለሁ ቢል የሚሆን አይደለም። በመሆኑም ኢትዮጵያ ላይ መቆጣጠር ካልተቻለ ኬንያ ትወረራለች፤ በተመሳሳይ ኬንያ ላይ ማቆም ካልተቻለ ኡጋንዳ ታንዛንያ ከፍ ያለ ወረራ ይደረግባቸዋል።

ለምሳሌ እኤአ ከ2019 እስከ 2020 ድረስ ያለው የአንበጣ ወረርሽኝ ኢትዮጵያ ውስጥ እያለ በተቻለ መጠን ቁጥጥር ቢደረግበት ኖሮ ወደ ሌሎች ሀገራት ባልተዛመተ ነበር፡፡ ወደ ኢትዮጵያም የገባው በሌሎች ሀገራት ቁጥጥር ባለመደረጉ ነው፡፡ ከተባባሰም በኋላ የቁጥጥር ስራው ጠንካራ ቢሆን ኖሮ ጉዳቱን መቀነስ ይቻል ነበር። እዚህ ላይ ግን መቆጣጠር አቅቶን ሳይሆን የመጣበት መጠን በጣም ከፍተኛ በመሆኑ ኢትዮጵያን ሁሉ አልፎ ሊሄድ ችሏል።

እዚህ ላይ እንግዲህ እኤአ በ2019 አንበጣ አዲስ አበባ ድረስ የደረሰበት ሁኔታ እንደነበር የምናስታውሰው ነው፤ በወቅቱ ግን እዚሁ እንዳይወጣ የተጠናከረ የቁጥጠር ስራ በመሰራቱ የትም ሳይወጣና ወደሌሎች አገሮች ሳይዛመት መግታት ተችሏል።

ኬንያ ኡጋንዳ ላለፉት 70 ዓመታት አንበጣን አይተው አያውቁም፤ ይህ የሆነውም ጠንካራ የመከላከል ስራ በመሰራቱ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- እነዚህ ሁለት ሀገራት 70 ዓመታት ያህል አንበጣ ካላዩ ማጥፋት ይቻላል ማለት ነው?**

**አቶ ኤልያስ፡-** በመጀመሪያ ደረጃ አንበጣን ሙሉ በሙሉ ማጥፋት አንችልም። ምክንያቱም አንድ ወይንም ሁሉት አንበጣ እንኳን ቢቀር የመራባት መጠኑ በጣም ከፍተኛ ነው። ሌላው ደግሞ ለመራባት በጣም ፈጣንና በብዛት የሚራባ ነው።

የበርሃ አንበጣ የሚባሉት የሚራቡበት አካባቢ በጣም ወጣ ያለ ሪሞት አካባቢ ነው። ለመራቢያ የሚመርጡት የቀይ ባህር ዳርቻዎችን ሲሆን ቦታዎቹም በጣም ብዙ ናቸው። ይህንን ስናይ አንበጣን የመከላከል ስራው በጣም አድካሚ ይሆናል።

ነገር ግን አሁን ላይ የብዙ ዓመት የመከላከል ልምድ ተቀምሮ የተደረሰበት ነገር ቢኖር በጥሩ የመስክ አሰሳ ገና ሳይራባ ቦታ ይዞ እንዳለ ማግኘትና እዛው ላይ የመከላከል ስራን መስራት ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ኢትዮጵያ ውስጥ ደግሞ አንበጣ በተደጋጋሚ እየተከሰተ ነው፤ የመከላከል ስራችን ደካማ ስለሆነ ይሆን?**

ወደ ገጽ 11 ዞሯል

# ‹‹አሁን የተከሰተው የአንበጣ መንጋ...

ከ ገጽ 10 የዞረ

**አቶ ኤልያስ፡-** ኢትዮጵያ ውስጥ በተለይም እኤአ በ2019 የመጣው አንበጣ ሁላችሁም እንደምትረዱት የመን ላይ የነበረው ሁኔታ በጣም መጥፎ የነበረ በመሆኑ በወቅቱ አሰሳ እንኳን ማድረግ አልተቻለም፡፡ በዚህም ከየመን ተነስቶ ወደ ኢትዮጵያ የገባው የአንበጣ መንጋ በጣም ብዙ ነበር።

በአፋር ክልል ላይ 32 ወረዳዎች ከየመን በመጣ አንበጣ ተወረው ነበር። በጣም የሚገርመው ደግሞ የመጣው አንበጣ እንቁላል ለመጣል የደረሰም በመሆኑ ሁሉም እንቁላል ጣለ። ይህንን በገፍ እንቁላል የጣለን አንበጣ የመከላከል ስራው ቢሰራም እንኳን ከአቅም በላይ ነበር።

በሌላም በኩል በዚህን ያህል ደረጃ ይከሰታል ተብሎም ስላልታሰበ በድርጅታችንም ሆነ በግብርና ሚኒስቴር በኩል የነበረው ዝግጁነት ብዙም ስላልነበር ከተፈጠረ በኋላ የተደረገው ርብርብ ውጤታማ አልሆነም።

እዚህ ላይ አንበጣ የሚዛመትባቸው ደረጃዎች አሉ፡፡ አንዱ በትንሽ ቦታ ላይ ለአጭር ጊዜ የሚነሳ ሲሆን ከአንድ ክልል ወደሌላ ክልል የሚተላለፍም ብቻ ነው። ሌላው ደግሞ ሁለት ወይም ሶስት አገሮችን ሊይዝ የሚችል ሲሆን ይህ እዚህ ብቻ የሆነ ሳይሆን ምዕራብ አፍሪካም ላይ እኤአ ከ 2003 እስከ 2005 ድረስ በጣም ከፍተኛ ወረርሽኝ ነበር። በጣም ብዙ ድካምም ጠይቋል፡፡ ነገር ግን ይህ ሁልጊዜ ይሆናልም ማለት ደግሞ አይደለም። ምንጩ የትኛው ቦታ ላይ እንደሆነ ያልታወቀ አንበጣ በአንድ ጊዜ በሚፈለፈልበት ወቅት የመባዛቱና በፍጥነት የመኳዙ ሁኔታ እንደዚህ ዓይነት ነገሮችን ይፈጥራል።

**አዲስ ዘመን፡- አሁን ላይ አገራችን ውስጥ የተፈጠረው አንበጣም ከአቅም በላይ ሆኖ ነው ወይስ ምክንያቱም ምንድን ነው?**

**አቶ ኤልያስ፡-** አሁን የተፈጠረው የአንበጣ ወረርሽኝ በኤርትራ ቀይ ባህር ላይ የተራባ አንበጣ ወደ ምዕራብ ኤርትራ በመምጣት ላይ ይገኛል፤ ምክንያ ቱ ደግሞ ሞቃታማና ደረቅ መሆኑ ነው። ሆኖም በአሁኑ ወቅት አንዱ ወይም ሁለቱ ነው ወደ ኢትዮጵያ የገባው እንጂ ኢትዮጵያ ላይ የተፈለፈለም ሆነ የተራባ አንበጣ አይደለም።

ምናልባት ሰዎች ግን አገራችን ላይ ተራብቶና ተፈልፍሎ የተከሰተ ሊመስላቸውና እንደዛም ሊሉ ይችላሉ፤ ነገር ግን አንበጣ እንቁላል ለመጣል ሁለት ሳምንት ከዛም በኩብኩባ ደረጃ ሆኖ ስድስት ሳምንት ይፈልጋል፤ አድጎ ለጥፋት ለመድረስ ሁለት ወር ያህል ይወስድበታል። ይህንን ስናይ ደግሞ አሁን ያለው አንበጣ በፍጹም ኢትዮጵያ ውስጥ ያልተፈለፈለ መሆኑን እኛም አረጋግጠናል።

ሌላው የንፋስ አቅጣጫ ከኤርትራ ወደ ኢትዮጵያ ስለነበር በአዲግራት እና በኮረም በኩል ወደ ደቡብ ምስራቅ ትግራይ ከገባ በኋላ አፋር ላይ ሙቀትና ምቹ ሁኔታ ስለነበር በዛ አካባቢ ሲዘዋወር የቆየ አንበጣ ነው። ይህ ትግራይ ላይ ያለው አንበጣ ራሱ ተበታትኖ አሁን ላይ በአማራና አፋር ክልል ላይ እንዳለ ነው ሪፖርቶች የሚያሳዩን።

በመሆኑም ይህንን የአንበጣ መንጋ ከዛሬ ሶስት ዓመቱ ጋር ማወዳደር በጣም ከባድ ነው። ምክንያቱም ያለፈው ዓመት በጣም ብዙና ከባድ ወድመትን ያስከተለ ነው የአሁኑ ግን በጣም በተበታተነ መልኩና መጠኑም ትንሽ ሆኖ የመጣ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- እኤአ በ2019 ዓ.ም ሆነ አሁን ላይ የተከሰተውን አንበጣ እንደ ኢትዮጵያ ለመቆጣጠር ድርጅታችሁ ምን ዓይነት ተግባራትን እያከናወነ ነው?**

**አቶ ኤልያስ፡-** በመሰረቱ እንደ ድርጅት በአባላት አገሮች፤ ትኩረት የሚሰጣቸውም ኢትዮጵያ ሱዳን ኤርትራና ሶማሊያ ናቸው። ከዚህ አንጻር አንበጣ የት አካባቢ ነው ያለው? የሚለው ይታያል፡፡ ለምሳሌ በሱዳንና ኤርትራ በፈረንጆች ሀምሌ ወር መጨረሻ ድረስ አንጠባ ተከስቷል፤ በእነዚህ አካባቢዎችም የመከላከል ስራ ተሰርቶ ጥሩ ውጤት ተመዝግቧል። ለምሳሌ ኤርትራ 1 ሺ 192 ሄክታር አካባቢ መከላከል ተችሏል። ይህ የሚያሳየው ደግሞ በአሁኑ ወቅት ከኤርትራ ይመጣል ተብሎ ስጋት ሊሆን የሚችል አንበጣ አለመኖሩን ነው።

ሱዳን አሁን ላይ አለመረጋጋት ውስጥ ብትሆንም እንኳን 849 ሄክታር አንበጣን የመከላከል ስራ ተሰርቷል። በኢትዮጵያም በያዝነው ወር የመከላከል ስራው ተጀምሯል። በዚህም 732 ሄክታር መሬት ላይ መድሃኒት ርጭት ተደርጎ የመከላከል ስራ ተሰርቷል።

ድርጅቱም አባል አገራት በሚጠይቁት ጥያቄ መሰረት የሚሰራ እንደመሆኑ ጥያቄ በቀረበ ቁጥር የመከላከል ስራው ላይ እንሰማራለን። ሁሉም ሊገነዘበው የሚገባው ነገር ግን እኛ የስራውን ባለቤት ግብርና ሚኒስቴርን እንደግፋለን እንጂ እንደ ባለቤት ተሳትፎ ልናደርግ አንችልም። ነገር ግን የእኛ እርዳታ በሚያስፈልግበትና ጥያቄ በምንጠየቅበት ወቅት ወዲያውኑ ምላሽ ለመስጠት እንዘጋጃለን።

**አዲስ ዘመን፡- እንደው የአሰሳ ስራው ምን መልክ ነበረው (ምን ያህል ታሰሰ) እንዲሁም ምን ያህል ቦታ ላይ አንበጣ ታየ?**

**አቶ ኤልያስ፡-** አዎ ይህንን የሚያሳይ ቁጥር አለ። በአጠቃላይም እንደ አገር አፋር ትግራይና አማራ ላይ ነበር የታየው፡፡ አሁን በቅርቡ ግን ምስራቅ ሀረርጌ ላይ ስለመታየቱ ሪፖርት ደርሶናል። ይህንንም የማጣራት ስራውን የግብርና ሚኒስቴር የእጽዋት ጥበቃ ክፍል እየሰራ ነው።

ድርጅቱ ምላሽ በሚሰጥበት ጊዜም አንደኛ ቴክኒካል ኮሚቴው ሁኔታው ምን ይመስላል፤ መቆጣጠር የሚቻለው በምን መንገድ ነው፤ ለመቆጣጠርስ ምን ያስፈልጋል፤ ለአሰሳ ምን ያስፈልጋል፤ ቴክኒካል ድጋፉ ለምሳሌ ሎጂስቲክስ እንዴት ነው የሚቀርበው የሚለውን ከተወያየ በኋላ ምክረ ሃሳቡን ለውሳኔ ሰጪዎች አቅርቧል።

በዚህም መሰረት አሁን በኮሚቴው ውሳኔ መሰረት የአውሮፕላን አስፈላጊነት በጣም ስለተሰመረበትና በአጋጣሚም የድርጅቱ አውሮፕላኖች አዲስ አበባ ላይ ስለነበሩ አብራሪዎችን ከናይሮቢ በማስመጣት አንድ አውሮፕላን ኮምቦልቻ ላይ ቆሞ የአሰሳ ስራውን ጀምሯል።

**አዲስ ዘመን፡- ከአባል አገራት ጥሪ ካልቀረበ ድርጅቱ በራሱ መንገድ አንበጣን ለማጥፋት ስምሪት አያደርግም ማለት ነው?**

**አቶ ኤልያስ፡-** ስራው የየሃገራቱ የግብርና ሚኒስቴር ስራ ነው። ነገር ግን ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በዚህን ጊዜና ሰዓት እርዳታ አድርጉልኝ ብሎ ይጠይቃል። ይህ ደግሞ በኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን ሁሉም አባል አገራት ላይ የሚሰራበት አካሄድ ነው። በነገራችን ላይ ይህ አሰራር አንበጣን ብቻ የሚመለከት ሳይሆን ወፍም ሲመጣ አካሄዱ ተመሳሳይ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ከላይ እንደገለጹት በአሁኑ ወቅት 732 ሄክታር መሬት ላይ መድሃኒት ርጭት ተደርጓል ይህ ከምን ያህል ሄክታር ነው በሌላ በኩል ደግሞ አንበጣ በአገራችን ላይ ቢስፋፋ የመከላከል አቅም አለ?**

**አቶ ኤልያስ፡-** ያለፈው የአንበጣ ወረርሽኝ ብዙ ነገሮችን አስተምሮናል። አንደኛ ቅድመ ጥንቃቄ ስራ ላይ ምን መደረግ እንዳለበት፣ ሁለተኛ መቼና የት የመከላከል ስራ መሰራት እንዳለበት ? ምን እንደሚያስፈልግ በደንብ ተምረንበታል።

በዚህ መሰረት አሁን እየታየ ያለው የአንበጣ ወረርሽኝ ከአቅም በላይ የሚሆን አይደለም፤ ቢሆንም ግን የግብርና ሚኒስቴር ከዚህ ቀደም የቀረቡት በቂ የመገልገያ ግብዓቶች አሉት፤ 5 አውሮፕላኖችን ገዝቷል፤ የእኛ ድርጅትም በፋኦ በኩል አዲስ አውሮፕላን አግኝቷል። ይህ አቅምን ከመገንባት አንጻር ጥሩ ማሳያ ነው።

አሁን አንበጣው የት ነው የሚራባው? ቀጣዩ ሁኔታስ ምንድን ነው? የሚለውን አይቶን ቴክኒካል ኮሚቴው ምክረ ሀሳብ አስቀምጧል። በዚህም አፋር ሸለቋማ ቦታዎች ላይ ሊኖር ይችላል በሚል ልየታ ስላለ አካባቢውን የማጥናት ህብረተሰቡ የአንበጣውን በቀለም ለይቶ አውቆ ሲታይ ወዲያውኑ ሪፖርት እንዲያደርግ የማሳወቅ ስራም በመሰራት ላይ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ስራውን በውጤታማነት ለማከናወን እየገጠማችሁ ያለው ችግር ምንድን ነው?**

**አቶ ኤልያስ፡-** አንዱ ቅድም ከላይ የገለጽኩት የአባል ሀገራት በወቅቱ መዋጮ አለመክፈላቸው ነው፡፡ ሌላው አውሮፕላን ለማስነሳት እራሱ የሀገራት ፍቃድ ያስፈልጋል። ሌላው ከጸጥታ አኳያ ያለው ነገር እንደልብ በየቦታው ተንቀሳቅሶ የአሰሳ ስራን ለመስራት አስቻይ ባለመሆኑ በተለይም በአማራ ክልል ያለው ኮማንድ ፖስት ይህንን ማመቻቸት ይኖርበታል። በአፋር ክልል ብዙ የመንግስት ስትራክተሮች ባለመኖራቸው የፌደራል ባለሙያዎች በሙሉ በክላስተር ተደራጅተው እንዲሰሩ ሆኗል።

ትግራይ ላይ እራሳቸው አደራጅተው ባለሙያዎች አሰማርተዋል። በነገራች ላይ አሁን ትግራይ ላይ አንበጣ የለም። ትግራይም አማራ ላይም ያለው በሙሉ ወደ አፋር ክልል ነው የሚሄደው ምክንያቱም የትግራይና የአማራ ክልል ተራራማ ቦታዎች ለመራቢያ ምቹ አይሆኑለትም፡፡ በመሆኑም የአፋር ሸለቋማ ቦታዎችን ተመራጭ ያደርጋል።

**አዲስ ዘመን ፡- እንደ አገር አንበጣም ለዘለቄታው ለማስቀረት ምን መሰራት አለበት ይላሉ?**

**አቶ ኤልያስ፡-** ከመጣ በኋላ መጮህ ሳይሆን መጀመሪያ አስፈላጊ የሆኑ የዝግጅት ስራዎችን መስራት ይገባል፤ ይህ ስራ ደግሞ በጣም በአስቸጋሪ ጊዜ ሊመጣ ይችላል የሚለውን ከግንዛቤ አስገብቶ መሰራት ያለበት ጉዳይ ነው። ምክንያቱም አንበጣ ቢመጣ ምን አለኝ? ምን ማድረግ እችላለሁ? የሚለውን ሰርቶ ማስቀመጥ ይገባል። ስራው ግን አንድ ሚኒስትር መስሪያ ቤት ብቻ ሊሰራው የሚችል አይደለም። ብዙ ባለድርሻ አካላት አሉ፡፡ በተለይም የዓለም የምግብና እርሻ ድርጅት፣ የምስራቅ አፍሪካ የበርሃ አንበጣ መከላከያ ድርጅት እንዲሁም ዩኤስ ኤይድ ይሳተፉበታል።

ሌላው ወቅታዊና ቶሎ ቶሎ የሚሆን የመስክ አሰሳን ማድረግ በጣም አስፈላጊ ነው። ይህንን ማድረግ ሲቻል ችግሩ ስር ሳይሰድ ማግኘት ያስችላል። በጊዜ ተገኘ ማለት ደግሞ የመከላከል ስራውንም ውጤታማ ያደርገዋል። በተጨማሪም ለባለሙያዎች ተከታታይ የሆኑ የአቅም ግንባታ ስልጠናዎችን መስጠት ያስፈልጋል። እነዚህን ነገሮች በቅንጅት መስራት ከተቻለ በእርግጠኝነት አንበጣን የመከላከል ስራው በጣም ቀላል ይሆናል።

**አዲስ ዘመን ፡- ስለነበረን ቆይታ በጣም አመሰግናለሁ።**

**አቶ ኤልያስ፡-** እኔም አመሰግናለሁ



ስፖርት እና መዝናኛ

# ፋሽን

## የሀገር ባሕል አልባሳትን ለአዘቦት ቀናት ጭምር

**ወርቅነሽ ደምሰው**

ኢትዮጵያውያንን ልብን ለሁለት ስንጥቅ የሚያደርጉ ውብና ማራኪ የሀገር ባሕል አልባሳት ባለቤቶች ናቸው።ይህም በተለይ በበዓላት ወቅት የምንመለከተው ሀቅ ነው።ከበአላት ውጪም የእነዚህ የባህል አልባሳት ተፈላጊነት በተለይ በሰርግ ላይ እየተፈለጉ ያለበት ሁኔታ አልባሳቱ ከመቼውም ጊዜ በላይ ተፈላጊነታቸው እየጨመረ እንዲመጣ እያደረገ ይገኛል።

ምክንያቱ ደግሞ የልብሶቹ ዲዛይን፣ ቀለም፣ ውበታቸው እና ለለባሽ ምቹ ተደርገው እየተዘጋጁ ያለበት ሁኔታ ነው።ቀልብን የሚስቡት እነኝህ አልባሳት ቀደም ሲል በባሕላዊ ዘዴ ብቻ ተሰርተው ሲለበሱ የኖሩ ቢሆንም፣ ለዲዛይነሮቻችን ምስጋና ይግባቸውና አሁን ባሕላዊ ይዘታቸውን ሳይለቁ እየዘመኑ የዘወትር ልብስ እንዲሆኑ ጭምር ተደርገው እየተመረቱ ይገኛሉ።

አልባሳቱ የሀገራችን ቱባ ባህል በቀላሉ ተመንዝሮ የማያልቅ ለመሆኑ ነጋሪ የማይሻው ሕያው ምስክሮች ናቸውም።እንዲህ ከዘመኑ ጋር አብረው የሚሄዱትን ልብሶች የሚያዘምኑትም የሀገራችን ዲዛይነሮች እየተበራከቱ መጥተዋል። ከዲዛይነሮቹ መካከል አንዷ ደግሞ የዛሬው ባለታሪካችን ዲዛይነር ደስታ እሸቱ ናት። ዲዛይነሯ ወደ ዲዛይን ሙያ ከገባች 14 ዓመታትን አስቆጥራለች።

ዲዛይነር ደስታ እንደምትለው፤ ቀደም ሲል ወደዚህ ሙያ ከመግባቷ በፊት በጸጉር ሙያ ላይ ትሰራ ነበር።የዲዛይኒንግ ሙያ ውስጣዊ ፍላጎቷ ስለነበረ ሙያውን ለመማር ወስና የዲዛይኒንግ ትምህርቷን በቴክኒክና ሙያ ተቋማትም ተከታትላለች።ትምህርቷንም እንዳጠናቀቀች ነው በቀጥታ ወደ ሥራ የተሰማራችው።

ከሌሎች ባለሙያዎች ጋር በመደራጀት ነው በተሰ ጣቸው መስሪያ ቦታ (ሼድ) ውስጥ ሥራዋን አሃዱ ብላ የጀመረችው።በጊዜው ሁኔታዎች አስቸጋሪ ሆነውባት ነበር። በዚህ መልኩ መስራት ውጤታማ እንደማያደርጋትም ውስጧ ያሳምናታል።እናም ጥቂት ጊዜያትን ከሰራች በኋላ ለሥራዋ አመቺ የሆነ ቦታ ቀየረች።በራሷ ጥልፍ፣ ስፌትና ዲዛይን መሥራትም ጀመረች።የሀገር ባሕል ልብሶችን ዲዛይን ወደማድረጉም ገባች።

በራሷ ፍላጎት የምታሸምናቸው ልብሶች እንዳሏት ሁሉ ከሸማኔዎችና አንዳንዴም ከገበያ የምትገዛቸው ልብሶች መኖራቸውንም ትናገራለች። በእንዲህ አይነት መንገድ የምታገኘውን ልብስ ዲዛይን በማድረግ፣ ስፌትና ጥልፉን በመስራት ለተጠቃሚዎች ታቀርባለች። በዚህ ሁኔታ መስራት ከጀመረች ስምንት ዓመታት አስቆጥራለች። አሁን ላይ የሸመናው ሥራውን ብቻ ለሸማኔዎች ሰጥታ የተቀሩትን ስራዎች ራሷ ናት የምትሰራቸው።

ባህላዊ ይዘታቸውን የጠበቁ ለሥራ የሚለበሱ፤ ለአለባበስ የሚመቹ ልብሶችን ዲዛይን አድርጋ ትሰራለች። እነዚህ አልባሳት ሲሰሩ ውብና ማራኪ እንዲሆኑ ታስቦባቸው ዲዛይን የሚደረጉ ናቸውም።ልብሶቹን ለመስራት ምንም አይነት የፋብሪካ ምርቶች አትጠቀምም።ለባሹ ፈልጎትና ወዶት የሚለብሰው አይነት ልብስ ለመስራት ጥረት ታደርጋለች።

የልብሶቹን ሽመና በተመለከተ ስትናገር ልብሶቹ የተለያዩ ዲዛይኖችን በመጠቀም እንዲያምሩ ተደርገው ይሰራሉ። እነዚህ ልብሶች ሲሰሩ ዘወትር እንዲለበሱ ተደርጎ ለአረማመድ፣ ለአለባበስ ፣ ለሥራ እንዲለበሱና እንዳያስቸግሩ ሆነው ነውም ስትል ታብራራለች። ልብሶቹ በተመሳሳይ ለሰርግ፣ ለተለያዩ ዝግጅቶች እና ፕሮግራሞች እንዲለበሱም ተደርገው የሚሰሩበት አጋጣሚ እንዳለም ታነሳለች። ሰዎች እንደ ፕሮግራሞቻቸው አይነት በሚፈልጉት ዲዛይን እንዲሰራላቸው ይደረጋልም ነው ያለችው።

ዲዛይነር ደስታ እንደምትለው፤ ቀደም ብላ ውስጧ የነገራትንና ያምራሉ ብላ ያሰበቻቸውን ልብሶች ዲዛይን አድርጋ ታስቀምጣለች። በየጊዜው አዳዲስ ፈጠራ የታከለባቸውን ልብሶች ዲዛይን እያደረገች ለተጠቃሚው ታቀርባለች። ተጠቃሚው ቀደም ሲል ዲዛይን የተደረጉ ልብሶችን ከመረጠ በኋላ የሚፈልገው ካለ ይወስዳል። ካልሆነም በፍላጎቱ መሠረት ተሰርቶ ይሰጠዋል፡፡

የምትሰራቸው ልብሶች በሁሉም የእድሜ ክልል ውስጥ ያሉ ሰዎችን ታሳቢ ያደረጉ ናቸው።አብዛኞዎቹ ልብሶች ለሁሉም ሰው የሚሆኑ (free size) የሚባሉ አይነቶች ሲሆኑ፤ ለምሳሌ፡- ለሴት ቁመት ይሆናሉ የሚባሉ ተመጣጣኝ የተባሉ ልብሶች በተለያዩ ዲዛይኖች ተሰርተው ይቀመጣሉ።ይህን ልብስ አይታ ለመግዛት የፈለገች ሴት አጋጣሚ ቁመቷ አጭር ሆኖ ቀሚሱ ቢረዝማት ወዲያወኑ እንዲያጥርላት ይደረጋልም ትላለች።

ልብሶችን ዲዛይን ስታደርግ በተለየ መልኩ የራሷን አዳዲስ ፈጠራ ለመጠቀም ጥረት እንደምታደርግ የምታስረዳው ዲዛይነሯ፤ እነዚህን ሥራዎቿን በቴሌግራም፣ በሚሴንጀር እና በመሳሳሉት ላይ በማህበራዊ ሚዲያዎች በማስተዋወቅ ገበያ ትስባለች። በዚህም በተለያዩ ውጭ ሀገራት የሚኖሩት ደንበኞችን ማፍራት ችላለች።ሥራዎቿን እያዩ የሚፈልጉትን ልብስ እየወሰዱላት፤ ትዕዛዝ እንደሚሰጧትና ልብሶቹ ሰርታ በዲኤችኤል ኢትዮጵያ እና በኢትዮጵያ ፖስታ በኩል እንደምትልክላቸው ትገልጻለች።





**ከዲዛይነሯ ሥራዎች በከፊል**

‹‹በሀገር ባሕል ልብስ በፈለግነው መልኩ ብዙ ነገር መስራት ይቻላል።ቀደም ሲል ያሉ ዲዛይነሮችን ልብሱ ብዙ ነገር መሆን እንደሚችል ሠርተው አሳይተውናል።ልብሱ በጣም ያምራል፤ ሥራውም የሚወደድ ነው›› የምትለው ዲዛይነር ደስታ፤ ለባሹም የሚያምርበትና ወዶት የሚለብሰው እንደሆነ ትናገራለች።አሁን ላይ ብዙ ሰው ወደ ሀገር ባሕል አልባሳት እየተመለሰ በመሆኑ ውስጡ የወደደውንና ያማረው ልብስ መልበስ የሚችልበት እድል ተፈጥሯልም ብላ ታምናለች።

የልብሶቹ ዋጋ እንደልብሱ፣ እንደ ጥልፉና እንደ ጥበቡ አይነት ይለያያል የምትለው ዲዛይነሯ፤ ዋጋው ልዩ ልዩ ቢሆንም ልብሶቹ ግን ሁሉም ሰው ሊገዛቸው የሚችላቸው አይነት ናቸው።በተጨማሪም በትዕዛዝ ለማሰራት የሚፈልጉ ደንበኞች የልብሱን ዋጋ አይተው ነው ወደ ማሰራቱ የሚገቡት።ስለዚህም የባህል አልባሳት ዋጋ እንደፈላጊው የተመጣጠነ ነው ብሎ መውሰድ ይቻላልም ትላለች።

‹‹ አሁን ባለው የልብስ ገበያ ሁኔታ ሥራው አንድ አይነት ሆኖ ዋጋ ግን እንደ መሸጫ ቦታው ይለያያል፤ በሙያ ላይ ያለ ሰው ሁሉ በተለይ ህዝቡ የራሱን ልብስ እንዲለብስ ለማድረግ ለልብሶቹ የተጋነነ ዋጋ ባያስቀምጥ ጥሩ ነው።እኛ ዲዛይን የምናደርጋቸውን ልብሶች ሁሉም ሰው ገዝቶ እንዲለብሳቸውና እንዲያምርባቸው ጥረት ማድረግ አለብን።የለባሹን የመግዛት አቅም ያላገናዘበ ዋጋ በማቅረብ ህብረተሰቡ ማማረር ተገቢ አይደለም፡፡›› ስትል ታስገነዝባለች።ልብሶቻችን ባሕላዊ ይዘታቸውን ሳይለቁ ዘምነው እንዲለበሱ በማድረግ ኢትዮጵያዊ አለባበሳችንን ማቆየት ይጠበቅብናል።በዘመነ መልኩ ሰርተንና ዋጋውን ተመጣጣኝ አድርገንም በአለባበስ ትውልዱን መስራት ይኖርብናል ስትል መልዕክቷን ታስተላልፋለች።

አሁን ላይ ለአራት ሰዎች ሥራ እድል የፈጠረችው ዲዛይነር ደስታ፤ ይህንን ሥራ ሰፋ አድርጎ ለመስራት ገንዘብና መስሪያ ቦታ ግን ፈትኗታል።እነዚህ ሁሉ ከተመቻቹላት ከዚህም በላይ ሰዎችን መጥቀም እንደምትችል ጠቅሳ፣ ይህ ሲሆን ሥራዎቿን በስፋት ሰርታ ለተጠቃሚው ለማድረስ ምቹ ሁኔታን እንደሚፈጥርላት ታምናለች።በቀጣይም የሀገር ባሕል ልብስን ባህላዊ ይዘቱን ሳይቀይር ማዘመንና ሥራዎቿን ሰፋ አድርጋ ለመስራት ሀሳቡ አላት። እቅዷ ምርቶቿን ለሀገር ውስጥ ገቢ በተመጣጣኝ ዋጋ ማቅረብ ብቻ ሳይሆን ወደ ውጭ ኤክስፖርት ማድረግም ነው።ሥራዎቿን በማስፋት የተለያዩ ቅርንጫፎችን በመክፈት በመላ ሀገሪቱ ተደራሽ መሆንንም ትሻለች።በዚህ ሥራዋ ደግሞ ኢትዮጵያዊ ሁሉ በሀገሩ ምርት እንዲኮራ እንደምታደርግበትም እምነቷ ነው።

# ትዝብት/ ማረፊያ

## ሥራ ይዞ ሥራ ፍለጋ

**መክሊት ወንድወሰን**

በከፍተኛ የትምህርት ተቋም ሳለን ብዙ በጎዎችን ተስፋ እናደርጋለን። ዲግሪ ስላለን ብቻ ህይወት ቀላል እንደሆነች ይሰማናል። ከዩኒቨርሲቲ እንደወጣን ወዲያው በከፍተኛ ደሞዝ ጥሩ ሥራ አግኝተን፤ ዓመት ባልሞላ ጊዜ ለቤተሰቦቻችን ቤትና መኪና መግዛትን እናስባለን። ታናናሾቻችንን ጥሩ ትምህርት ቤት እያስተማርን ስናቀማጥል ይታየናል።እውነት ነው አብዛኞቻችን ከቤተሰቦቻችን ጫንቃ ወርደን የራሳችን ቤትና ቆንጆ መኪና መያዝን ወጥነነናል፣ አልመናል።

ከዩኒቨርሲቲ ከወጣን በኋላ ግን ህይወት እንዳሰብነው ቀላል አልሆነም። ስራ የለም፤ በየቦታው ለፈተና እንጠራለን መልስ የለም። በዚህ ፍለጋ ውስጥ እየኳተንበት ጫማ ቢንሻፈፍ፣ በየማስታወቂያ ሰሌዳው ያንጋጠጥንበት የሸሚዛችን ኮሌታ ቢያልቅ አይገርምም፡፡

የመጀመሪያ ሰሞን ከቤት ለስራ ፍለጋ ስንወጣ እጩ አምባሳደር መስለን፣ ከላይ እስከ ታች ዘንጠን ነው።በሂደትም በምረቃችን ቀን የተበረከቱልንን ሸሚዞችና ጥቂት የስራ መፈለጊያ የገንዘብ ኖቶች መመንዘር እንጀ ምራለን። የኮት ቤቱ ነገር ደግሞ አይወራ፤ ያልታወቀበት ስር ነቃይ ወጭ አለው፡፡

እናም በምረቃህ ማግስት ማስረጃህን በደርዘን በደርዘን ኮፒ አድርገህ ይዘህ መዞር ትጀምራለህ።ስትንከራተት መዋልህን የማያስተውሉት ቤተሰቦችህ ወጥተህ ስትመለስ "እህ እንዴት ነው ዛሬ?" በጥያቄ ይቀበሉሃል።አንተም ትደናበርና ምኑ ትላለህ።"ስራ ፍለጋው? በቀናነት አስበው የጠየቁህ ጥያቄ ያናድድህል፣ያበሳጭህል፡፡

አንተ በአናትህ የዋለው ፀሐይ፤ ትራንስፖርት ማጣቱ፤ የየመስሪያ ቤቱ ጥበቃዎች ማመናጨቅ፤ ውል ይልሀል። ከኪስህ ገንዘብ አጥተህ ቤተሰብ ለመጠየቅ ከመሳቀቁ ጋር ተደማምሮ ሆድ ይብስሃል፡፡

ወዲያው ውስጥህ ‹‹ተናገር፣ ተናገር፣›› ይልሀል። ወላጅ አባትህን ለመዳፈር ታስባለህ። ‹‹እና ‘ምንድነው? የሄድኩት እኮ አንተ አቋቁመኸው የረሳኸውን ድርጅት ላስተዳድር አይደለም፤’ ለማለት ያምርሃል። ነገር ግን ፈጽሞ አትለውም። ጥገኛ ነህና ትውጠዋለህ። እየተቅለሰለስክ ‹‹ምንም አዲስ ነገር የለም፤ ብዙ ቦታ አመልክቻለሁ ››ትላለህ።‘ ማመልከት ብቻ ምን ያደርጋል፤ መቼ ነው የሚቀጥሩህ?’ ይሉሃል።

‹‹ኸረ ተረዱኝ ወገን አሁን አመለከትኩ ማለት ይቀጥሩኛል ማለት አይደለም።‹‹ገና የጽሁፍ፣ የቃል ፈተና አለ›› እያልክ ልታስረዳ ስታስብ ይደክምሃል።ስንቱን አስረድተህስ ትዘልቀዋለህ!፤ በየቦታው ያሉ ጥበቃዎች እንደሚገላምጡህ፤ ከእግር እስከ ራስህ እያዩ ወዴት ነው? እንደሚሉህ አትናገርም።አንዳንዴ አዲስ ስራ ፈላጊ ስትሆን ከጽሁፍ ፈተናው ሳትደርስ ሊጥልህ የሚችለውን መመዘኛ ልብ አትልም። ጥበቃውን ኮራ ብለህ ‹‹ወደ ውስጥ ነዋ!›› ልትለው ትችላለህ፡፡

እንደዛ ካልከው እመነኝ አልቆልሃል። በያዘው ሽመል ወገብህን ሊልህ ይችላል።እና ልምከርህ ወዳጄ! ዋናው ፈተና የሚጀምረው ከጥበቃው በር ነው፡፡

‹‹ይቅርታ የኔ ጌታ›› ብለህ ንግግርህን ትጀምርና ‹‹እንደው የስራ ማስታወቂያ ወጥቶ ነበር፤ ለማመልከት መግቢያው በየት ይሆን?›› ትለዋለህ።ያኔ የልቡ ደጅ ወለል ይላል። በሩን ከፍቶ ቦታውን ጠቁሞ፣ እዛው አድርሶህ ይመለሳል። አንተም አባቴ ያራዳ ልጅ ከሆንክ አመስግነህ ዘው ነው፡፡

ውስጥ ከገባህም በኋላ ሁለተኛው ፈተና ይቀጥላል። የስራ ፈላጊዎችን ግለ መረጃ (ሲቪ) የምትሰበስበው ሰራተኛ ተጨንቀህ፣ ተጠበህ ‹‹ስለ ፈጣሪ፤ ለነብስ ይሆናችኋል ቅጠሩኝ›› ይል ይመስለውን ማመልከቻህን እያገላበጠችው ትቆያለች። ይህን ስታይ የተመራጭነት ስሜት ይሞላህና ትደሰታለህ፡፡

ወዲያው ግን እዚያ አስቀምጠውና ፎርም ሞልተህ ውጣ ትልሃለች። ማስረጃህን አንተ አሽሞንሙነህ እንዳመጣኸው ክብር የሚሰጠው ሰው የለም። ዞር ስትል ጠጣ አትዝለውም የሚያስብል፣ እንደ ጤፍ ክምር የተቆለለ ማስረጃ ታይና እንባህ ይቀራል፤ ግን አታለቅስም፡፡

የዛሬው ትዝብቴም ይህንን ሁሉ ውጣ ውረድ ታልፎ ስራው ተገኝቶ ‹‹እፎይ!›› ሲባል የሚከተለውን ሌላ ፈተና ያስቃኛል። በተለይ በባንክ ቤቶች ስለተቀጠሩ ጀማሪ ሰራተኞች።

አሁን አሁን የአብዛኞቹ ባንክ ቤቶች የገበያ ፉክክር ብልጠት ከተሞላበት የንግድ ስልት በፈረንጅኛው አፍ ‹‹strategic marketing›› መመራቱን የተወ ይመስላል። በየሱቁ፣ በየመንገዱ ከልመና ያልተናነሰ ድርጊትን ማየት ከተለመደ ሰነባብቷልና፡፡

በተለይ ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ ፈር የለቀቀ ይመስላል፤ የባንክ ባለሙያዎች በደቦ መንገድ ይዞ የአነጋግሩን ልማድ። ይህ የቁጠባ ሂሳብ ‹‹ክፈቱልን›› ልመና ህብረተሰቡን ከማሰልቸት አልፏል። የባንክ ቤት ሰራተኞቹንም ላልተገባ ጫና ብሎም ማሸማቀቅ እየዳረገ ነው። ይህን ደግሞ በየአጋጣሚው መታዘብ ችለናል።

ይህን ተከትሎ በትላልቅ ህንጻዎች ላይ አስገራሚ ማስታወቂያዎች መነበብ ጀምረዋል።“የባንክ ቤት ሰራተኞች እና የኔ ቢጤዎች መግባት ክልክል ነው፣” በሚል። ሰራተኞቹን ያዩ ጥበቃዎችም ዝም አይሉም። ከዱላ ባልተናነሰ ቁጣ ፊት ነስተው እያመናጨቁ ያስወጧቸዋል።

ነገሩ በዚህ ብቻ አይቀርም፤ እነዚህ የባንክ ሰራተኞች ቀደም ሲል በማህበረሰቡ ዘንድ የነበራቸው ክብር አብሯቸው የለም። በየአጋጣሚውና በየማህበራዊ ሚዲያው እጅግ የሚያሸማቅቁ ተረቦችን ሲያስተናግዱ ማየት ተለምዷል።

ከሰራተኞቹ ከፍ ሲል ባንኮቹ በዚህ ልክ ህብረተሰቡን እስከማሰልቸት የደረሰ የገበያ ስልት መምረጣቸው ያስገርማል። ሂደቱን ረዘም ላለ ጊዜ መከተላቸው ደግሞ አግራሞትን ያጭራል፡፡

ዓለም ከደረሰበት የቴክኖሎጂና ፈጠራ በመነሳት በየእለቱ እንደማህበረሰብ የሚያስደንቁ ጊዜ ወለድ አገልግሎቶችን እንጠብቃለን። ይህ አይነቱ አካሄድ በዚህ ከቀጠለ ግን የኢንዱስትሪውን የለውጥ ጊዜ እንደ ሚያረ ዝመው ጥርጥር የለውም፡፡

ሁሌም ቢሆን ማህበረሰቡ ከአገልግሎት ሰጪ አካላት አዳዲስ የገበያ ስልቶችን ይጠብቃል። ሂደቱ አስተማማኝና ማራኪ ቢሆን ደግሞ ለሁሉም ይበጃል። ከዚህ ረገድ አንዳንድ ባንኮች እያደረጉት ያለው ጥረት የሚበረታታ ነው። ዓለማችን መሽቶ ሲነጋ አፍ የሚያሲይዙ አዳዲስ ፈጠራዎችን ማየት ትሻለች። ይህን አይነቱ የተሰላቸ አሰራር ደግሞ የባንክ ኢንዱስትሪውን የገበያ ስልት የዳዴ ጉዞ አመላካች ነው ፡፡

ከሚሰማው መረጃ ማወቅ እንደሚቻለው በአንዳንድ ባንኮች አንድ የባንክ ሰራተኛ ከደንበኞች በወር በአማካኝ ከ40 እስከ 70 ደብተሮችን የማስከፈት ግደታ አለበት። እዚህ ላይ ለአንባብያን አንድ ጥያቄ ላንሳ፤ ምን ያህል የባንክ ደብተር ኖሯችሁ ምን ያህሉን ትጠቀሙበታላችሁ?

እንደ እኔ ፈልጌም ይሁን ለአሳዛኝ ፊቶች ስል ከከፈትኳቸው በርካታ ደብተሮች ከሁለቱ ውጭ ተጠቅሜ አላውቅም። እንደኔ የሰራተኞቹ መንከራተት እና እንድከፍትላቸው የሚያደረጉት የበዛ ጥረት መና መቅረቱ ሁሌም ያሳዝነኛል

ቁጠባ እጅግ አስፈላጊና ኢንቨስትመንትን የሚያበረታታ ነው። ይሁን እንጂ ሰዎች እንዲቆጥቡ ሲባል ደብተር ማስከፈት ብቻውን ሚና አይኖረውም።

የባንክ ኢንዱስትሪውን ለማሳደግና ኢንቨስትመንትን ለማበረታታት ያልተሰላቹና በስራቸው ደስተኛ የሆኑ የባንክ ቤት ሰራተኞች፤ ሊኖሩ ያስፈልጋል። አዳዲስ የገበያ ስልቶችና ልዩ የአገልግሎት አሰጣጦች መዘርጋታቸው ደግሞ በእጅጉ አስፈላጊ ነው።እንዲህ መሆኑ ሥራ ይዘው ሥራ ፍለጋን ለሚንከራተቱ የባንክ ሰራተኞች አይነተኛ መፍትሄ ይሆናልና።ትዝብቴን ቋጨሁ!

# ዓለም አቀፍ

## የካፒቶል ሒል አመጽን የመሩ ሁለት ሰዎች እስር ተፈረደባቸው

በጋዜጣው ሪፖርተር



በአሜሪካው ካፒቶል ሒል የተነሳውን ነውጥ መርቷል የተባለው 'ፕራውድ ቦይስ' የተሰኘው የቀኝ ጽንፈኛ አክራሪው ቡድን ሁለት አባላት እስር ተፈረደባቸው።

የቡድኑ አባልና የ46 ዓመቱ ዶሚኒክ ፔዞላ በፖሊስ ላይ ጥቃት በማድረስ እንዲሁም መንግሥታዊ ሥራዎችን በማደናቀፍ ክስ ቀርቦበት የ10 ዓመት እስር ተፈርዶበታል።

የ32 ዓመቱ ኢታን ሮርዲያን በበኩሉ ከሁለት ዓመት በፊት በአሜሪካ የምክር ቤት ጉባዔ ላይ ነውጠኞችን መርቷል የተባለው ከበድ ባለ በአመጽ ሴራ ክስ 18 ዓመት ተፈርዶበታል።

በከባድ የሴራ አመጽ 18 ዓመት የእስር ቅጣት የተፈረደበት ሮርዲያን ከብያኔው በፊት "በእለቱ በነበረው የአመራር ጉድለቴ ይቅርታ እጠይቃለሁ" ብሏል።

አክሎም የተነሳውን ሁከት "ፍጹም አሳዛኝ" መሆኑንም ነው የገለጸው። በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የበደልኳችሁ ሁሉ ይቅርታ አድርጉልኝ ሲልም ተናግሯል።

ነገር ግን የአሜሪካ ግዛት ዳኛ ቲሞቲ ኬሊ በዕለቱ የተከሰቱት ክስተቶች ሀገሪቷ ረዘም ላለ ጊዜ የገነባችውን የፖለቲካ ባህልን የገረሰሰ እንደሆነ ነው የተናገሩት።

"በዚህች ሀገር ሰላማዊ የሥልጣን ሽግግር ከሌለን ምንም የለንም" ሲሉ ዳኛ ቲሞቲ መናገራቸውን ቢቢሲ ዘግቧል።

ሩፊዮ ፓንማን በሚል ቅጽል ስም የሚጠራው ኖርዲያን ጸረ-ፋሺስት እና ዘረኝነትን ከሚታገለው አንቲፋ ከተሰኘው ቡድን ጋር በተደጋጋሚ ፍጥጫ ውስጥ በመግባትም ይታወቃል።

አርብ ዕለት የተፈረደበት የ46 ዓመቱ የቀድሞ የአሜሪካ የባህር ኃይል አባል ሲሆን ከፖሊስ ጋር በመታገል እንዲሁም መስኮት መስበሩም ተገልጿል።

የካፒቶል ሒል አመጽ ከተነሳ ሁለት ዓመት ሊደፍን ነው። የቀድሞው የአሜሪካ ፕሬዚዳንት ትራምፕ መሸነፍ ያልተቀበሉ ነውጠኛ ደጋፊዎች የጆ ባይደንን የምርጫ አሸናፊነት በመቃወም የምክር ቤት አባላቱን ጉባዔ ማወካቸው ይታወሳል።

የምክር ቤቱ አባላት ይነጋገሩ የነበረውም የጆ ባይደንን መመረጥ ለማጽደቅ ነበር።

ጆ ባይደን ለካፒቶል ሒል ግርግር ብቸኛውና አውራው ተጠያቂ ዶናልድ ትራምፕ እንደሆኑ በማያሻማ ሁኔታ መናገራቸው የሚታወስ ነው።

ከዚህ የካፒቶል ሒል ግርግር ትንሽ ቀደም ብሎ በምርጫ ተሸንፈው የነበሩት ዶናልድ ትራምፕ ነውጠኛ ደጋፊዎቻቸውን እስከመጨረሻው እንዲፋ ለሙ ቀስቅሰው ነበር።

ዶናልድ ትራምፕ ያን ወቅት ምርጫው መጭበርበሩን ደጋግመው ይናገሩ የነበረበት ጊዜ ነው።

በካፒቶል ሒል ግርግር ጥቂት ሰዎች ሞተዋል፤ 140 የሚሆኑ የጸጥታ አካላት ላይ ጉዳት ደርሷል። በወቅቱ የፖሊስ መርማሪዎች 725 ተጠርጣሪዎችን በቁጥጥር ሥር አውለው ምርመራ እያደረጉ መሆኑን አስታውቀው ነበር።

ከካፒቶል ሒል ግርግር በኋላ ተሰናባች የነበሩት ዶናልድ ትራምፕ ነውጥ በመቀስቀስ በሚል ክስ ተመስርቶባቸው የነበረ ሲሆን ያን ጊዜ በሪፐብሊካኖች ተሞልቶ የነበረው ሴኔት ግን ክሱን ውድቅ አድርጎት እንደነበረ ይታወሳል።

የካፒቶል ሒል ግርግር የአሜሪካ ሕዝብ በፖለቲካ ምን ያህል እየተከፋፈለ እንደመጣ ሁነኛ ማሳያ ተደርጎ በብዙ ተንታኞች ዘንድ ይወሳል።

ዲሲ የመንግሥት መቀመጫ ከተማ ናት። አሜሪካ በመንግሥታዊ ቅርጽ ስትወለድ ከፊላደልፊያ ወደ ዲሲ ማዞሯ ይታወሳል። ካፒቶል ሒል በዋሽንግተን ዲሲ የሚገኝ የቤተመንግሥት ዋና ግቢ ነው።

የመጀመርያው የአሜሪካ ፕሬዚዳንት ጆርጅ ዋሺንግተን የመንግሥት መቀመጫ ዲሲ ውስጥ እንዲሆን ሲወስኑ አንድ ኮረብታ ታያቸው። የጀንኪንስን ኮረብታ። ካፒቶል ሒል በጆርጅ ዋሽንግተን ተጸንሶ ቢወለድም በርካቶች የሚኅበኙት ሥፍራ ነው።

የአሜሪካ የመንግሥት መቀመጫን በአንድ ሕንጻ ማመላከት ከባድ ቢሆንም ምናልባት ለዚህ ቀረብ የሚለው ካፒቶል ሒል ነው። ለኢትዮጵያውያን የአራት ኪሎ ቤተመንግሥት ዕውቅ እንደሆነ ሁሉ ለአሜሪካውያኑ ደግሞ የመንግሥት ዋና መጨመጫን ሲያስቡ ቀድሞ ወደአዕምሯቸው የሚመጣው ካፒቶል ሒል ነው።

የላዕላይና የታህታይ ምክር ቤቶች ፓርላማ ሕንጻ የሚገኘው እዚህ ነው። የጠቅላይ ፍርድ ቤት የሚገኘውም በዚሁ ግቢ ነው። ኮንግረስ ላይብረሪ እዚህ ኮረብታ ላይ ነው። ዝርዝሩ ብዙ ነው።

ይህ ሕንጻ ብዙ ታሪክ የተሸከመ ነው። ለዚህ ነው የፖለቲካ ብቻ ሳይሆን የቱሪዝም መዳረሻም የሆነው።

ከሕንጻዎቹ ንጣትና ምስስሎሽ የተነሳ ዋይት ሐውስና ካፒቶል ሒል አንድ የሚመስሏቸው ብዙ ናቸው። በሁለቱ ሕንጻዎች መሀል ግን የሁለት ማይል ወይም የ3.2 ኪሎ ሜትር ርቀት አለ። የግብርም ልዩነት አለ። ካፒቶል ሒልና ዋይት ሐውስን በመጠን ቢነጻጸሩ ሰፊ ልዩነት አላቸው፤ ምክንያቱም ካፒቶል ሒል ግዙፍ ሕንጻ ነው።

በውስጡ የሚገኘው ኮንግረስ ቤተመጻሕፍት ብቻ 38 ሚሊዮን መጻሕፍት ይዟል።

የትራምፕ ደጋፊዎች ነውጥ ካላስነሱበት የካፒቶል ሒል ግርግር 13 ቀናት በኋላ ጆ ባይደን ሕንጻው ለፊት ቆመው 46ኛው ፕሬዚዳንት ሆነው ቃለ መሐላ መፈጸማቸው የሚታወስ ነው።

---

## የዘመን በረከት!

MInT
የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር

### ይህ ዓምድ ከኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር

ጋር በመተባበር በየሳምንቱ በሳይንስ፣ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ርዕሰ ጉዳዮች ዙሪያ ግንዛቤ የሚያስጨብጡ ዕትሞችን ይዞ ይወጣል

## የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የ2016 በጀት ዓመት እቅድ

የኢትዮጵያ ኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር በቴክኖሎጂና በኢኖቬሽን ስራና ሀብትን ለመፍጠር የምትመች ሀገር መፍጠርን ርዕይ አድርጎ የሚሰራ ነው፡፡ ይህንን ርዕይውን ለማሳካት በ2016 በጀት ዓመት የተለያዩ ዘርፎች ላይ ስኬታማ ስራዎችን ለማከናወን በእቅድ ውስጥ አስቀምጧል፡፡

የኢኖቬሽን ምርምርና ቴክኖሎጂ ልማትን ውጤታማ ለማድረግ በቁስ፣ በአሰራር ስርዓቶች እና በሰው ሃብት አቅም ግንባታ ረገድ ሰፋፊ ስራዎች ይሰራሉ፡፡ ከዚህ አኳያ ለኢኖቬሽን ምርምርና ቴክኖሎጂ ልማት አገልግሎት የሚውሉ መሰረተ ልማቶችን መገንባት እና ማደራጀት፣ የሠው ኃብት አቅምን መገንባት፣ ወሳኝ የሆኑ ተቋማትን ማቋቋም መደገፍና ማብቃት፣ እንዲሁም የአሰራር ስርዓቶችን መዘርጋትና ማጎልበት ትኩረት የሚሰጣቸው ቁልፍ ጉዳዮች ይሆናሉ፡፡

ሀገራዊ የዲጂታል ኢኮኖሚ ለመገንባት እና ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ተጠቃሚነትን ለማሳደግ የሚያስችሉ ሥራዎችን በመከወን ረገድ ሀገራዊ የዳታ ማዕከል መገንባት፣ የተቋማትን የኢንተርኔት ትስስር ሽፋንና የመጠቀም ደረጃን በማሻሻል በቀጥታ (Online) የሚሰጡ የመንግስት አገልግሎቶችን ማሳደግ፣ ሀገር አቀፍ የአድራሻ ሥርዓት መዘርጋት፣ ኮምፒውቴሽናል ቴክኖሎጂዎችን እና ብሄራዊ የዳታ ክምችቶችን ማልማት፣ እንዲሁም የመንግስት አገልግሎቶችን ተገልጋዮች በኤሌክትሮኒክ አግባብ እንዲያገኙ ማድረግ ቁልፍ ተግባራት ናቸው፡፡

ሀገራዊ ጠንካራ የኢኮኖሚ አቅም ለመገንባት የቴክኖሎጂ ኢንዱስትሪዎችን በመገንባት ምርታማነትና ተወዳዳሪነትን ማሻሻል በዕቅድ ዘመኑ ትኩረት የሚሰጠው ሲሆን ለዚህም የቴክኖሎጂ ማጎልበቻ፣ ማላመጃና ማሸጋገሪያ፤ ምርምሮችን ማካሄድና መደገፍ፤ የዲጂታል ቴክኖሎጂዎችን ማጎልበት፣ ማልማት፣ ማላመድና ማሸጋገር እንዲሁም ምርት፣ ምርታማነትንና ተወዳዳሪነትን ለማሻሻል የሚያግዙ ሀገራዊና ዓለም አቀፋዊ ትብብሮችን መፍጠርና ማጎልበት ትኩረት ይሰጣቸዋል፡፡

ቴክኖሎጂዎችን ከመምረጥ፣ ከማላመድ፣ ከመጠቀምና ከማስወገድ አንፃር የአሰራርና የሬጉላቶሪ ሥርዓቶች ወሳኝ ሚና አላቸው። የቴክኖሎጂ ልማትና አስተዳደር እንዲሁም የሬጉላቶሪ ሥርዓት የመዘርጋትና የማጎልበት ስራዎች ትኩረት ተሰጥቷቸው የሚከናወኑ ይሆናል።

የብሔራዊ ዲጂታል ኢኮኖሚ ልማት እና የአገልግሎት ዲጂታላይዜሽን ፕሮግራም የሀገሪቱን ዲጂታል ኢኮኖሚና አገልግሎቶች ለማሳደግ የታለመ ፕሮግራም ነው። ፕሮግራሙ ሁሉን አቀፍ፣ ዘላቂና የበለፀገ ዲጂታል አቅም ያለው ኢኮኖሚ መፍጠርን ታሳቢ ያደርጋል። ውጤታማ፣ ግልጽ እና ተጠያቂ የሆነ በዲጂታል ቴክኖሎጂ ላይ የተመሰረተ የመንግሥት አሰራር መፍጠር እና ዜጎችን፣ የንግድ ድርጅቶችን እና ሸማቾችን የሚጠቅም ይበልጥ ውጤታማ፣ ግልጽ እና ሁሉንም የሚያካትት የኢ-ኮሜርስ ገበያ ስርዓት እንዲዘረጋ ማድረግ የፕሮግራሙ ዋና አላማዎች ናቸው፡፡ ፕሮግራሙ የኢ-መንግስት መተግበሪያዎች እንዲለሙ እና የአሰራር ሂደቶችን አውቶሜት በማድረግ፣ የወረቀት ስራዎችን በመቀነስ አገልግሎት ተቀባዮች ባሉበት ሆነው አግልግሎት እንዲያገኙ በማድረግ ፕሮግራሙ የኢትዮጵያ የመንግስት አገልግሎቶችን በማዘመን ላይ ጉልህ አስተዋፅኦ ይኖረዋል።

በተጨማሪም የመንግስት ለመንግስት ግንኙነቶቸን እና መንግስት ከንግድ ተቋማት ጋር የሚያደርገው ግንኙነቶችን የተሳለጠ፣ ግልፅ አዋጭ እና ከአድልዎ የፀዳ ለማድረግ የሚያስችሉ የዲጂታል ፕላትፎርም የአሰራር ስርዓቶች በማልማት መልካም አስተዳደር እንዲሰፍን ይረዳል በተጨማሪም ፕሮግራሙ የኢ-ኮሜርስ ጥቅም ላይ ግንዛቤ እንዲፈጠር በማድረግ፣ የንግድ ድርጅቶችና ሸማቾች የኢ-ኮሜርስ ፕላትፎርሞችን እና አሰራሮችን እንዲጠቀሙ በማበረታታት እና ለኢ-ኮሜርስ ልውውጥ አሰራር ስርዓት እና ደረጃዎችን በማውጣት እና ሸማቾችን ከአደጋ እንዲጠብቁ የሚያደርጉ የአሰራር ስርዓቶች እንዲዘረጉ በማድረግ የኢ-ኮሜርስ ልማት በኢትዮጵያ እንዲፋጠን ያደርጋል።

ብሔራዊ የሳ.ቴ.ኢ ልማት ፕሮግራም በኢትዮጵያ ውስጥ ያለውን የሳይንስ፣ ቴክኖሎጂ እና ፈጠራ ለማዳበር የተዘጋጀ ፕሮግራም ነው። ፕሮግራሙ በፈጠራ እና በምርምር የሚመራ በእውቀት ላይ የተመሠረተ ኢኮኖሚ ለመፍጠር ያለመ ነው፡፡ ፕሮግራሙ ጥራት ያለው የምርምር የሰው ኃይል በመገንባት፤ አዳዲስ ፈጠራዎችን እና የፈጠራ ውጤቶችን የንግድ ልውውጦችን (Commercialization) በማስፋፋት፤ የሳቴኢ አስተዳደር እና አመራርን በማሻሻል የሳ.ቴ.ኢ ምርምርና ልማት ማጠናከርን ዓላማ አድርጓል።

ፕሮግራሙ በኢትዮጵያ የሚገኙ የሳ.ቴ.ኢ ተመራማሪዎችንና ሳይንቲስቶችን ቁጥር እንዲጨምር፤ የሀገሪቱን ችግሮች ለመፍታት ጥቅም ላይ ሊውሉ የሚችሉ አዳዲስ የሳ.ቴ.ኢ ዕውቀትና ቴክኖሎጂዎችን እንዲዳብሩ በማድረግ፤ የሀገሪቱን ኢኮኖሚ ፍላጎት ማሟላት የሚችል በሳ.ቴ.ኢ የተግባር ዕውቀት ያለው የሰው ኃይል እንዲፈጠር አስተዋፅኦ በማድረግ አዳዲስ የስራ ዕደሎች እንዲፈጠሩ እና የሀገራችን ኢኮኖሚ በ ሳ.ቴ.ኢ የተደገፈ እንዲሆን አስተዋጸኦ የሚያደርግ ነው።

ብሔራዊ የሳ.ቴ.ኢ መሰረተ ልማት ፕሮግራም በፈጠራና በፈጠራ ችሎታ የሚመራ በእውቀት ላይ የተመሰረተ ኢኮኖሚ ለመፍጠር የሀገሪቱን ሳይንስ፣ ቴክኖሎጂና ፈጠራ ሊደግፍ የሚያስችል መሰረተ ልማትን ማዳበር ላይ ትኩረት የሚያደርግ አገራዊ ፕሮግራም ነው። እንደ ላብራቶሪ፣ ቤተ መጻሕፍት እና የምርምር ተቋማትን መገንባትን ወይም ማሻሻልን፤ የኢንኩቤሽን እና አክስለሬሽን (Incubation & acceleration) ማዕከላትን መገንባት፣ የብሮድባንድ የኢንተርኔት አገልግሎቶች ማስፋፋት፣ የዳታ ማዕከላት እና የክላውድ ኮምፒዩተር አገልግሎቶችን እንዲለሙ በማድረግ በሀገሪቱ የሳ.ቴ.ኢ መሰረተ ልማት እንዲሻሻል ለማድረግ ዓላማ ያደረገ ነው።

ከመሰረተ ልማቶች ባሻገር ፕሮግራሙ የሳ.ቴ.ኢ ውጤቶች ወደ ንግድ ልውውጥ እንዲገቡና በተመራማሪዎች፣ የንግድ እና በመንግሥት ድርጅቶች ባሉ የሳ.ቴ.ኢ ተዋናዮች መካከል ያለውን ትብብር በማቅለል የሳ.ቴ.ኢ መረጃዎችን በቀላሉ ማግኘትና ማሰራጨት እንዲችለ በማድረግ ለሳቴኢ ልማት አስተዋጽኦ ያደርጋል። የሳይንስ, ቴክኖሎጂ እና ኢኖቬሽን (ሳ.ቴ.ኢ) ሬጉላቶሪ ፕሮግራም የሳ.ቴ.ኢ ልማት፣ አጠቃቀም እና ኮሜርሻላይዜሽን ሥራ ላይ የሚያተኩሩ የድጋፍ እና የቁጥጥር ስርዓቶችን መዘርጋትና ተግባራዊ ማድረግ ነው። የሳቴኢ የሬጉላቶሪ ፕሮግራም የሳ.ቴ.ኢ ውጤቶች እና አገልግሎቶች አደጋ በማያስከትል እና ኃላፊነት በተሞላበት ሁኔታ ጥቅም ላይ እንዲውሉ በማድረግ ማህበረሰቡ ከሳ.ቴ.ኢ ተገቢውን ጥቅም እንዲያገኙ በማድረግ ጤናማ የሆነ የሳ.ቴ.ኢ ስነ ምህዳር እንዲገነባ ያደርጋል።

ፕሮግራሙ በኢትዮጵያ ውስጥ ተገቢ የሆነ የሳይንስ፣ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን (STI) ስርዓት ለማልማት የሚያስችል የሳ.ቴ.ኢ የሪጉላቶሪ ማዕቀፍ እንዲለማ በማድረግ አዳዲስ የፈጠራ ስራዎች በቀላሉ ወደ ስራ እንዲገቡ ምቹ ሁኔታዎችን ታሳቢ ያደረገ ነው፡፡ ፕሮግራሙ የምርምር አሰራርን እና የሥነ-ምግባር ሁኔታዎችን የሚደነግጉ የአሰራር ስርዓቶችን መዘርጋትን፤ ሳ.ቴ.ኢን የሚጠቀሙ ምርቶችና አገልግሎቶች ደህንነትና ውጤታማነትን የሚቆጣጠሩ አሰራሮችን ተግባራዊ ማድረግ እና፣ የአዕምሮ ንብረት ባለቤትነትን እና አጠቃቀምን የሚቆጣጠሩ፣ የፈጠራ ባለቤትነት ወይም የቅጂ መብት የአዕምሮ ንብረቶችን የሚመለከቱ የህግ ማዕቀፎችን ስራ ላይ ማዋል፤ የሳ.ቴ.ኢ ምርምርና ልማት የገንዘብ ድጋፍ የሚያደርግባቸው የአሰራር ስርዓቶችን፤ የሳ.ቴ.ኢ ላብራቶሪ እና የምርምር ማዕከላት እውቅናን እና የባለሙያዎችን ትምህርትና ስልጠና የሚቆጣጠሩ አሰራሮችን መዘርጋትን የመሳሰሉ ስራዎችን የሚያካትት ነው።

The Ethiopian Herald
አዲስ ዘመን
BARIISAA
العلم
ወጋሕታ
BAKKALCHO
የህትመት ውጤቶቻችንን ለማንበብ ድረገጻችንንና ፌስቡክ ገጻችንን ይጎብኙ!
የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት
ዌብሳይት፡- www.press.et
ፌስቡክ፡- Ehiopian Press Agency

አዲስ ዘመን ስፖርት

ይህ ቦታ ለማስታወቂያ ክፍት ነው!

# ወላይታ ሶዶና አዲስ አበባ የፓይለት ፕሮጀክቶች ዋንጫ አሸነፉ

ዓለማየሁ ግዛው

በኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌዴሬሽን መሪነት በሲዳማ ክልል ይርጋለም እና ሃዋሳ ከተሞች አስተናጋጅነት ሲካሄድ የቆየው ከ16 ዓመት በታች የፓይለት ፕሮጀክቶች የእግር ኳስ ምዘና ውድድር ፍጻሜውን አግኝቷል። ለዋንጫ በተደረገው ፍልሚያም በወንዶች ወላይታ ሶዶ በሴቶች ደግሞ አዲስ አበባ ከተማ የፓይለት ቡድኖች አሸንፈዋል።

ከነሃሴ 16/2015 ዓ.ም አንስቶ በሃዋሳ እና ይርጋለም ከተሞች በርካታ ጨዋታዎች ሲከወኑ የቆዩ ሲሆን፤ ነሃሴ 26/2015 ዓ.ም በደማቅ ሁኔታ ተጠናቋል። በሁለቱም ጾታዎች ለዋንጫ እና ለደረጃ ያለፉ ቡድኖችም ተለይተዋል። በአሁኑ ወቅት በርካታ መሰል የታዳጊ እግር ኳስ ውድድሮች በአንዳንድ የሀገሪቱ ክፍሎች እየተከናወኑ ሲሆን ተተኪ እግር ኳስ ተጫዋቾችን በማፍራቱ ረገድ የጎላ ሚና ይጫወታሉ ተብሎ ይጠበቃል። በእግር ኳስ ፌዴሬሽኑ የሚዘጋጁት የፓይለት ፕሮጀክቶች የምዘና ውድድሮች ከሌሎቹ ውድድሮች ይበልጥ ትኩረት ስለሚሰጣቸው ለታዳጊዎቹ የተሻለ የመታየት እድልን እንደሚፈጥሩም ታምኖባቸዋል።

በወንዶች ይርጋለም ስታዲየም 16 ፕሮጀክቶች በአራት ምድቦች ተከፍለው የምድብ ማጣርያቸውን ሲያደርጉ ቆይተዋል። ቡድኖቹ የምድብ ማጣርያ ፍልሚያቸውን ካደረጉ በኋላ ከየምድቡ ለጥሎ ማለፍ መድረስ የቻሉ ቡድኖች ውድድራቸውን አከናውነው የግማሽ ፍጻሜ ተፋላሚዎች ሊለዩ ችለዋል። ለዋንጫ በተደረገው ፍልሚያም ወላይታ ሶዶ ፓይለት ፕሮጀክት አርባምንጭ ከተማ ፓይለት ፕሮጀክትን ገጥሞ በመለያ ምት በማሸነፍ የዋንጫ ባለቤት መሆን ችሏል። በዚህም አርባ ምንጭ ከተማ በግማሽ ፍጻሜ ጨዋታ ሻሸመኔ ከተማን በመለያ ምት 4-3 በማሸነፍ ለፍጻሜ ሊደርስ ችሏል። ወላይታ ሶዶ ፓይለት እንዲሁ አፋር ሰመራ ፓይለትን በመለያ ምቶች 3-1 አሸንፎ ለፍጻሜው ፍልሚያ በመድረስ ዋንጫውን የግሉ አድርጓል። ለደረጃ በተደረገው ጨዋታ ደግሞ ሻሸመኔ ከተማ ፓይለት ፕሮጀክት አፋር ክልል ፓይለትን ፕሮጀክትን 4-2 በመርታት 3ኛ ደረጃን በመያዝ አጠናቋል።




ወላይታ ሶዶ ፓይለት ፕሮጀክት የወንዶችን ውድድር በማሸነፍ ዋንጫ አንስቷል፤

በተመሳሳይ የተደረገው የሴቶች ፓይለት ፕሮጀክቶች ምዘና ውድድር አስር ቡድኖችን ያካተተ ሲሆን፤ በሁለት ምድቦች ተከፍለው ውድድራቸውን በማድረግ ቡድኖቹ ለዋንጫና ለደረጃ በመፋለም ውድድራቸውን ቋጭተዋል። በሴቶች ለዋንጫ በተደረገው ፍልሚያ አዲስ አበባ ከተማ ፓይለት ሲዳማ ክልል ፓይለትን በመለያ ምቶች 5-4 አሸንፎ ዋንጫውን ከፍ አድርጓል። በግማሽ ፍጻሜው ጨዋታ ሲዳማ ክልል ፓይለት ጋምቤላ ከተማ ፓይለትን 3-2 አሸንፎ የዋንጫ ተፋላሚ መሆኑን ሲያረጋግጥ ተጋጣሚው አዲስ አበባ ፓይለት አዳማ ከተማ ፓይለትን በመለያ ምት 4-2 አሸንፎ ለፍጻሜ ደርሷል። ለደረጃ በተደረገው ጨዋታም አዳማ ከተማ ፓይለት የጋምቤላ ክልል ፓይለትን 3-2 በማሸነፍ 3ኛ ደረጃን በመያዝ አጠናቋል።

በውድድሩ በሁለቱም ጾታ ከ1ኛ-3ኛ ይዘው ለጨረሱ ቡድኖች የወርቅ፣ የብርና ነሃስ ሜዳሊያ የተበረከተላቸው ሲሆን ከ1ኛ-4ኛ ደረጃን ይዘው ላጠናቀቁ ቡድኖችም የትጥቅ ድጋፍ ተደርጎ ውድድሩ ፍጻሜውን አግኝቷል። በተጨማሪም በውድድሩ ጥሩ ሥነ ምግባር ያሳዩ ቡድኖች የጸባይ ዋንጫ ተበርክቷል፤ በወንዶች ወላይታ ሶዶ በሴቶች ደግሞ ሲዳማ ክልል ፓይለትም ዋንጫዎቹን መውሰድ ችለዋል።

በ2015 ዓ.ም የፓይለት ፕሮጀክት ውድድር ከሁሉም የሀገሪቱ ክፍሎች የተውጣጡ የታዳጊ ፕሮጀክቶች የሚሳተፉበት ሲሆን የኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌዴሬሽን ከሚያካሄዳቸው ዓመታዊ የታዳጊዎች ውድድር ውስጥ አንዱ ነው። ለአንድ ሳምንት ሲካሄድ የቆው ውድድር ዓላማውም በእግር ኳሱ ብቃት ያላቸውን እና ተተኪ እግር ኳስ ተጫዋቾችን በዘላቂነት ማፍራትን ታሳቢ ያደረገ ነው። ፌዴሬሽኑ እምቅ አቅም ያላቸውን ታዳጊዎች መረጃ በመያዝ ወደ ፊት በሚኖሩት የታዳጊ ልማት መርሃ ግብሮች ላይ እንዲካተቱም ጥረት እንደሚያደርግ ውድድሩ በተጀመረበት ወቅት መጠቆሙ ይታወሳል።

---

ከኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ጋር በመተባበር በየሳምንቱ የሚታተም

# የማከፋፈያ ጣቢያዎችን አቅም የማሳደጉ ግብ

ቀደም ሲል የነበረው የኃይል አቅርቦት ውስን ስለነበር የኃይል ማከፋፈያ ጣቢያዎችም አቅማቸው በዚያው ልክ የተቃኘ ነበር።ከቅርብ ዓመታት ወዲህ መንግሥት እንደሀገር የኤሌክትሪክ ኃይል አቅምን ለማሳደግ ትኩረት መስጠቱን ተከትሎ ከተለያዩ አማራጮች ኃይል ማምረት እየተቻለ ነው።ከዚሁ ትይዩ የኃይል ማከፋፈያ ጣቢያዎች እየተገነቡ ሲሆን የቀድሞዎቹንም አቅም የማሳደግና የማስፋፋት ሥራ ተሠርቷል።አቶ ሙሉጌታ አየልኝ የሰበታ -2 ከፍተኛ የኤሌክትሪክ ኃይል ማከፋፈያ ጣቢያ ኃላፊ እንደሚገልጹት፤ በኢትዮጵያ የመጀመሪያው ባለ 400 ኪሎ ቮልት የሰበታ ሁለት ኃይል ማከፋፈያ ጣቢያ ነው።በ1998 ዓ.ም ተጀምሮ 2002 ዓ.ም የግንባታ ሥራው የተጠናቀቀው የሰበታ ሁለት ኃይል ማከፋፈያ ጣቢያ ከግልገል ጊቤ ሁለት ኃይል ማመንጫ ጣቢያ የሚመረተውን ኃይል ለመቀበል ታስቦ የተገነባ ነው። ጣቢያው 2 ባለ 250 ሜጋ ቮልት አምፒር (MVA) ትራንስፈርመሮች አሉት።

ሰበታ ቁጥር ሁለት ማከፋፈያ ጣቢያ ኃይል የሚቀበልባቸው ባለ 400 ኪሎ ቮልት አራት ገቢ መስመሮች አሉት።እነሱም በነጠላ መስመር ከጊቤ ሁለት ኃይል ማመንጫ ጣቢያ እና ከቃሊቲ ቁጥር ሁለት ኃይል ማከፋፈያ ጣቢያ እንዲሁም በጥንድ መስመር ከሆለታ ኃይል ማከፋፈያ ጣቢያ የሚቀበላቸው ናቸው። የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ማከፋፈያ ጣቢያዎች እርስ በርስ የተሳሰሩ ናቸው።የሰበታ ቁጥር ሁለት ኃይል ማከፋፈያ ጣቢያ ኃይል ከሌሎች ጣቢያዎች እንደሚቀበል ሁሉ ወደ ሌላ እንዲሰጥ ተደርጓል።ለዚህም ባለ 230 ኪ.ቮ በጥንድ መስመር ለሰበታ ባቡር ጣቢያ እና ባለ230 ኪ.ቮ በጥንድ መስመር ለሰበታ አንድ ኃይል ማከፋፈያ ጣቢያ ይሰጣል።



አቶ ሙሉጌታ አየልኝ

በተጨማሪም ሰበታ በኦሮሚያ ክልል የኢንዱስትሪ ዞን ተብለው ከተለዩ ከተሞች አንዱ በመሆኑ ለአካባቢው ነዋሪና ኢንዱስትሪዎች የሚያገለግሉ ቀድመው ከነበሩት 10 ባለ 33 ኪሎ ቮልት ወጭ መስመሮች ላይ ሌሎች 10 ባለ 33 ኪሎ ቮልት ወጭ መስመሮች እንዲኖሩት ተደርጓል፡፡

እያደገ የመጣውን የኃይል ፍላጎት ለመመለስ ከ2011 እስከ 2014 ዓ.ም ባለው ጊዜ የጣቢያውን አቅም የማሳደግና የማስፋፋት ሥራዎች ተሠርተዋል።በዚህም መሠረት አንድ ባለ 125 አዲስ (MVA) ትራንስፎርመር የመትከል ፣የብሬከር፣ የዲስ ኮኔክተር፣ የባዝባር፣ ለውጦች ተደርገዋል።ጣቢያው በተከናወነለት የአቅም ማሳደግ ሥራ በተጨማሪ 100 ሜጋ ዋት እንዲያስገኝ አስችሏል፤ ይህም ጣቢያው ቀድሞ ይሰጥ ከነበረው 80 ሜጋ ዋት 180 ሜጋ ዋት እንዲሰጥ አስችሏል።የተጨመረው 100 ሜጋ ዋት ከፍተኛ ኃይል የሚያስፈልጋቸው ከ10 በላይ ፋብሪካዎችን መሸፈን የሚችል ነው።

በአቅም ማሳደግ ሥራው የተተከለው ትራንስፎርመር ዘመኑ የደረሰበትን ቴክኖሎጂ የተላበሰና ሲስተሙ በኮምፒውተር መነበብ የሚችል ነው።ይህም ኦፕሬተሮች ከትራንስፎርመሩ ጋር ንክኪ ሳያደርጉ በኮምፒውተር ታግዘው ሥራቸውን እንዲያከናውኑ አስችሏቸዋል።

ቀደም ሲል የነበሩት ወጪ መስመሮች ሙሉ ለሙሉ በተጠቃሚዎች በመያዛቸው ምክንያት በአካባቢው ያለውን የኢንቨስትመንት ፍላጎት በተወሰነ መልኩ ገድቦት ነበር ያሉት ኃላፊው፤ ከተደረገው ማሻሻያና ማስፋፊያ በኋላ ጥያቄዎችን ከመመለስ ባሻገር በቀጣይ ለሚኖሩ የኃይል ፍላጎቶች ተጠባባቂ ወጪ መስመሮችን አዘጋጅቶ ማስቀመጥ ተችሏል።

የማስፋፊያ ሥራ አንዴ ተሠርቶ የሚቆም አይደለም ያሉት አቶ ሙሉጌታ፤ በቀጣይም የፋብሪካዎችንና የተጠቃሚዎችን የኃይል ፍላጎት ከአቅርቦት ጋር ለማጣጣም የማስፋፊያ ሥራዎች እንደሚኖሩ ተናግረዋል።

እንደ አገር 400 ኪሎ ቮልት የኃይል ማከፋፋያ ጣቢያዎች ለፋብሪካዎችና ለመለስተኛ ኃይል ማከፋፋያዎች ከሚሰጡት ኃይል በተጨማሪ የብሄራዊ ኃይል ቋቱን ከማረጋጋት አንጻር የሚጫወቱት ሚና ከፍተኛ ነው።ቀጥታ ግንኙነታቸው ከኃይል ማመንጫ ጣቢያዎች ጋር በመሆኑ ሲስተሙ እንዳይዋዥቅ ወይም በመላ ሀገሪቱ ኃይል እንዳይቋረጥ እገዛ ያደርጋሉ። አብዛኛዎቹ የሀገሪቱ ማከፋፈያ ጣቢያዎች እርስ በእርስ የተሳሰሩ መሆናቸውን የተናገሩት ሃላፊው፤ በተለያዩ ምክንያቶች አንዱ ጣቢያ ከሥራ ውጭ ቢሆን ሌሎች ጣቢያዎች የእርሱን ሚና ተክተው ሊሠሩ እንዲችሉ ተደርገው የተሳሰሩ መሆናቸውን አስረድተዋል።

የኃይል ማከፋፋያ ጣቢያው በየጊዜው አቅሙን ለማሳደግና የኃይል አቅርቦት ፍላጎትን ለማርካት የማስፋፊያና የአቅም የማሳደጊያ ሥራዎችን የመሥራት እንዲሁም አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን የመጠቀም ጥረቶችን ያደርጋል፤ በዚህም አበረታች ለውጦችን እያመጣ መሆኑን ተናግረዋል።ይሁንና በኤሌክትሪክ መሠረተ ልማት ላይ የሚፈጸመው ስርቆት የተቋሙን ስኬታማ ጉዞ እየገታው እና ባሰበው ልክ እንዳይራመድ ደንቃራ እንደሆነበት አቶ ሙሉጌታ ገልጸዋል።

ቀደም ባሉት ዓመታት ኤሌክትሪክን የመጨረሻው ተጠቃሚ ድረስ ለማድረስ ፈተና የነበረው የኃይል እጥረት እንደነበር ያስታወሱት ኃላፊው፤ ይህ ችግር ተፈትቶ በመላ ሀገሪቱ ፍትሃዊና ያልተቆራረጠ የኃይል አቅርቦትን ለማዳረስ ሥራዎች እየተሠሩ ባለበት በአሁኑ ሰዓት ግን በኤሌክትሪክ የብረት ምሰሶዎች ላይ የሚደረገው ስርቆት ትልቅ ፈተና እየሆነ መምጣቱን ተናግረዋል።ከብረት ማማዎቹ ላይ ግማሽ አካላቸው ሲሰረቅ እስከ መውደቅ ይደርሳሉ።በዚህ የተነሳ መብራት ስለሚቋረጥ በርካታ አገልግሎቶች ይቋረጣሉ፤ ተቋሙም የሚሰጠው አገልግሎት ሲስተጓጎል የሚያጣው ገቢና ለጥገና የሚያወጣው ወጪ ከፍተኛ መሆኑን ተናግረዋል። ህብረተሰቡ ተጎጂው እኔ ነኝ የሚል መንፈስ ተላብሶ የኤሌክትሪክ መሠረተ ልማቶችን እንዲጠብቅም ጥሪ አስተላልፈዋል።

የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል